# በእምነት መኖር
# Living by Faith

## ከምኒልክ አስፋውና ከተስፋዬ ሮበሌ

**ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር**
**የመልእክት ሣጥን ቍጥር** 23045፤ **ኮድ** 1000
**አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ**

# ማውጫ

መግቢያ....................................... ...................................

እምነት በብሉይና በአዲስ ኪዳን ..........................................

የሚሠራ እምነት እንዴት ያለ እምነት ነው?.........................

እምነት እንዴት ሊያድግ ይችላል? .......................................

እምነትና ፈውስ...................................................................

የእምነት እንቅስቃሴ ታሪካዊ ዳራ.........................................

የእምነት እንቅስቃሴ ስለ እምነት ያለው አስተምህሮ ..............

እግዚአብሔር እምነት አለውን? ............................................

እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው በእምነት ነውን?..................

እግዚአብሔር ለመፍጠር ቃላትን የግድ መጠቀም አለበትን?..

ጤንነትና ብልጽግና................................................................

ርእስ - በእምነት መኖር
Title - Living By Faith.

አሳታሚ - ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር
Publisher - Tesfa Evangelical Society For Apologetics.

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
Copyright 2002 - Tesfa Evangelical Society For Apologetics.

ያላሳታሚው ፈቃድ አብዝቶ ማሳተም ማሳተምም ሆነ የተወሰነን ክፍል በተለያዩ መንገዶች ማራባት በጥብቅ የተከለከለ ነው። በማንኛውም መልኩ መረጃን ለመውሰድ ከተፈለገ፣ በትክክል ሥርዐቱን ጠብቆ ሊጠቀስ፣ በግርጌ ማስታወሻ ሊግላከት ይገባዋል።
All rights reserved. No part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted in any form or by any means - electronic, mechanical, photocopying, recording, or other wise - without the prior written permission of the publisher and copyright owner.

ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ወይም ጥያቄ፣ አስተያየትም ሆነ ሂስ ካልዎ በሚከተለው አድራሻ ይጻፉልን፤

ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር
የመ. ሣ. ቁጥር 23045 ኮድ 1000
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

Comments, questions,and criticisms of this booklet are welcome. Please address all correspondence to The Evangelical Society For Apologetics

The Evangelical Society For Apologetics
Post Office Box 23045, Code 1000
Addis Ababa, Ethiopia

# የእምነት እንቅስቃሴና መዘዙ
# እምነት በእምነት ላይ ወይስ በእግዚአብሔር?

**ከምኒልክ አስፋውና ከተስፋዬ ሮበሌ**

## መግቢያ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ «*እምነት*» የሚለው ቃል ፍጹም ባዕድ በሆነ መንገድ ሲተረጐምና ሲገለጽ ይታያል። ቃሉ ከፍጡራን ጋር መያያዙ እየቀረ፣ ከፈጣሪ ጋር መያያዝ ከጀመረ ከሁለትና ሦስት ዐሥርታት በላይ ሆኖአል። እንደሚባለው ከሆነ በእምነት የምንኖረው እኛ ምድራውያኑ ብቻ አይደለንም፤ ሰማያዊውም እግዚአብሔር ይህን ዓለም የፈጠረውና የወደደውን ማድረግ የሚችለው በእምነት ነው። ጆሮአችን እንዲ የመሰለውን አነጋገር መስማት ከጀመረ ሰንበትበት ብሎአል።

ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ስንነሣ፣ ዐላማችን ያደረግነው፣ ሙግትን ወይም ሒስን አይደለም። ደግሞም ሐሰተኛ መምህራኖችን እየጻንን ለማጋለጥ አይደለም፤ እውነትን በፍቅር ለመናገር እንጂ (ኤፌ 4÷15)። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለማንሣት የሞከርናቸውን ርእሰ ጉዳዮች ከተለያየ አቅጣጫ ለማገናዘብ ጥረናል። በአንድ በኩል ለነገረ መለኮታዊ ትንታኔው ሰፊ ቦታ ሰጥተናል። የእምነትን ምንነት የሚገልጹ ምንባቦችን ስንጠቅስ ዐውዳዊ፣ ታሪካዊ፣ ሥነ ልሳናዊና (ሰዋስዋዊና) ነገረ መለኮታዊ ይዞታቸውን በተቻለ ዐቅም ለማመራመር ሞክረናል። በሌላ በኩል ደግሞ ለታሪካዊ ቅኝቱም ስፍራ ሰጥተናል።

በዚህ ዘመን የምንኖር ክርስቲያኖች ድንገት የተገኘን አይደለንም። ከቀድሞዎቹ ጋር ጥብቅ ትስስር አለን። በብዙ ነገር ከእኛ ቀዳሚ የሆኑ ሰዎች በርእሰ ጉዳዩ ላይ ምን ብለው እንደ ጻፉ ወደ ኋላ መለስ ብለን ብንቃኝ ፣ ብዙ ትምህርት እናገኛለን። እንዲህ ለማድረግ የፈለግነው በተቻለን ዐቅም ጥንቁቅ ሥራ ለማከናወን በማሰብ ነው። ብርቱ ጥንቃቄ አድርገንም፣ በዚህና በዚያ ምንባብ ላይ የሰጣችሁት «ሐቲታዊ ብያኔ» (exegetical decision) ፍትሕ ይጐድለዋል ልንባል እንችላለን። ከፍ ሲል እንዳመለከትነው ዐላማችን ግልጽ ነው እውነትን በፍቅር መነጋገር። ሐቲታዊ ብያኔአችን መዛባቱ በተጨባጭ ከተነገረን እንታረማለን።

ግን አንድ ሥጋት አለን። ይኸውም «*ኧረ ወገኖች ይህ አስተምህሮ እኮ ትክክል አይደለም*» በማለት ነገሩን በደፈናው ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያት በመስጠት የሚነገረውና የሚሰበከው ቃል በፍጹሙ መለኪያ እንዲመዘን ሐሳብ የሰጡ የእግዚአብሔር ሰዎች ብዙ «ታርጋ» ተለጥፎባቸዋል፤ አንዳንዶቹ «የተቀቡ አገልጋዮች ጠላት» ተደርገው ሲቈጠሩ፣ ሌሎቹ ደግሞ «የቅዱሱ መንፈስ ጠላት» ተደርገው ተፈርጀዋል። ምናልባትም ይህን ሁሉ ያልነው እኛም ይህ ዕጣ ፈንታ እንዳይደርስብን በመሥጋት ቢሆንስ! ሥጋት ቢይዘን አይፈረድብንም። ብቻ ለሁላችንም የሚበጅ ነገር ለማለት እንወዳለን። ክርስትና የሐቅ ብቻ ሳይሆን የኅሊናም ወዳጅ ነው። ማለትም እውነትን ኅሊናዊ፣ ምክንያታዊና አመክንዮአዊ በሆነ መንገድ የሚያቀርብ ነው። ስለ እውነት ሲሟገት በጭፍንነት አይሟገትም፤ ምክንያታዊና አመክንዮአዊ በሆነ መንገድ እንጂ። ኅሊናን የሰጠን አምላክ ኅሊናችንን ጥለን በስሜት ብቻ እንድንጋልብ

አይፈቅድም። ጌታ ራሱ አንድ ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲ ብሏቸው ነበር፦ «. . . ገና አልተመለከታችሁምን? አላስተዋላችሁምን? ልባችሁስ ደንዝዞአልን? ዓይን ሳላችሁ አታዩምን? ጆሮስ ሳላችሁ አትሰሙምን? ትዝስ አይላችሁምን?» (ማር 8÷17-18)። ጸሎታችን እንደ ቤርያ ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን እየመረመርን ቃሉን በሙሉ ፈቃድ እንድንቀበል ነው (ሐሥ 17÷11)።

# እምነት በብሉይና በአዲስ ኪዳን
## ምዕራፍ አንድ

የክርስትና ሕይወት የእምነት ሕይወት ነው ሲባል እንሰማለን ። ግን እምነት ራሱ ምንድን ነው? በእምነት የምንኖረው እንዴት ነው? እምነትን የምናገኘውስ ከየት ነው? የሚሉ መሠረታዊ ጥያቄዎች መነሣታቸው አይቀርም።

እምነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አርእስት ነው። በመሆኑም ስለ እምነት ምንነት ማለትም እምነት ምን እንደ ሆነ ስንነጋገር፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ዋቤ ማድረግ ግድ ይሆናል። በዚህ ምዕራፍ ሥር ስለ እምነት በብልይና በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተሰጠውን ትርጕምና ትንተና እንመለከታለን።

## 1. እምነት በብሉይ ኪዳን

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ እምነት የተነገረን በቀጥታ ሳይሆን በምሳሌ ነው። በሌላ አነጋገር በብሉይ ኪዳን እምነት «ምን እንደ ሆነ» ማለትም ትርጕሙና ፍቺው አልተነገረንም። ልክ በአዲስ ኪዳን እንደምናነበው «እምነት» ማለት እንዲህና እንዲያ ነው ተብሎ አልተጻፈልንም (ዕብ 1÷11 ያነቧል)። ይልቁንም እምነት «ምን እንደሚመስል» ማለትም ጠባዩና ባሕርዩ ነው የተነገረን። እምነት የሚለውን የአማርኛ ቃል (እንዲሁም ቃሉ የወከለውን ፅንሰ ሐሳብ) ለመግለጽ በብሉይ ኪዳን የገባው የዕብራይስጡ ቃል እንደ ላስቲክ የመሳብ ባሕርይ አለው። እኛ «እምነት» የምንለውን ቃል ለመግለጽ የዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀመው «አማን» (በግእዙም ያው «አማን» ነው) የሚለውን ሥርወ ቃል ነው።

ይህ ሥርወ ቃል ከሦስት በላይ የሚሆኑ ፅንሰ ሐሳቦችን ይዞአል። ለጊዜው በሦስቱ ላይ ብቻ እናተኩራለን።

አንደኛው ጽኑ ወይም ጥብቅ የሚለውን ፅንሰ ሐሳብ የሚገልጽ ነው። በሌላ አነጋገር አለመናወጥን፣ አለመበገርን፣ አለመፈታትን የሚያሳይ ቃል ነው። በዚህ አገባቡ በጫንቃ ላይ ተደላድሎ መቀመጥን (ኢሳ 60÷4)፣ እንደ ችንካር መተከልን (ኢሳ 22÷23)፣ ጽኑ ስፍራ መያዝንና (1ሳሙ 2÷35፤ 1ነገ 11÷38) ታምኖ መጽናትን (ኢሳ 7÷9) ይገልጻል። በብሉይ ኪዳን ቃሉ የእግዚአብሔርን «ጽኑነት» ይኸውም እንደ ቃሉ የሚገኝ አምላክ መሆኑን ለመግለጽ የገባበት ጊዜም አለ (ኢሳ 49÷7፤ ኤር 42÷5)። በዘዳግም 7÷9 ላይ እንዲህ የሚል ቃል ተጽፎ እናገኛለን፦ «. . . አምላክህ እግዚአብሔር. . . የታመነ አምላክ እንደ ሆነ ዕወቅ»። ይህ የሚያስረዳን እግዚአብሔር አባያ (ዋሾ) እንዳልሆነ ይልቁንም በነገር ሁሉ እሙን መሆኑን ነው። እርሱ የተናገረውን ቃል አጥፎ ወይም የገባውን ኪዳን ሽሮ አያውቅም። በተናገረው ቃል ታምኖ፣ በገባውም

ኪዳን ጸንቶ የሚኖር ነው። ደግሞም በእርሱ የታመኑትን፣ ሁለንተናቸውን በእርሱ ላይ የጣሉትን፣ ወደ እርሱም የሸሹትን አሳፍሮ አያውቅም (መዝ 31÷5-6)።

ሁለተኛው እሙን ወይም ታማኝ የሚለውን ፅንሰ ሐሳብ የሚገልጽ ነው። ሰው የሚታመነው ጽኑና ጥብቅ በሆነ ነገር ነው። ድጥ በሆነና አንሸራቶ በሚፈጠፍጥ ለመታመን የሚሞክር ማን ነው? እግዚአብሔር ታሪክ አለው። ከጥንት ጀምሮ የሚታወቅበት ዝናም አለው። ታሪኩ እሙንነቱ ነው። ዝናውም ታማኝነቱ ነው። ርዳታም ሆነ ምሕረት (ይቅርታ) ፈልገው ወደ እርሱ የመጡትን አሳፍሮ አያውቅም (መዝ 91÷2)። አብርሃም በእግዚአብሔር «ያመነው» (ዘፍ 15÷6)፣ ዘሮቹም በእግዚአብሔር «እንዲያምኑ» (ዘፀ 4÷5፡31) የታዘዙት መታመን የሚችል አምላክ በመኖሩ ነው። እግዚአብሔር ታማኝነቱን በተለያዩ ጊዜዎች አሳይቶአል።

በሚታመነውነና ሊታመን በሚችለው ማመን ተገቢ ሆኖ ሳለ፣ በእርሱ አለመታመንና አለመጽናት በመደበኛው አነጋገር በሕይወት አለመኖር ነው።

እግዚአብሔር ሕዝቡን «ባታምኑ አትጸኑም» (ኢሳ 7÷9) በማለት እቅጩን የነገራቸው ከእርሱ በቀር ሌላ ረዳት እንደሌላቸው ለመግለጽ ነው። ስለዚህ ማመን መጽናት ነው፤ በሕይወትም መኖር ነው። ባንጻሩም አለማመን መጥፋት ነው፤ የእሳት ራት መሆን ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የምናምነው የምናውቀውን እንደ ሆነ በትንቢተ ኢሳይያስ ላይ ተጽፎልናል፡- «ታውቁና ታምኑብኝ ዘንድ፣ እኔም እንደ ሆንሁ ታስተውሉ ዘንድ እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ» (ኢሳ 43÷10)። በዚህ ምንባብ ላይ «ማወቅና ማመን» ተዛማጅ እንደ ሆኑ ተነግሮአል። ለማመን ማወቅ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ማንነቱን የማናውቀውን ልናምነው አንችልም። ታሪኩንና ዝናውንም ያልሰማነውን ልንከተለው አንችልም። ይሁን እንጂ ማወቅ በራሱ ምንም አይጠቅምም። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ሕዝቡን የጠ ራው በእርሱ እንዲያምኑ ብቻ ሳይሆን እርሱን አምላክና ጌታ ባሰኘውም ነገር ሁሉ እንዲያምኑም ነው።

ሦስተኛው እሙን ወይም እውነተኛ የሚለውን ፅንሰ ሐሳብ የሚገልጽ ነው። በእግዚአብሔር የምንታመነው፣ አንዳች ሳንሠጋ በእርሱ ላይ የምንቆመው፣ ምን አለብኝ ብለን በእርሱ ላይ የምንደገፈው እውነተኛ ስለ ሆነ ነው። እሙን ማለትም እውነተኛ በመሆኑ የተናገራቸውን ነገሮች ሁሉ ምንም ሳንጠራጠር እንቀበላለን። ምክንያቱም እርሱ የታመነ ነው። ንጉሥ ዳዊት በጸሎቱ እንዲህ ህሎ እንደ መሰከረው «ጌታዬ እግዚአብሔር ሆይ!አሁንም አንተ አምላክ ነህ፤ ቃልህም እውነት ነው» (2ሳሙ 7÷28)። እግዚአብሔር እሙን ነው ሲባል እውነተኛ ነው ማለት ነው። ዳዊት በመዝሙሩ የእግዚአብሔርን እውነተኛነት የሚነግረን «የዙፋንህ መሠረት ጽድቅና ፍርድ ነው፤ ምሕረትና እውነት በፊትህ ይሄዳሉ»በማለት ነው (መዝ 89÷14-15)። መዝሙረኛው በብዙ ምንባቦች ላይ የእግዚአብሔርን እሙንነት ከእውነ ተኛነቱ ጋር አያይዞት እናገኛለን (መዝ 119÷43፡142፡151፡160)።

እምነት በብሉይ ኪዳን የተነገረው ትርጉሙ ሳይሆን ባሕሪው ነው የሚለው አባባል ምን ያህል እውነት እንደ ሆነ ከፍ ሲል የተወያየንባቸው ነጥቦች ያመለክቱናል። አሁን ደግሞ ከብሉይ ኪዳን ሳንወጣ አንድ ምሳሌ ወስደን ነገሩን እንመልከት።

በቅድሚያ የምንጠቅሰው አብርሃምን ይሆናል። በአብርሃም ሕይወት ውስጥ እምነት የተመሰለው «ወጥቶ በመሄድ» ነው። አብርሃም የሚሄድበትን ባያውቅም በእምነት ግን ይሄድ ነበር። እርግጥ ነው አብርሃም የሚሄደው የዕውር ድንብሩን አይደለም። የተሰጠውን ተስፋ ይዞ እንጂ። ተስፋውን ግን የያዘው በእምነት ነው። ተስፋን የሰጠው አምላክ ቃሉን እንደሚጠብቅ አምኖ ሂድ ወደተባለው አገር ወጥቶ ሄደ። እንግዲህ የአብርሃም እምነት ጽድቅ ሆኖ የተቈጠረለት ተስፋን የሰጠውን አምላክ በመታመኑ ነው። እግዚአብሔር ሊታመን የሚችል እውነተኛ አምላክ መሆኑን የአብርሃም «የእምነት ርምጃ» ያስረዳናል። በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ሊታመን የሚችል እውነተኛ አምላክ እንደ ሆነ ቈጥሮ እርሱን መታዘዝ በረከት እንዳለውም ያስተምረናል። መታዘዝ ሕይወትን ሙሉ ያደርጋል። አብርሃም ከአገሩ (ዕትብቱ ከተቀበረበት አገር) በእምነት ወጥቶ ሄደ፤ በማያውቀው ሕዝብ መኻከል ኖረ። የእምነት ርምጃ በመጀመሩና አምላኩንም ታምኖ በመኖሩ ግን አንዳች ያጣው ነገር የለም። በምድራዊውም ሆነ በሰማያዊ ነገሮች ተባረከ፤ዘሩም በዛ።

ከአብርሃም ታሪክ እንደምንረዳው እምነት በኑሮና በርምጃ የሚገለጥ ነው። አብርሃም ሁል ጊዜ የሚታመነው በእሙኑና በእውነተኛው አምላክ በያህዌ ነው። አብርሃም በታሪኩ ሁሉ አንድም ቀን በራሱ ታምኖ አያውቅም። የሚያየውም ሆነ ተስፋ የሚያደርገው በቃሉ ሁሉ ታማኝ የሆነውን ጌታ ነው። ሂድ ወደተባለው ስፍራ ሲሄድ (ማለትም ወደ ከነዓን)፣ አድርግ የተባለውን ነገር ሲያደርግ (ማለትም ልጁን ሲሠዋ)፣ እመን የተባለውን ነገር ሲያምን (ማለትም ዘሮቹ እንደ ምድር አሸዋ ሲበዙ) ሁሉንም ያደረገው በሚታመነው በመታመን ነው።

አብርሃም በማየት የተመላለሰበት ጊዜ የለም። እርግጥ ነው ዐይን አለው- የሚያይበት፤ ዐይኑ ግን ታማኙ እግዚአብሔር ነው። ዛሬንና ነገን የሚኖረው ጽኑውን አምላክ ይዞ ነው።

በብሉይ ኪዳን «እምነት» የሚለው ቃል ተተርጒሞና ተተንትኖ አናይም ብለናል። ይልቁንም ቃሉ በምሳሌ ሲነገርና ሲገለጽ ነው የምናየው። ቃሉ ብዙ ጊዜ ወክሎ የምናገኘው እሙንነትንና ጸናኢነትን ነው። በነገር ሁሉ ታማኝ ሆኖ መገኘትን ነው። በሌላ አነጋገር ማመንና ማድረግ ፍጹም የተዋደዱ (አንድ የሆኑ) ነገሮች ናቸው። ድርጊትን ከእምነት ወይም ደግሞ እምነትን ከድርጊት መለየት አይቻልም። ይህን አባባል እንደ ሐዋርያው ያዕቆብ አባባል በሥራ የማይገለጥና የማይታይ እምነት የሞተ እምነት ነው (ያዕ 2÷14-26)። እስቲ አሁን ደግሞ ከብሉይ ኪዳን አንድ ምንባብ ወስደን እንወያይ።

ኤር 29÷10-14፤ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፤ ሰባው ዓመት በባቢሎን በተፈጸመ ጊዜ እጐበኛችኋለሁ፤ ወደዚህም ስፍራ እመልሳችሁ ዘንድ መልካሚቱን ቃሌን እፈጽምላችኋለሁ። ለእናንተ የማስበትን አሳብ እኔ አውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም። እናንተም ትጠሩኛላችሁ ሄዳችሁም ወደ እኔ ትጸልያላችሁ እኔም እሰማችኋለሁ። እናንተ ትሹኛላችሁ፤ በፍጹም ልባችሁም ከሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ። ከእናንተም ዘንድ እገኛለሁ ይላል እግዚአብሔር፤ ምርኮአችሁንም እመልሳለሁ፤ ከአህዛብም ሁሉ ዘንድ እናንተንም ከሳደድሁበት ስፍራ

ሁሉ እሰበስባችኋለሁ ይላል እግዚአብሔር፤ እናንተንም ለምርኮ ወዳፈለስሁበት ስፍራ እመልሳ ችኋለሁ።

ይህ ምንባብ እምነት ሁለት ገጽታዎች እንዳሉት ያሳስበናል። አንደኛው ታማኞች (እሙናን) እግዚአብሔርን ተግተው ይፈልጋሉ። እግዚአብሔርን በትዕግሥት መጠበቅ ብቻ ሳይሆን እርሱንና ሓሳቡን ለማወቅ ናፍቀው ይፈልጉታል። ፍለጋቸውና ናፍቆታቸው ፍጹም ነው፤ የሚፈልጉትም ከልባቸው ነው ( "With all you heart")። ሁለተኛው ከሕዝቡ ታሪክ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። ሕዝቡ ያህዌን የተወ ዕለት

በያህዌም ይተዋል፤ ወደ ያህዌ የተመለሰ ዕለት ያህዌም ወደ ሕዝቡ ይመለሳል።

## 2. እምነት በአዲስ ኪዳን

ጌታችን አንድ ጊዜ እንዲህ ሲል ጠይቆ ነበር፦ «የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆንን?» (ሉቃ 18÷8)። ልብ እንበል! ጌታ ይህን ጥያቄ ያቀረበው «በራሳቸው ለሚታመኑ» ትውልዶች ነው ሉቃ (18÷9)። ወደ እሙኑ አምላክ ሳይሆን ወደ ገዛ ራሳቸው ለሚመለከቱ ሕዝቦች ነው። በቅድሚያ እምነት በአራቱ ወንጌላት ውስጥ ያለውን ትርጕምና ባሕርይ እንቃኝ።

«እምነት» የሚለው ቃል ሁል ጊዜ ግንኙነትን ገላጭ ነው። ሰዎች ከሰዎች ጋር ወይም ሰዎች ከፈጣሪ ጋር ያላቸው ግንኙነት በእምነት ሊገለጥ ይችላል። እምነት የሚለው ቃል በስምና (በግሪኩ ፒስቲስ) በግሥ (በግሪኩ ፒስቴኦ) መልክ በወንጌላቱ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል። የዮሐንስ ወንጌል በተለይ በግሥ መልክ (ለምሳሌ ለሚያምኑ 1÷12፤ የሚያምን 3÷16፤ ብታምኚስ 11÷40፤ ታምኑ ዘንድ 20÷30)ቃሉን 100 ጊዜ ያህል ተጠቅሞበታል። ባንጻሩም ቃሉ በስም መልክ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ አንድም ጊዜ አልተጠቀሰም።

የመሲሑ ወደዚህ ምድር መምጣት ሁለት ወሳኝ ነገሮችን እንደናደርግ ይጋብዘናል - ንስሓ ገብተን እንድናምን (ማር 1÷15)። በአራቱ ወንጌሎች ውስጥ እምነት ሁል ጊዜ ተያይዞ የምናገኘው ከክርስቶስ ማንነት ማለትም ከሚሠራውና ከሚያደርገው ነገር ጋር ነው። ከክርስቶስ አንዳች ነገር ለመቀበል የሚፈልጉ ሰዎች የክርስቶስን ማንነት ተረድተው ወደ እርሱ በእምነት መምጣት አለባቸው (ማቴ 9÷22፤ ማር 9÷23)። ጌታ ከሰዎች የሚፈልገው ትልቅ እምነት አይደለም። የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ያላቸው ሰዎች በፊቱ ሞገስ ያገኛሉ (ማቴ 17÷20)። እንዲያውም ሰዎች በክርስቶስ የመጣውን በረከተ ድኅነት

መካፈል የሚችሉት በእርሱ ሲያምኑ ብቻ ነው (ዮሐ 20÷31)። የቀድሞ ታሪክም ሆነ ዘር በረከተ ድኅነቱን ለመካፈል ምክንያት አይሆኑም (ማቴ 15÷21-28 ይመለከቷል)። ጠላታችን ዲያብሎስ ሰዎች «አምነው እንዳይድኑ. . . ቃሉን ከልባቸው ይወስዳል» (ሉቃ 8÷12)። እውነተኛ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ተለይተው የሚታወቁት በእምነታቸው ነው። (ሉቃ 1÷45)። ለእግዚአብሔር መገለጥ ትክክለኛው ምላሽ እምነት ነው (ዮሐ 3÷16፤17÷3 )። እግዚአብሔር ልናምነው የሚገባውን ነገር ሊገባን በሚችል መንገድ ገልጦልናል (ዮሐ 1÷14)። ታዲያ ምላሻችን ምን መሆን አለበት? «እግዚአብሔር በላከው ማመን» (ዮሐ 6÷29)።

በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ እምነት/ማመን ሁል ጊዜ ታያይዞ የምናገኘው ከደኅንነት ጋር ነው። በመስቀሉና በትንሣኤው የሚያምኑ ሁሉ ደኅንነትን ያገኛሉ (1ቆሮ 15÷3-4፡11)። በሌላ በኩል ደግሞ እምነት የእግዚአብሔር ስጦታና የመንፈስ ፍሬ ተደርጎ የቀረበበትም ጊዜ አለ (ኤፌ 2÷8-9፤ ገላ 5÷22)። በጳውሎስ እምነት ሰዎች የሚጸድቁት በእምነት ነው (ሮሜ 5÷1) ። በገላትያ መልእክቱ ላይ «ነገር ግን ሰው የሚጸድቀው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንጂ የሙሴን ሕግ በመፈጸም እንዳልሆነ እናውቃለን፤ እኛም ሕግን በመፈጸም ሳይሆን በክርስቶስ በማመን እንድንጸድቅ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነናል» (2÷16) በማለት ለመመካት ብንፈልግ በእግዚአብሔር ብቻ እንድንመካ ይመክረናል። በጳውሎስ እምነት «ማመን ማረፍ» ነው። ማለትም ወደ እኛ ማየትን ትተን ወደ እግዚአብሔር ማየት ነው። እምነት «ከእኔ የሆነ የለም» ይልቁንም «ሁሉ የሆነው በአንተ ነው» የምንልበት ነው። ከእግዚአብሔር የሆነውን ነገር የምንቀበለው በእምነት ከሆነ፣ እኔነት ስፍራ አይኖረውም።

ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት በሙሉ በእምነት ላይ እንደተመሠረተ በግልጽ የነገረን የዕብራውያን መልእክት ጸሓፊ ነው። ጸሓፊው ወደ ኋላ መለስ ብሎ በምዕራፍ 11 ላይ ስለ እምነት አርበኞች ታላላቅ ነገሮችን ያወጋናል። ጸሐፊው በተለይ ሊያወጋን የፈለገው እምነት ከማየት ጋር ምንም ዝምድና የሌለው መሆኑን ነው።

ምክንያቱም «ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም» (ቁ 6)። በሌላ አነጋገር እነዚህ የእምነት አርኞች የተመላለሱት በማየት ሳይሆን በማመን ነው።

በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ውስጥ እምነት ትልቅ እሳቤ ነው። እምነት ማለት በራስ መታመንን መካድ ነው። እምነት ማለት ራስን ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር እጅ ላይ መጣል ማለት ነው። እምነት ማለት እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት የገባልንን ቃል ታግሦ መጠበቅ ማለት ነው። እምነት በእግዚአብሔር ላይ ፍጹም መታመንና እርሱን ፍጹም መታዘዝ ነው።

# የሚሠራ እምነት እንዴት ያለ እምነት ነው?
## ምዕራፍ ሁለት

በእምነት መኖር ማለት ምን ማለት ነው? በዚህ ዘመን የምንኖር ክርስቲያኖች፣ በድሮ ዘመን የነበሩ አማኞች የኖሩትን የእምነት ሕይወት መኖር እንችላለን?

መልሱ «አዎን» ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ እኛ ወዳለንበት የመጣው፣ በእኛ ምትክ የሞተው፣ እኛንም ከሞት እስራት ነጻ ለማውጣት ሲል ከሙታን የተነሣው እንዲሁም ልቡናችንን ለማንቃት የሚችለውን ቅዱስ መንፈስ የሰጠን፣ እርሱ የሚፈልገውን ዐይነት የእምነት ሕይወት እንድንኖር ነው። ይሁንና የእምነት ሕይወት ዋጋ የሚያስከፍል ሕይወት ነው። በየዕለቱ ለራስ፣ ለዚህ ዓለምና ለምኞቱ መሞትን ይጠይቃል።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ «እምነት» የሚለው ቃል በሁለት መንገድ ገብቶ እናገኛለን፡፡ በአንድ በኩል ተግባርን ወይም «ድርጊትን» ለመግለጽ ገብቶአል፡፡ ለማመን አንድ የምናምነው ነገር መኖር አለበት፡፡

ለምሳሌ በማቴዎስ ወንጌል 15÷21-28 ላይ ታሪኳ ተጽፎ የምናገኘው የከነዓናዊቷ ሴት ኢየሱስ ልጇን እንዲፈውስላት በእምነት ጠየቀች፡፡ ይህች ሴት የታመነችው በኢየሱስ ነው፡፡ ኢየሱስ ልጇን ሊፈውስላት እንደሚችል ርግጠኛ ነበረች፡፡ ስለዚህም ወደ ኢየሱስ መጥታ «እርዳኝ» አለችው፡፡ ኢየሱስም፡— «አንቺ ሴት እምነትሽ ታላቅ ነው፤ እንደ ወደድሽ ይሁንልሽ አላት» (ቊ 28)፡፡ ወዲያውም ልጇ ዳነ፡፡ ከከነዓናዊቷ ሴት ታሪክ እንደምንረዳው «እምነት» በተግባርና በድርጊት ተገልጾ የሚገኝ መሆኑን ነው፡፡ የሴቲቱ እምነት በተጨባጭ የሚታይ እምነት ነው፤ በኢየሱስ ታመነች፡፡ ማለትም ችግሯን ይዛ ወደ ኢየሱስ ሄደች፤ እርሷም ልትፈታው ያልቻለችውን ነገር ለኢየሱስ ሰጠች፡፡ ወደ እርሱ ስትሄድ ግን ኢየሱስ ሁሉን ለማድረግ ሥልጣን እንዳለው በማመን ወይም በማወቅ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ቃሉ «በስም» መልክ ገብቶ እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ 6÷7 ላይ እንደዚህ ተጽፎ እንደምናነበው፡- «የእግዚአብሔርም ቃል እየሰፋ ሄደ፤. . . ብዙ ሰዎች ለሃይማኖት የታዘዙ ሆኑ»፡፡ በዚህ ስፍራ «ለሃይማኖት» (በግሪኩ ፒስቲስ) የሚለው ቃል «ለእምነት» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፡፡ ቃሉ የገባው በስም መልክ ነው፡፡ ባንጻሩም ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ሲያሳስበው፡- «በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች . . . የተሰጠውን የአጋንንት ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ» (1ጢሞ 4÷1) ይለዋል፡፡ በዚህም ስፍራ «ሃይማኖትን» (በግሪኩ ፒስቲስ) የሚለው ቃል «እምነትን» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፡፡ ቃሉም የገባው በስም መልክ ነው (ከ2ቆሮ 13÷5 ጋር ያነጻጽሯል)፡፡

ሰዎች ስለ እግዚአብሔር የተነገራቸው ነገር እውነት መሆኑን አምነው በሙሉ ልብ ሲቀበሉ፣ አሁን ቃሉ የገባው በስም መልክ ነው እንላለን፡፡ የአንድን ነገር እውነተኛነትና ርግጠኝነት አምኖ መቀበል እምነት ነው፡፡ እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንደሚሰማ፣ ልመናችንን እንደሚያደምጥ፣ ከጠላቶቻችንም እንደሚታደገን ታምነን ሁለንተናችን በእርሱ ላይ ስንጥል አሁን ቃሉ የገባው በግሥ መልክ ነው እንላለን፡፡

በአንድ ነገር ላይ ራስን መጣልና መደገፍ መታመን ነው፡፡ ደግሞም እግዚአብሔርን በመታዘዝና በፊቱም በታማኝነት ስንኖር አሁን ቃሉ የገባው በቅጽል መልክ ነው እንላለን፡፡ ለአንድ ነገር ያለን መሰጠትና ታማኝነት ነው፡፡ ይህ የሚያሳየን እምነት በባሕርይው የሕያውነት ጠባይ እንዳለው ነው፡፡ የሚሠራ ማለትም ሕያው የሆነ እምነት በተግባር የሚታይ ነው፡፡ እንዲህ ዐይነቱ ሕያውና የሚሠራ እምነት ምን እንደሚመስል ለማየት መሄድ የሚኖርብን ወደ ዕብራውያን መልእክት ነው፡፡ በዚህ መልእክት በምዕራፍ 11 ላይ ብቻ ቃሉ 24 ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ ጸሓፊው በምዕራፉ መግቢያ ላይ የእምነትን ትርጕም ከነገረን በኋላ «የቀድሞ ሰዎች የተመሰገኑት በእምነት ምክንያት ነው» (1÷2፤ አዲሱ ትርጕም) ይለናል፡፡ ትንሽ ወረድ ብሎ ደግሞ፡- «ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሰው እግዚአብሔር መኖሩንና እርሱን ለሚፈልጉት ሰዎችም ሽልማት የሚሰጥ መሆኑን ማመን አለበት» (ቊ 6) በማለት ሁነኛ ነገር ይነግረናል፡፡ ከአቤል ጀምሮ የነበሩ

የእግዚአብሔር ሰዎችን የሚያመሳስላቸው አንድ ነገር ቢኖር «የእምነት ሰው» መሆናቸው ነው። እነዚህ ሰዎች ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን ተረድተዋል። አንደኛው «ጻድቅ የሚኖረው በእምነት» ነው። እግዚአ ብሔር ደስ የሚሰኘውም ሆነ የሚከብረው ከእምነት በሆነ ሕይወት ነው። የነገራቸውን ቃል ብቻ በመታዘዝ እግዚአብሔር ወደሚልካቸው ስፍራ የሚሄዱ፣ የገባውን ኪዳን ብቻ በመታመን ዘወትር በተስፋ የሚጠባበቁ፣ የሰጣቸውን መገለጥ በመጨበጥ በፊቱ ሁለንተናቸውን የሚያኖሩ፣ እነርሱ በእምነት የሚኖሩ ሰዎች ናቸው። ለእግዚአብሔር የምነሳየውም ሆነ በፊቱ የምንደረድረው አንዳች ጽድቅ የለንም። ነገር ግን ማንነቱን በማወቅ የምንኖረው ሕይወት የእምነት ሕይወት ነው።ሁለተኛው እግዚአብሔርን ተግተው የሚፈልጉ ሰዎች ዋጋቸውን (ሽልማታቸውን) ያገኛሉ። እግዚአብሔር ደንታ ቢስ አምላክ አይደለም። እግዚአብሔር ባዶ እጃቸውን ወደ እርሱ መጥተው በእርሱ የሚታመኑትን እንደማይገፋቸው ሁሉ፣ ስለ ስሙም ብለው እርሱን ደስ ለማሰኘት የሚደክሙትን ችላ አይልም፤ ይልቁንም ይመልስላቸዋል፤ ይበልጥ ይገኝላቸዋል፤ ትክ ብሎ ይመለከታቸዋል።

ነገሩን ይበልጥ ለማብራራት ሌላ አብነት እንጥቀስ። ባለ ታሪኩ አንድ ሮማዊ የመቶ አለቃ ነው (ማቴ 5÷5-9)። የመቶ አለቃው ወደ ኢየሱስ ቀርቦ አገልጋዬ ታሟልና ፈውስልኝ አለው። ኢየሱስም መልካም፣ መጥቼ እፈውሰዋለሁ አለው። የመቶ አለቃው ራሱንና ቤቱን ሲመለከት ኢየሱስ በእርሱ ቤት ለመግባት የሚገባው ሰው አይደለም። ስለዚህም «ቃል ብቻ ተናገር» አገልጋዬም ይፈወሳል አለው። በሉቃስ 7÷1-10 ላይ በምናገኘው ተጓዳኝ ታሪክ ላይ የመቶ አለቃው ራሱ ወደ ኢየሱስ ለመምጣት የሚገባው ሰው እንዳልሆነና ከዚህም የተነሣ ሌሎች ሰዎችን እንደ ላከ እናነባለን። ጌታ ኢየሱስ በሰዎች ዘንድ ከቁብ የሚቈጠር ነገር አግኝቶ ሲደነቅ አናየውም። ጌታን ሁል ጊዜ የሚያስደንቀው በሰዎች ዘንድ የተለየ እምነት ማየቱ ነው። ኢየሱስ በመገረምና በመደነቅ በዙሪያው ላሉት ሰዎች እንዲህ አላቸው:- «እውነት እላችኋለሁ በእስራኤል እንኳ [እግዚአብሔርን ዐውቀዋለሁ በምትለው እንኳ] እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት [ፒስቲን ] አላገኘሁም» (ቊ 10)።

ይህ የመቶ አለቃ እምነትን በተመለከተ ሁለት ነገሮችን ተረድቶአል። አንደኛው የሥልጣንን ባሕርይ ተረድቶአል። እርሱ ራሱ የጦር መኰንን በመሆኑ ከበላዩ እርሱ የሚታዘዛቸው፣ ከበታቹ ደግሞ እርሱ የሚያዛቸው ሰዎች አሉ። ከበላዩ ያሉት እርሱን ሲያዙት በእሺታ ይታዘዛቸዋል። ከበታቹ ያሉትን እርሱ ሲያዛቸው በእሺታ ይታዘዙታል። ሥልጣን በባሕርይው ከዋኝ (በድርጊት የተሞላ) ነው። ሁለተኛው የኢየሱስን ሥልጣን ተረድቷል። እርሱ ከበታቹ ያሉትን ለማዘዝ ሥልጣን እንዳለው ሁሉ ኢየሱስም ደዌን ሁሉ ለመፈወስ ሥልጣን እንዳለው በእምነት ተገንዝቦአል። እምነትም በባሕርይው ከዋኝ ነው። አንድን ነገር መከወን የሚችል ደግሞ ሕያው የሆነ ነገር ነው። እንግዲህ እምነትን ሕያውና የሚሠራ የሚያሰኘው ይህ ባሕርይው ነው።

## እምነት እንዴት ሊያድግ ይችላል?

እምነት በባሕሪው የሚሠራ ማለትም ሕያው ነው ብለናል። መልካም! ታዲያ እምነት ሊያድግ ይችላልን? እምነት የሚያድግ ከሆነ

ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል:: የእምነታችንንስ ዕድገት በሚገባ መለካት የምንችለው እንዴት ነው?

እምነት የሕያውነት ባሕርይ ስላለው ያድጋል:: ባንጻሩም እንደሚገባ ካልተያዘ ማለትም ካልተመገበ ይቀጭጫል:: አንዳንድ ሰዎች የእምነታቸውን ዕድገት የሚለኩት ጌታ ቤት በቆዩበት ዘመን ነው:: በጌታ ቤት ብዙ ዘመን ያሳለፉ ሰዎች በእምነታቸው እንዳደጉ ተደርገው ይቈጠራሉ:: ይህ ግን ትክክለኛ መለኪያ አይደለም:: በጌታ ቤት ምንም ያህል ብዙ ዘመን ብናሳልፍ፣ ለእምነታችን ዕድገት ዋስትና ሊሆን አይችልም:: እርግጥ ነው እምነት ለማደግ ጊዜ ይፈልጋል:: ይሁን እንጂ ዘመን ስለ ተቈጠረ ብቻ እምነት አያድግም:: እስቲ ከዚህ በታች ያለውን ግራፍ እናጢን:—




በሥዕሉ ላይ እንደምናየው የእምነት ዕድገት የተወከለው በአምዳዊው ዘንግ ሲሆን በጌታ ቤት የቆየንበት ዘመን ደግሞ በአግድማዊው ዘንግ ተወክሏል:: በዚህ አስተሳሰብ መሠረት በጌታ ቤት ባሳለፍነው ዕድሜ መጠን እምነታችን ያድጋል:: ይህ ግን ትክክለኛ አስተሳሰብ አይደለም:: ምክንያቱም እምነት «የዘመን» ወይም «የዕድሜ» ውጤት አይደለም:: እምነታችን የሚያድገው በሂደት ነው:: ከእያንዳንዱ ገጠመኝ የምንማራቸው ነገሮች ናቸው እምታችንን ለዕድገት የሚያበቁት::

ከድካማችን፣ ከመከራችን፣ ከውድቀታችን፣ ወዘተ በምንማረው ልክ ነው እምነታችን የሚያድገው:: የአካል ዕድገትና የእምነት ዕድገት ተመሳሳይ ነገር አላቸው:: አካል/ሰውነት የሚፋፋውና የሚጠነክረው ተመጣጣኝ ምግብ ሲያገኝ ነው:: እምነትም ልክ እንደዚሁ ነው:: በመንፈሳዊ ሕይወታችን ላይ የሚያደርሱት ማናቸውም ነገሮች በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ እምነታችንን ያሳድጉታል:: ገጠመኞቻችን እንደ ተመጣጣኝ ምግብ ናቸው:: በአግባቡ ካስተናገድናቸው እምነታችንን ያሳድጉታል:: ከዚህ ውጭ እምነት የሚያድግበት ሌላ መንገድ የለም:: እስቲ አሁን ደግሞ ቀጥሎ የተመለከተውን ግራፍ እናጢን:—




በዚህ ሥዕል ላይ እንደምናየው ደግሞ የእምነት ዕድገት የተወከለው በአምዳዊው ዘንግ ሲሆን በጊዜ ወይም በሂደት ውስጥ እየተመገበ የሚያድገው እምነት ደግሞ በአግድማዊው ዘንግ ተወክሏል:: በአግድማዊው ዘንግ የተወከለውና እየተመገበ የሚያድገው እምነት ብዙ ገጠመኞች እንዳሉት በሥልሉ ላይ ተመልክቷል:: ገጠመኞች እንደ ምግብ ሊቈጠሩ እንደሚችሉ ቀደም ሲል አመልክተናል:: በኑሮ ውስጥ ከሚገጥሙን ውጣ ውረዶች በተማርን ቊጥር እምነታችን ያድጋል:: «እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራ» (ኤፌ 1÷11) አምላክ ከምናልፍባቸው ጎዳናዎች እያስተማረን ያሳድገናል::

ጳውሎስ በሮሜ 1÷17 ላይ «ጻድቅ በእምነት ይኖራል የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና» ሲል ይህን መለኮታዊ አሠራር እያሰበ ይመስለናል:: እንደ ሐዋርያው አባባል የክርስትና ሕይወት «ከእምነት ወደ እምነት» ነው:: ከአንዱ ገጠመኝ እየተማርን ወደ ሌላው ገጠመኝ እናልፋለን:: በዚህ ዐይነት እምነታችን እየጠነከረ ይሄዳል:: እምነት የጽናት ውጤት ነውና::

እዚህም ላይ አብርሃምን እንደ ምሳሌ ብንጠቅስ ትምህርት እናገኛለን:: አብርሃም ተወልዶ ያደገበትን ቀዬ ጥሎ እንዲወጣ ሲታዘዝ አንድ ገጠመኝ ነው:: ትእዛዙን በእምነት ተቀብሎ ወጣ፣ ሄደ (ዘፍ 12÷1-2):: በሌላ ጊዜ እግዚአብሔር ተገልጦ «እጅግም አበዛሃለሁ» (ማለትም ልጅ እሰጥሃለሁ) ሲለው ነገሩን በእምነት ተቀብሎ ጸና (ዘፍ 17÷2):: ይህም ሌላ ገጠመኝ ነው:: በተስፋ ጸንቶ ቆመ:: ልጅ ካገኘ በኋላ «የምትወደው አንድ ልጅህን . . . መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው» (ዘፍ 22÷2) ሲባል «እግዚአብሔር ከሙታን ሊያስነሣው እንዲቻለው አስቦአልና [በእምነት ተረድቶአልና] [ዕብ 11÷19] ወዲያው ታዘዘ:: ይህም ሌላው ገጠመኝ ነው:: የአብርሃም እምነት ሊያድግ የሚችለው በዚህ ዐይነት መንገድ እንደ ነበር እግዚአብሔር ያውቃል:: ይህም ያዕቆብ በመልእክቱ ላይ እንዲህ ሲል እንደ ተናገረው ነው:- «ወንድሞቼ ሆይ፣ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥት እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቊጠሩት ትዕግሥትም ምንም የሚጐድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም» (1÷3-4):: እግዚአብሔርን ታምነን እርሱ በሚያሳልፈን ጐዳና ከሄድን አሁን በትክክለኛው የዕድገት መንገድ ላይ ነን:: ዕድገት ቀመር ካለው ቀመሩ ይህ ብቻ ነው::

የክርስትና ሕይወት የመጻተኛነት ሕይወት ነው። ምክንያቱም ቤታችንም ሆነ አገራችን በዚህ ምድር አይደለም። በዚህ ምድር እንግዶችና መጻተኞች ነን። ማለትም ለዚህ ዓለም ባይተዋሮች ነን።

የክርስትና ሕይወት የእምነት ሕይወት ነው። ይህ ሕይወት እግዚአብሔርን ታግሦ በመጠበቅ የምንኖረው ሕይወት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ «በትዕግሥት መኖር» አንዱ የሕይወት ዘይቤአችን እንዲሆን መክሮናል (ሮሜ 8÷24-25)። ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችን አድርገን በተቀበልን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር በተለየ ኅብረት እንድንመላለስ ተጠ ርተናል ፣ ከእርሱ ጋር በእርግጥ አንድ እንደሆንን ወይም የእርሱ ደቀ መዝሙርት መሆናችን የሚታወቀው በመከራውና በሥቃዩ ዘመን ታማኝነታችንን ስንገልጽ ነው። እንግዲህ በዚህ ምድር በሕይወት እስካለን ድረስ የምንኖረው በእምነት ነው። ክርስቲያን በዚህ ምድር የሚኖረው በመታመን ነው። እውነቱ እንዲህ ከሆነ እምነት በማየት የሚተካው በመጻኢው ዘመን ሊሆን ነው። እስከዚያው ድረስ በእምነት እንኖራለን፤ በመታመን እንመላለሳለን፤ መጻኢውን ተስፋችንን በመደገፍ እንገሠግሣለን።

በዚህ ምድር እንድንኖር የተጠራነው በእምነት እንጂ በማየት አይደለም። ይህን መሠረታዊ እሳቤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አብነት ጠቅሶ ማስረዳት የሚያስፈልግ ይመስለናል። አሁን ለምንለው ነገር ትልቁ ምሳሌያችን ክርስቶስ ኢየሱስ በመሆኑ፣ እርሱ ከተናገረው ነገር በመጀመር ወደ ሌላው እንዘልቃለን።

ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመኑ የነበሩትን «ምልክት» አሳዳጆችን ክፉኛ ገሥጿል። በቅርናሆም የሹምን ልጅ ከፈወሰ በኋላ «እናንተ እኮ ተአምራትና ድንቅ ነገር ካላያችሁ በቀር ምንም አታምኑም» በማለት ወቅሷል (ዮሐ 4÷48)። የትውልዱን ጠማማነት አስመልክቶ ሲናገር ደግሞ፡— «የዚህ ዘመን ሰዎች እንዴት ክፉዎች ናቸው፤ ምልክት ለማየት ይፈልጋሉ፤ ነገር ግን ከነቢዩ ከዮናስ ምልክት በቀር ሌላ ምልክት አይሰጣቸውም» ብሏል (ሉቃ 11÷29)። ሰዎች ከዕውርነታቸው የተነሣ እግዚአብሔር በመካከላቸው ሕያው በሆነ መንገድ ሲመላለስ ላያስተውሉት ይችላሉ (ሉቃ 17÷20-21)። በተለይ ደግሞ ዋናውን (ኢየሱስን) ትተው ተራውን (ድንቃ ድንቁን) የሚያሳድዱ ሰዎች ይህ ፍጹም ሊሰወርባቸው ይችላል።

ኢየሱስ የዮናስ ምልክት ሲል ከዐውደ ምንባቡ እንደምንረዳው ትንሣኤውን ነው። ሰዎች ይህን ምልክት ማስተዋል የሚችሉት በእምነት ብቻ ነው። ኢየሱስ አያሌ ምልክቶችንና ተአምሮችን አድርጓል (ማቴ 9÷30፤ 12÷16፤ ማር 3÷7-12)። ይህንን ያደረጋቸውን ነገሮች ከበሮ እየደለቁ፣ ጥሩንባ እየነፉ እንዲናገሩ አላደረገም። ይልቁንም ይህን ለማንም እንዳይናገሩ ነው ያስጠነቀቃቸው።

ሐዋርያው ጳውሎስም ይህን የጌታን ፈለግ ተከትሎ አስተምሯል (1ቆሮ 1÷22-23)። ንስሓ ገብተው በእምነት ለሚኖሩ ወንጌሉ «የእግዚአብሔር ኀይልና የእግዚአብሔር ጥበብ ነው» (1ቆሮ 1÷24)። እርግጥ ነው ከጳውሎስ መልእክቶች እንደምንረዳው ምልክቶችንና ተአምሮችን የምናየው በእምነት ዐይን ከሆነ የእምነትን ምስጢር ይገልጠ ልናል። ይሁንና ጳውሎስ ራሱ እንደተናገረው ምልክቶችና ተአምሮች ለእውነተኛ እምነት አያበቁም (2ቆሮ 12፡11-13)።ከክርስቶስ ግራና ቀኝ ከተሰቀሉት ሰዎች መካከል አንዱ ምልክት ጠይቆ ነበር (ሉቃ 23÷39)። ይህን ሰው ጌታ ሳይሆን ከጎኑ የተሰቀለው

ሌላው ሰው ገሥጸው (ሉቃ 23÷40)፡፡ ይኸኛው ሰው ምልክትን ሳይሻ በክርስቶስ አመነ፡፡ እጅግ መራር በሆነ ሥቃይ ውስጥ ሆኖ ሳለ በክርስቶስ ለማመን ቻለ - አይቶ ሳይሆን አምኖ ፡፡ ይህ ሰው ለዚህ ታላቅ እምነት የበቃው በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ እንደ ሆነ ምንም ጥርጥር የለውም

ደቀ መዝሙሩ ቶማስ ጌታ ኢየሱስ ከሞት እንደተሣ በተነገረው ጊዜ «ካለየሁ አላምንም» አለ፡፡ «ማየት ማመን ነው» የሚለው ብሂል የድኅረ ዘመናዩ ትውልድ መርሕ ብቻ ሳይሆን የጥንቱም ዓለም መርሕ ነበር፡፡ ቶማስ የኢየሱስን ጐንና እጁን ካለዳሰስሁ አላምንም አለ፡፡ ቶማስ በነበረበት ድንገት የተገለጠው ጌታ ጐኑንና እጁን እንዲዳስስ እንዲያይ ቶማስን ጋበዘው፡፡ ቶማስም ጮቤ እየረገጠ እንዲህ አለ:— «ጌታዬ አምላኬ» (ዮሐ 20÷28)፡፡ ጌታ ኢየሱስ የቶማስን ደካማነት አይቶ ከፍቅሩ

የተነሣ «አለማመኑን ቢረዳውም» የቶማስን መርሕ («ማየት ማመን ነው» የሚለውን) ግን ከቶ አላጸደቀም፡፡ ይልቁንም እንዲህ ሲል ተናገረ «ሳያዩ የሚያምኑ ብፀዓን ናቸው» (ዮሐ 20÷29) ፡፡ አባባሉ የቶማስን መርሕ የሚያወግዝ ነው፡፡

ክርስትና በማየት ለመመላለስ መመኘትን አያደፋፍርም፡፡ እንዲያውም በማየት ለመመላለስ መሞከር «አማኒነትን» ሳይሆን «ተጠራጣሪነትን» ነው የሚያሳየው፡፡ የተለየ ምልክት የተሰጣቸው ሰዎች የበለጠ ምልክት ሲፈልጉ እንጂ ወደ እምነት ሕይወት ሲገሠግሡ አልታዩም፡ ለዚህ አባባል ትልቅ ምሳሌ የሚሆነን ጌዴዎን ነው (መሳ 6÷14-40)፡፡ እምነትን የሚያጠነክረው እምነት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር እምነት የሚጠነክረውና የሚያድገው በእምነት ስንኖር እንጂ በማየት ስንኖር አይደለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በማየት ለመመላለስ መሞከር ትምክሕትን/ትዕቢትን ይጭራል፡፡

የእግዚአብሔርን ሐሳብ ለመረዳት ማመን እንጂ ማየት ብዙ አይጠቅምም (ማቴ 16÷17)፡፡ ምክንያቱም በመንፈሳዊው ዓለም በማየት መመላለስ መንፈሳዊ ሕይወትን ያመነምናል ደግሞም ያቀጭጫል እንጂ አያለመልምም (አያወፍርም)፡፡

እዚህ ላይ አንድ የእግዚአብሔር ሰው የተናገሩትን ጠቅሰን እናሳርግ፡፡ «ጸጋ እግዚአብሔር ለእኛ እንዲህ በማለት የተናገረበት ነው:- «ከቶ አልተዋችሁም»፡፡ እምነት እኛ ለእግዚአብሔር እንዲህ የምንልበት ነው:- «ከቶ አልተውህም»፡፡ እምነት ለእግዚአብሔር ጸጋ ምላሽ የምንሰጥበት ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትም ሆነ ጉዞ የምንጀምረው በእምነት ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከምናነባቸው ጥቅሶች ሁሉ በብዙዎች ዘንድ በቃል የሚታወቀው ጥቅስ ምላሽ/መልስ ይጠብቃል (ዮሐ 3÷16)፡፡ ይሁንና እምነት ደግሞ የምንወለድበት ወይም ዋስትና የምናገኝበት ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም በዚህ ምድር ስንኖር የሕይወታችንና የትግላችን ሁሉ መገለጫ እንጂ! ጌታ አንድ ጊዜ እንዲህ ብሎ ጠየቀ:-«የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆን» (ሉቃ 18÷8)፡፡ እውነተኛ እምነት ለተስፋ መቁረጥ አይዳርግም፡፡ ይልቁንም በትዕግሥት መኖርን ያስተምረናል፡፡ ጌታን መጠበቅን ያስተምረናል፡፡

በክርስትና ሕይወት ውስጥ እምነት ቁልፍ ስፍራ አለው፡፡ የእግዚአብሔርን በጎ ስጦታዎች ሁሉ የምንቀበለው በእምነት ነው፡፡ ያለ እምነት እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ሊኖር አይችልም፡፡ የእምነትን ጉዞ የጀመርነው በእምነት ነው፡፡ ጉዞውን የምንዘልቀው በእምነት ነው፡፡ ደግሞም ጉዞውን የምንጨርሰው በእምነት ነው፡፡

ክርስቲያናዊ ሕይወት ከእምነት ወደ እምነት ደግሞም ወደ እምነት ነው:: ማለትም በእምነት እንደ ጀመርን በእምነት እየኖርን በእምነት እንጨርሳለን::

# እምነትና ፈውስ
## ምዕራፍ ሦስት

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ «*እምነትና ፈውስ*» የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ተደርገው ሲነገሩ መስማት እየተለመደ መጥቶአል:: ሰዎች ፈውስን የሚያገኙት ከብረት የጠነከረ፣ ከውቅያኖስ የጠለቀ፣ ከሰማይ የመጠቀ እምነት ሲኖራቸው ብቻ ነው:: ባንጻሩም ሰዎች ከደዌአቸው የማይፈወሱት እምነተ ደካሞች ስለ ሆኑ ነው:: «*ያለተፈወስኸው እምነት ስለሌለህ ነው*» የተባሉ ሰዎች ቍጥራቸው ቀላል አይደለም:: ከዚህም የተነሣ ሰዎች ከደዌአቸው የሚፈወሱት እምነት ሲኖራቸው ብቻ ነው የሚል ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ቀመር የብዙ ሰዎችን መንፈሳዊ ሕይወት እየቀጠፈ ይገኛል:: በዚህ ክፍል በጥሞና ለመመርመር የምንሞክረው መጽሐፍ ቅዱስ በተለይም ወንጌላት እምነትን ከፈውስ ጋር ምን ያህል እንዳያያዙት ይሆናል::

ምንም እንኳ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ «*ሐኪም*» (ልክ «መምህር፣ ረቢ፣ መሲሕ» ተብሎ እንደተጠራው) የሚል መጠሪያ ተሰጥቶት ባናገኝም፣ አንድ ሐኪም የሚያከናውነውን ተግባር ሲሠራና ሕመምተኞችን ሲፈውስ እናያለን (ማር 2÷17፤ ሉቃ 5÷31):: ኢየሱስን ለመጀመሪያ ጊዜ «*ሐኪም*» ብሎ የጠራው የአንጾኪያው አግናጥዮስ (35-107 ዓ.ም) ነው:: ኢግናጥዮስ ሰማዕት ከመሆኑ በፊት ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን በጻፈው መልእክቱ ላይ «*አንድ ሐኪም ብቻ እንዳለና እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሆነ*» አመልክቶአል:: የእስክንድርያው ቀለሜንጦስ (150-215 ዓ.ም) በበኩሉ ኢየሱስን «*ሐኪም*» በማለት በብዙ ስፍራ ጠርቶታል:: እንደ ቀለሜንጦስ አባባል ኢየሱስ «*የሥጋና የነፍስ*» ሐኪም ነው:: በጥንት ክርስቲያናዊ ሥነ ጽሑፎች ላይ ኢየሱስ ሐኪም እንደ ሆነ ተነግሮአል:: ከሁሉ ይልቅ ግን ስለዚህ ጒዳይ በሰፊው የጻፈው አርጌንስ (ኦሪገን፤ 185-254 ዓ.ም) ነው:: አርጌንስ ኢየሱስን «*ታላቁ ሐኪም*» በማለት ጠርቶታል:: በመጨረሻም ኢየሱስ «*ሐኪም*» እንደ ሆነ ያመለከተው አውሳብዮስ (260-340ዓ.ም) ነው:: የአውሳብዮስ ኢየሱስ «*እጅግ ክቡር ሐኪም*» እንደ ሆነ አመልክቶአል:: አሁን ደግሞ ወደ ወንጌላቱ በመሄድ ኢየሱስ እንደ አንድ ሐኪም ለበሽተኞች ያደረገውን ሕክምና እንመልከት::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጌታ ኢየሱስ ሐኪም ተብሎ ባይጠራም እንደ ሐኪም ግን ሕሙማንን ፈውሶአል:: ከዚህ በመቀጠል የምንመለከተው የወንጌላቱ ጸሓፊዎች (ከዚህ በኋላ «*ወንጌላውያኑ*» በማለት እንጠቀማለን) 1) ስለ ፈውስ ምን ያህል ጊዜ እንደ ተናገሩ፣ 2) የፈውሱ መንሥኤ ማን እንደ ሆነ፣ 3) የፈውሱ ምክንያት ምን እንደ ሆነ፣ 4) የፈውሱ መንገድ ምን እንደ ነበር ይሆናል::

በተለምዶ «የድሮው ትርጒም» (የ1954ቱ ትርጒም) የሚባለውን ወስደን እያንዳንዱ ወንጌል ምን ያህል ቍጥሮች እንዳሉትና በእነዚህ ቍጥሮች ላይ ስለ ፈውስ ምን ያህል ጊዜ እንደ ተነገረ ብንቈጥር ከዚህ የሚከተለውን ውጤት እናገኛለን::

| ወንጌላት | የቁጥሮች ብዛት | ስለ ፈውስ የሚናገሩ | በመቶኛ ሲሰላ |
|---|---|---|---|

| | | ቁጥሮች | |
|---|---|---|---|
| ማቴዎስ | 1058 | 99 | 9% |
| ማርቆስ | 678 | 139 | 20% |
| ሉቃስ | 1149 | 134 | 12% |
| ዮሐንስ | 879 | 112 | 13% |

ይህን ስታትስቲካዊ ዘገባ ከኢየሱስ ተልእኮ ጋር ስናነጻጽረው ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣው የሰዎችን ሁለንተና (ነፍሳቸውንና ሥጋቸውን) ለመፈወስ እንደ ሆነ እናስተውላለን። እርግጥ ወንጌላውያኑ ኢየሱስን የሳሉልን እንደ ሐኪምና ተአምር ሠሪ አድርገው ሳይሆን፣ እንደ መምህርና እንደ ሰባኪ አድርገው ነው። በሌላ አነጋገር ስለ ፈዋሽነቱም ሆነ ስለ ተአምር ሠሪነቱ የነገሩን ከመምህርነቱ ጋር አያይዘው ነው። ሲያስተምርና ሲሰብክ ይፈውሳል፤ ተአምርም ይሠራል። ወንጌላውያኑ የኢየሱስን የፈውስ አገልግሎት የሚያመለክቱት በሁለት መንገድ ነው። በአንድ በኩል ኢየሱስ ሰዎችን የሚፈውሰው ኀይልና ሥልጣን ስላለው ነው። እንደ አብ ሁሉ እርሱም ጌታ ነው። የወደደውን ማድረግ ይችላል (ዮሐ 5÷17-22)። በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔር መንግሥት በደረሰበት ስፍራ የመንግሥቱ መገለጫ ባሕርያት ይከሠታሉ። የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችን ስትገኝ ብዙ አዳዲስ ነገሮች ይፈጸማሉ (ማቴ 4÷23-25)። መጻኢው የጽድቅ፣ የሰላም፣ የዕረፍት፣ በጥቅሉ የበረከት ዘመን መጥቶአልና።

በአራቱ ወንጌላት ውስጥ 48 የፈውስ ታሪኮች ተዘግበው እናገኛለን። ወንጌላቱን በጥንቃቄ ስናነብ ታዲያ ከ48ቱ የፈውስ ታሪኮች መካከል አንዳንዶቹ በሌላው ወንጌል ውስጥ በድጋሚ የተጠቀሱ ናቸው። አንዳንዶቹ ሁለት ጊዜ፣ ሌሎቹ ደግሞ ሦስት ጊዜ ተጠቅሰዋል። በድጋሚ የተጠቀሱትን ስናቀናንስ 26 የፈውስ ታሪኮችን እናገኛለን።

| ወንጌላት | አካላዊ ፈውስ የተቀበሉ | ከርኩሳን መና ፍስት የተፈቱ | ከሙታን የተነሡ | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|
| ማቴዎስ | 8 | 5 | 1 | 14 |
| ማርቆስ | 8 | 4 | 1 | 13 |
| ሉቃስ | 11 | 4 | 2 | 17 |
| ዮሐንስ | 3 | -- | 1 | 4 |
| ድምር | 30 | 13 | 5 | 48 |

እነዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ የፈውሱ መንሥኤ ማን ነው? ማለትም ለፈውሱ የመጀመሪያውን ርምጃ የተራመደው ወይም የመጀ መሪያውን ጥያቄ ያቀረበው ማን ነው? የሚለው ነው። ወንጌላውያኑ የኢየሱስን የፈውስ አገልግሎት በሚዘግቡበት ጊዜ የፈውሱ መንሥኤ ማን እንደ ሆነ ነግረውናል። ቀደም ሲል እንደገለጽነው በአራቱ ወንጌላት ውስጥ 26 የፈውስ ታሪኮች ተዘግበዋል። ከእነዚህ ውስጥ ከአራቱ በስተቀር የሌሎቹ መንሥኤ ማን እንደ ሆነ በትክክል ይታወቃል። ሁኔታውን ከዚህ በታች በተመለከተው ሠንጠረዥ ያጤ ኖአል፦

| ወንጌላት | በኢየሱስ ጠያቂነት | በደቀ መዛሙርቱ | በሕመምተኞቹ ጠያቂነት | በሕመምተኞቹ ዘመዶች | በሕመምተኞቹ ወዳጆች | በኢየሱስ ተቃዋሚዎች | ባልታወቁ ሰዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|

| | | ጠያቂነት | | ጠያቂነት | ወይም ጌቶች ጠያቀነት | ጠያቂነት | ጠያቂነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ማቴዎስ | -- | -- | 1 | -- | 1 | -- | 2 |
| ማርቆስ | -- | 1 | 4 | 3 | 1 | -- | 2 |
| ሉቃስ | 3 | -- | 2 | -- | -- | 2 | -- |
| ዮሐንስ | 1 | 1 | -- | 2 | -- | -- | -- |

**እርግጥ ነው እምነታቸውን በራሳቸው ላይ ሳይሆን በኢየሱስና በእግዚአብሔር ላይ ያደረጉ ሰዎች ፈውሳቸውን ተቀብለዋል። እምነትና ፈውስ ዝምድና ቢኖራቸውም ለመፈወስ (ፈውስ ለመቀበል) ግን እምነት ሁልጊዜ አስፈላጊ አይደለም።**

**በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተለይም በአራቱ ወንጌላውያን የተነገሩን የፈውስ ዘገባዎች ሁነኛ ዐላማ ወይም ምክንያት አላቸው። ኢየሱስም ሆነ ሐዋርያቱ ሰዎችን በፈወሱበት ጊዜ ይህን ያደረጉበት ምክንያት አላቸው። ጌታ ኢየሱስ ሁሉን ማድረግ ቢችልም የተጠየቀውን ሁሉ ግን አላደረገም። ለምሳሌ ፈውስ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ አልፈወሰም (ዮሐ 5÷3-5)፤ ምልክት እንዲያሳያቸው ለለመኑት ሁሉ ምልክት አላደረገም (ማቴ 12÷38-40)። ለምን ቢባል መልሱ ግልጽ ነው፤ ኢየሱስ ሰዎችን የሚፈውሰው (ምልክትን፣ ድንቅንና ተአምራትን የሚያደርገው) ሰማያዊ ዐላማውን ለመፈጸም ነው። እርግጥ ነው ሰዎች ከሥጋዊ እስራቶቻቸው መፈታት አለባቸው። ይህ ግን ወሳኝ አይደለም። ወሳኙ ከመንፈሳዊ እስራቶቻቸው መፈታት ነው። የጌታም ዐላማ ይህ ነበር። ከዚህ በመቀጠል የምንነጋገረው ወንጌላውያኑ የዘገቡልን የፈውስ ታሪኮች የተፈጸሙበትን ምክንያት ይሆናል። የወንጌላውያኑን ዘገባ በጥንቃቄ ስንመረምር ወደ አምስት የሚጠጉ ምክንያቶችን እናገኛለን:—**

**አንደኛው፣ ኢየሱስ ሰዎችን የፈወሰው ርኅራኄውን (አዘኔታውን) ለመግለጽ ነው። ጌታ ኢየሱስ የተራቡ ሰዎችን (ማቴ 15÷32፤ ማር 8÷2)፣ መሪ የሌላቸውን ሕዝቦች (ማቴ 9÷36፤ ማር 6÷34)፣ የተጨነቁ ሰዎችን (ሉቃ 7÷13)፣ በደዌ የተመቱ ሰዎችን (ማር 9÷22) ባየ ጊዜ ያዝንላቸው ነበር። የርኅራኄም እጁን ይዘረጋላቸው ነበር። ወንጌላውያኑ ኢየሱስ ከርኅራኄውና ከአዘኔታው የተነሣ የፈወሳቸው አራት ሰዎች እንዳሉ ዘግበውልናል።**

| ወንጌላት | ምንባብ | ፈውሳቸውን የተቀበሉ ሰዎች |
|---|---|---|
| ማቴዎስ | 20÷34<br>14÷14 | - ዐይነ ስውሩ በርጤሜዎስና<br>- ብዙ ሕዝብ |
| ማርቆስ | 1÷41 | - በለምጽ የተወረሰው ሰው |
| ሉቃስ | 7÷13 | - ልጇ የሞተባት የናይን ከተማ ሴት |
| ዮሐንስ | -- | -- |

**ሁለተኛው፣ ኢየሱስ ሰዎችን የፈወሰው ጩኸታቸውን ተመልክቶ ነው። «የዳዊት ልጅ ሆይ ማረን» በማለት ወደ እርሱ የጮኹትን ሰዎች ራርቶ ፈውሷል። እዚህ ላይ አንድ**

ነገር ልብ እንበል፡፡ ኢየሱስን «ማረን» በማለት የለመኑት ሰዎች በሙሉ «*ይህን ማድረግ እንድችል ተምናላችሁ?*» የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸዋል፡፡ ይህም ቀደም ሲል ለመጠቆም እንደሞከርነው የኢየሱስ ፈውስ ምክንያታዊ መሆኑን ያሳየናል፡፡ በሰዎች ፊት ድንቅ ነገሮችን የሚያደርገው የሰዎችን ሐሳብ ወደሚሻለውና ወደሚበጀው የእግዚአብሔር ሐሳብ ለመሳብ ነው፡፡ ሰዎች የእግዚአብሔርን ማዳን ማየት አለባቸውና፡፡

| ወንጌላት | ምንባብ | ፈውሳቸውን የተቀበሉ ሰዎች |
|---|---|---|
| ማቴዎስ | 9÷27<br>15÷22<br>17÷15<br>20÷30 | - ሁለቱ ዐይነ ሥውር ሰዎች<br>- ከነናዊቷ ሴት<br>- የሚጥል በሽታ የነበረባት ልጅ<br>- ዐይነ ስውሩ በርጤሜዎስ |
| ማርቆስ | --- | -- |
| ሉቃስ | 17÷13 | - ዐሥሩ ለምጻም ሰዎች |
| ዮሐንስ | --- | -- |

**ሦ**ስተኛው፣ ኢየሱስ ሰዎችን የፈወሰው እምነታቸውን ተመልክቶ ነው፡፡ ግን የትኛውን እምነት? የዚህ ዘመን መምህራን እንደሚሉን «*በውስጣቸው የታመቀውንና ሰዎቹ እንዲሆንላቸው የሚመኙትን ሁሉ የሚያከናውንላቸውን እምነት?*» *ወይስ በራሱ በጌታ ላይ ያላቸውን እምነት?*» ወንጌላውያኑ ከዘገቡልን 26 የፈውስ ታሪኮች መካከል እምነት ከፈውስ ጋር ተያይዞ የተጠቀሰው በ12ቱ ላይ ብቻ ነው፡፡ በእነዚህ ስፍራዎች ሁሉ ሄደን የሰዎቹን እምነት ብንመረምር ሁልጊዜ ሊምራቸው፣ ሊፈውሳቸውና ሊያድናቸው በሚችለው ጌታ ላይ ሲታመኑ ነው የምናያቸው፡፡ በሌላ አነጋገር እምነታቸው የሚያየው ወደ ውስጥ ማለትም ወደ ራሳቸው ሳይሆን ወደ ውጭ ማለትም ወደ ጌታ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እምነት ሁል ጊዜ የሚያመለክተው በሌላው ላይ መደገፍን ነው፡፡ በራስ መደገፍና በሌላ መደገፍ እንዲሁም ወደ ራስ መመልከትና ወደ ሌላ መመልከት ትልቅ ልዩነት አላቸው፡፡ ጌታም ያለው፡- «*ይህን ማድረግ እንደምችል ታምናላችሁ?*» ነው፡፡ መልሳችን «*አዎን*» ጌታ ሆይ! ካልሆነ፣ በራሳችን እየታመንንና ወደ ራሳችንም እየተመለከትን ነው፡፡

| ወንጌላት | ምንባብ | ፈውሳቸውን የተቀበሉ ሰዎች |
|---|---|---|
| ማቴዎስ | 8÷10<br>9÷28-29<br>15÷28 | - የመቶ አለቃው አገልጋይ<br>- ሁለቱ ዐይነ ስውር ልጆች<br>- ከነናዊቷ ሴት |
| ማርቆስ | 2÷5<br>5÷34<br>9÷24 | - ሽባው ሰው<br>- ደም ይፈሳት የነበረችው ሴት<br>- የሚጥል በሽታ የነበረባት ሰው |
| ሉቃስ | 17÷19<br>18÷42 | - የሰማርያዎቹ ለምጻም ሰዎች<br>- ዐይነ ስውሩ በርጤሜዎስ |
| ዮሐንስ | ------ | ----- |

**ሦ**ራተኛው፣ ኢየሱስ ሰዎችን የፈወሰው ክብሩን ለመግለጥ ነው። የእግዚአብሔርን ክብር መግለጥ ማለት ኀይሉንና ግርማውን መግለጥ ማለት ነው። ይህ የፈውስ ዐላማ ተጠቅሶ የሚናገኘው በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ሲሆን፣ ዐላማው የእግዚአብሔርን ክብር ብቻ ሳይሆን የኢየሱስንም ክብር መግለጥ ነው፤ ምክንያቱም የኢየሱስና የአብ ክብር አንድ ነው (ዮሐ 1÷14፤ 2÷11÷4፤ 17÷5፡22፡24)። በመሆኑም ኢየሱስ ተአምራትን ሲያደርግ የምናየው እርሱ ማን እንደ ሆነ ለማሳየትና ከእግዚአብሔርም የተላከ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው። አንዳንድ ጊዜ ማንነቱን በተመለከተ ውዝግብ ሲነሣ እርሱን ባያምኑ እንኳ ያደረጋቸውን ምልክቶች እንዲያስተውሉ ይለምናቸው ነበር (ዮሐ 5÷36፤ 10÷25፤ 14÷11፤15÷24)። ምክንያቱም እርሱ የመጣው ሰዎችን ለማስገረምና ለማስደነቅ አይደለም (ዮሐ 4÷48)። እርሱ የመጣው በሚያደርጋቸው ምልክቶች (በግሪክ ሴሚያ) አማካይነት ሰዎች የእርሱን ተልእኮ እንዲያስተውሉ ለማድረግ ነው። ይህ መሠረታዊ ዐላማ በሌሎቹም ወንጌላውያን በተለይም በሉቃስ ተመዝግቦ እናገኛለን። በሉቃስ ወንጌል ውስጥ በኢየሱስ የተፈወሱ ሰዎች እግዚአብሔርን ሲያከብሩና ሲያመሰግኑ እንመለከታለን (ሉቃ5÷25፤ 13÷13፤ 17÷15፤ 18÷43)።ፈውሱን ከተቀበሉት ሰዎች ምላሽ እንደምንረዳው፣ ሰዎቹ ተገርመውና ተደንቀው ብቻ አልቀሩም። ይልቁንም የእግዚአብሔርን ኀይልና ማዳን ማለትም በመካከላቸው «የሚሠራው አምላክ» እየተመላለሰ እንደ ሆነ ተገነዘቡ። መደነቅ አንድ ነገር ነው። ማመን ግን ሌላ ነገር ነው። የምልክቶቹም ዐላማ ሰዎቹን ማስደነቅ ሳይሆን ወደ እምነት ማድረስ ነው።

| ወንጌላት | ምንባብ | ፈውሳቸውን የተቀበሉ ሰዎች |
|---|---|---|
| ማቴዎስ | -- | --- |
| ማርቆስ | -- | --- |
| ሉቃስ | -- | --- |
| ዮሐንስ | 4÷54<br>9÷3<br>11÷4 | - የሹሙ ልጅ<br>- ዕውር ሆኖ የተወለደው ሰው<br>- አልዓዛር |

**አ**ምስተኛው፣ ኢየሱስ ሰዎችን የፈወሰው ትንቢትን ለመፈጸም ነው። ጌታ ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣው በእግዚአብሔር ጊዜና ሰዓት ነው። ጌታ ወደዚህ ምድር በመጣ ጊዜ ምን እንደሚሠራ አስቀድሞ በትንቢት ተነግሮአል፤ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ኢየሱስን በተመለከተ ከ300 በላይ ትንቢቶችን ተናግረዋል። ጌታ ኢየሱስ በሉቃስ ወንጌል ምዕ 4 ላይ በነቢዩ በኢሳይያስ የተጻፈውን ትንቢት ካነበበ በኋላ «ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ» (ቁ.21) አለ። ስለ እርሱ የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ መጣ። እጁ የሰለለችውን ሰው በፈወሰ ጊዜ ይህ የሆነው «በነቢዩ በኢሳይያስ የተባለው ይፈጸም ዘንድ» መሆኑን ወንጌላዊው ማቴዎስ ዘግቦአል (12÷17-21) ። ኢየሱስ በምድራዊ አገልግሎቱ ወቅት መሲሑ በመጣ ጊዜ የሚሠራውን ሥራ እያከናወነ እንደ ሆነ አስገንዝቦአል (ሉቃ 7÷21-23)። ምክንያቱም የመሲሑ ማንነት የሚታወቀው በሚያደርጋቸውና በሚያከናውናቸው ተግባሮች ነው።

| ወንጌላት | ምንባብ | ፈውሳቸውን የተቀበሉ ሰዎች |
|---|---|---|
| ማቴዎስ | 8÷16-17<br>11÷2-6<br>12÷15-21 | -በቅፍርናሆም የፈወሳቸው ብዙ ሰዎች<br>-የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት<br>-በባሕሩ አጠገብ የፈወሰው ሰው |

| | | |
|---|---|---|
| ማርቆስ | -- | --- |
| ሉቃስ | -- | --- |
| ዮሐንስ | -- | --- |

ከዚህ በመቀጠል የምንነጋገረው ስለ ፈውሱ መንገድ ይሆናል። ኢየሱስ ሰዎችን ለመፈወስ የተጠቀመባቸው መንገዶች እጅግ የሚያስደንቁ ናቸው። እርግጥ መንገዶቹ ቀላል ቢመስሉም ብርቱም ነበሩ። በወንጌላቱ ውስጥ የምናስተውላቸው አምስት (አንዳንዶች ስድስት እንደሆኑ ይናገራሉ) መንገዶች አሉ። ይሁንና ሁሉም በሁለት ፈርጅ ሊጠቃለሉ የሚችሉ ናቸው። አብዛኛውን ጊዜ ኢየሱስ ሰዎችን የፈወሰው ወይ ቃል ተናግሮ አልያም በእጁ ዳሶ ነው።

## ቃል ተናግሮ የፈወሳቸው

ጌታ ኢየሱስ ቃል በመናገር ብቻ የፈወሳቸው በርካታ ሰዎች አሉ። በተለይም በርኩስ መንፈስ የተያዙ ሰዎችን የፈወሰው ቃል ብቻ በመናገር ነው። ኢየሱስ በርኩስ መንፈስ በተያዙ ሰዎች ላይ እጁን አንድም ጊዜ አልጫነም። ይልቁንም በቃሉ ሥልጣን እያዘዘ ያስወጣቸው ነበር። በምኩራብ ርኩስ መንፈስ ያደረበትን ሰው ሲፈውስ ርኩሱን መንፈስ «ዝም በል! ከእርሱ ውጣ! ብሎ ገሠጸው» (ማር 1÷25)። በጌርጌሴኖን አገር በርኩስ መንፈስ የተያዘውን ሰውና (ማር 5÷8) የሚጥል በሽታ የነበረበትን ልጅ (ማር 9÷25) የፈወሰው ቃል በመናገር ብቻ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች «ተነሣና ዐልጋህን ተሸክመህ ሂድ» ሲላቸውና ሰዎቹም ሲፈወሱ እናያለን (ማር 2÷11፣ ዮሐ 5÷8)። ዐሥሩን ለምጻም ሰዎች ደግሞ «ሂዱ ራሳችሁን ለካህናት አሳዩ» ባላቸው ጊዜ ተፈውሰዋል (ሉቃ 17÷14)። እጁ የሰለለችበትን ሰው «እጅህን ዘርጋ» ብቻ ሲለው ተፈውሶአል (ሉቃ 6÷10)።

ኢየሱስ ሙታንን ያስነሣው ሁለት ጊዜ ብቻ እንደ ሆነ በወንጌላውያኑ ተዘግቧል። ሁለቱንም ጊዜ ሙታኑን ያስነሣቸው ቃል በመናገር ብቻ ነው። የናይን ከተማ ነዋሪ የነበረች አንዲት መበለት ሴት ልጇ ሞተ። ጌታም «አንተ ጐበዝ እለሃለሁ ተነሣ» ሲለው ልጁ ከሞት ተነሣ (ሉቃ 7÷14)። አልዓዛርን ደግሞ «ወደ ውጭ ና» ብሎ በጠራው ጊዜ ከመቃብሩ ወጥቶ ቆመ (ዮሐ 11÷43)። ኢየሱስ ሲሻው ቃል ብቻ ተናግሮ ይፈውሳል።

## በእጁ ዳሶ የፈወሳቸው

ኢየሱስ በእጁ ዳሶ የፈወሳቸው ሰዎች ቊጥር ሰባት እንደሆነ ተነግሮናል። ከእነዚህ መካከል አራቱን የፈወሳቸው እርሱ ራሱ በሽተኞቹን ዳሶ ሲሆን ሦስቱ የተፈወሱት ደግሞ በሽተኞቹ ራሳቸው ኢየሱስን ዳሰው ነው።

ኢየሱስ ራሱ በእጁ ዳሶ ከፈወሳቸው ሰዎች መካከል ሆዱ የተነፋው ሰው (ሉቃ 14÷1-4)፣ ማልኮስ (ሉቃ 22÷51)፣ በናዝሬትና (ማር 6÷5) በምሽት የፈወሳቸው ሰዎች (ሉቃ 4÷40) ይገኙበታል። ኢየሱስ ሲሻው በእጁ ዳሶም ይፈውሳል።

## ቃል ተናግሮና በእጁ ዳሶ የፈወሳቸው

ከወንጌላውያኑ ዘገባ እንደምንረዳው ኢየሱስ በአንዳንድ ጊዜ ቃል በመናገርና በእጁ በመዳሰስ የፈወሳቸው ስድስት ሰዎች አሉ፡፡ እነርሱም የጴጥሮስ ዐማች (ማቴ 8፥14-15፤ ሉቃ 4፥39)፣ ለምጻሙ ሰው (ማቴ 8፥1-3)፣ የመቶ አለቃው ልጅ (ሉቃ 8፥49-56)፣ ሁለቱ ዐይነ ስውር ሰዎች (ማቴ 9፥27-31)፣ የድካም መንፈስ ያደረባት ሴትና (ሉቃ 13፥10-13) ዐይነ ስውሩ በርጤሜዎስ (20፥29-31፤ ማር 10፥46-52፤ ሉቃ 18፥35-42) ናቸው፡፡ኢየሱስ ሲሻው ቃል ተናግሮና በእጁ ዳሶ ይፈውሳል፡፡

## ምራቁን እንትፍ ብሎ የፈወሳቸው

ጌታ ኢያሱ ምራቁን እንትፍ ብሎ (ቀብቶ) የፈወሳቸው ሦስት ሰዎች እንዳሉ በወንጌላውያኑ ተጠቅሶአል፡፡ ደንቆሮና ኰልታፋ የሆነውን ሰው (ማር 7፥32-35)፣ የቤተ ሳይዳውን ዐይነ ስውር ሰው (ማር 8፥22-25) እንዲሁም ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው (ዮሐ 9፥5-7) የፈወሰው ምራቁን እንትፍ በማለት ነው፡፡ ኢየሱስ ሲሻው ምራቁን እንትፍ ብሎ ይፈውሳል፡፡

## ከሩቅ ሆኖ የፈወሳቸው

ኢየሱስ ከሩቅ ሆኖ የፈወሳቸው ሦስት ሰዎች አሉ፡፡ አንደኛው የሹሙ ልጅ ነው (ዮሐ 4፥46-54)፡፡ ሁለተኛው የመቶ አለቃው ብላቴና ነው (ማቴ 8፥5-13)፡፡ ሦስተኛው የሲሮፊንቃዊቷ ልጅ ነው (ማር 7፥24-30)፡፡ ኢየሱስ ሲሻው ከሩቅ ሆኖ ይፈውሳል፡፡

እንግዲህ ነገሩን እንዲህ በዝርዝር ለማንሣት የፈለግነው የፈውስ መንገዱ የተወሰነ አለመሆኑንና ጌታ የወደደውን ነገር፣ እርሱ በመረጠው መንገድ ለማድረግ መብት ያለው መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ ጌታን መወሰን አይቻልም፡፡ እርሱ ደስ በሚለው መንገድ ለመሥራት መብት አለው፡፡ ከእኛ የሚጠበቀው እርሱ ለመሥራት በወሰነው መንገድ እንዲሠራ መተባበር ብቻ ይሆናል፡፡

ስለ እምነትና ፈውስ በሚነገርበት ጊዜ ሐዋርያው ጴጥሮስ በመጀመሪያው መልእክቱ ምዕ 2፥24-25 ላይ ያወሳው ቃል ብዙ ጊዜ አግባብ ባልሆነ መንገድ ሲተረጐም ይታያል፡፡ ይህ ምንባብ እስከ አሁን ስንነጋገርበት ከነበረው አርእስት ጋር ተጓዳኝነት ስላለው፣ የምንባቡን ሐሳብ በዐውዱ መሠረት ለመተንተን እንሞክራለን፡፡ በመሠረቱ ፈውስን በተመለከተ «የብልጽግና ወንጌል» መምህራን የሚጠቅሷቸውን ጥቅሶች በሙሉ አንሥተን ብንወያይ ደስ ባለን ነበር፡፡ ይሁንና በእኛ እምነት ወሳኝ ነው የምንለውን ምንባብ ወስደን ውይይቱን እንቀጥላለን፡፡

ጴጥሮስ «በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ» ሲል ምን ማለቱ ነው (1ጴጥ 2፥24-25)? ይህን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት ምናልባት የሐሳብ መተላለፍ እንዳይከሠት አንዳንድ ነጥቦችን ግልጽ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ይኸውም አሁን የምንኖረው በሁለት ዘመኖች መካከል ነው በአሁኑ ዘመንና በመጻኢው ዘመን፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችን በመሆኗ የመጻኢውን ዘመን በረከት አሁን መካፈል እንችላለን፡፡ እንዲህ ሲባል ግን በዚህ በአሁኑ ዘመን የመጻኢውን ዘመን በረከት ሙሉ በሙሉ እንካፈላለን ማለት አይደለም፡፡

ግን ደግሞ የመጻኢው መንግሥት ተካፋይ በመሆናችን የውድቀት ርግማን ሙሉ በሙሉ አይገዛንም:: ስለዚህ አንድ ጊዜ የምንታመመው፣ ሌላ ጊዜ የምንፈወሰው ከዚህ እውነታ የተነሣ ነው:: በእኛ እምነት እግዚአብሔር ዛሬም ፈዋሽ ነው:: ፈውሱን መረዳት ያለብን ግን በመካከላችን ከምትገኘው የእግዚአብሔር መንግሥት ባሕርይ አንጻር መሆን አለበት:: አቋማችንን ይሄን ያህል በግልጽ ካሳወቅን አሁን ጥያቄውን ወደ መመለሱ እናምራ:-

ቀደም ሲል የጠቀስነው ምንባብ የሚያወሳው ስለ ምንድን ነው? ስለ ሥጋዊ ፈውስ ወይስ ስለ መንፈሳዊ ፈውስ? የ1ኛ ጴጥሮስንም ሆነ ጴጥሮስ ይህን ምንባብ የጠቀስንበትን ዐውደ ምንባብ (ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕ 53) በሚገባ ስንመረምር የሁለቱም መጻሕፍት ደራስያን ስለ መንፈሳዊ ፈውስ እንጂ ስለ ሥጋዊ ፈውስ ለመናገር ዐላማ እንደሌላቸው እንገነዘባለን:: የሁለቱም ደራስያን ዋና ዐላማ ስለ መንፈሳዊ በሽታችን፣ ከእግዚአብሔርም ጋር ለዘላለም ስላቈራረጠን ሕመማችን መናገር ነው:: ያም በሽታችንና ሕመማችን በውድቀት ምክንያት ሁለንተናችንን የወረሰው ሞት ነው:: ኀጠ .አት ያስከተለብን መንፈሳዊ በሽታ አለ:: ከዚህ መንፈሳዊ በሽታ ደግሞ መፈወስ አለብን:: ይህ ሊሆን የሚችለው የእግዚአብሔር የመጨረሻው ዘመን ማዳን በመካከላችን ሲገለጥ ብቻ ነው:: 1ጴጥ 2÷24-25 ስለ እግዚአብሔር ማዳን (ፈውስ) አምስት መሠረታዊ ነገሮችን ያስተምረናል:

አንደኛው ስለ ማዳኑ እውነታ ነው (ቍ 24ለ):: «እርሱ ራሱ በሥጋው ኀጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ»:: ጴጥሮስ በግልጽ እንደሚናገረው ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው የኀጢአታችንን ዕዳ ለመክፈል ነው:: የእኛን ቅጣት እርሱ ተሸከመ፤ የእኛን ሞት እርሱ ሞተ:: ለፈጸምነው በደል፣ ለሠራነውም ኀጢአት መሥዋዕት መቅረብ አለበት:: ኢየሱስ ደግሞ መሥዋዕታችን ሆነ (1ቆሮ 5÷6፤ ዕብ 7÷26-27፤ 10÷12)::

ሁለተኛው ስለ ማዳኑ ዐላማ ነው (ቍ 24ሀ):: «ለኀጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር»:: የጌታ ሞት ምክንያታዊ ነው:: በኀጢአት የተተበተበ ሰው፣ በጨለማ የተከበበ ሰው፣ እርሱን ሊያከብረው እንደማይችል ያውቃል:: ለጽድቅ መኖር የምንችለው ከእስራታችን ስንፈታ ብቻ ነው:: ኀጢአትን ለመናቅ የሚያስችል ደረጃ ላይ ካልደረስን እርሱ የሚፈልገውን ዐይነት ሕይወት መኖር አንችልም:: የተፈጠርነው ትርጕም ላለው ሕይወት ቢሆንም፣ በውድቀት ጊዜ ግን ይህን መለኮታዊ ዐላማ አጥተናል:: እንግዲህ ጌታ፣ እኛ ወዳለንበት የመጣውና በእኛም ምትክ የሞተው ወደ ተፈጠርንበት ዐላማ ሊመልሰን ነው::

ሦስተኛው ስለ ማዳኑ መንገድ ነው (ቍ 24ሐ):: «በመገረፉ ቍስል ተፈወሳችሁ»:: ሰዎች ከምንም በላይ የሚያስፈልጋቸው መንፈሳዊ ፈውስ ነው:: ለእኛ እጅግ የሚጠቅመንን ነገር ከጌታ በላይ ሊነግረን የሚችል ማንም ሰው የለም:: በምድር አገልግሎቱም ቢሆን ሙሉ አካል ይዘን ወደ ሲኦል/ገሃነም ከምንወርድ ይልቅ ጐዶሎ አካል ቢኖረን እንደሚሻል አመልክቶናል (ማቴ 5÷30):: በሌላ በኩል ደግሞ ከሥጋዊውና ከምድራዊው ይልቅ መንፈሳዊውና ሰማያዊው እንደሚበልጥ ሲናገር «አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨርላችኋል» ብሎአል (ማቴ 6÷33):: ይህ የሚያሳየን ለሰው ልጆች ከምንም በላይ የሚያስፈልጋቸው መንፈሳዊ ፈውስ መሆኑን ነው:: እንዲያውም ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያስተምሩት ለሥጋዊው ፈውስ መሠረቱ

መንፈሳዊው ፈውስ መሆኑን ነው። ያለ እውነተኛ መንፈሳዊ ፈውስ እውነተኛ ሥጋዊ ፈውስ ሊኖር አይችልምና።

**ሦ**ራተኛው ስለ ማዳኑ አስፈላጊነት ነው (ቊ 25ሀ)። «እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና»። ጴጥሮስ ይህን ተምሳሌታዊ አገላለጽ የወሰደው፣ የብሉይ ኪዳን ጸሓፊዎች፣ እስራኤል ያለ መሪ በምትሆንበት ወይም በክፉ ገዦች ሥር በምትወድቅበት ሰዓት የምታሳየውን ባሕርይ ለመግለጽ ከተጠቀሙበት ነው (ዘኊ 27÷16-17፤ 1ነገ 22÷17፤ መዝ 119÷176፤ ኤር 50÷6፤ ሕዝ 34÷5-6)። እስራኤል ይህ ሁኔታ ሲያጋጥማት ሁለንተናዋ ይናጋል። መንፈሳዊ ሕይወቷ ይወድቃል፤ ሥጋዊም ሕይወቷ ይነቅዛል። ይህ እንግዲህ እረኛው በማይኖርበት ሰዓት በበጎቹ ላይ የሚደርሰው ዕጣ ፈንታ ነው። ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ሲያስጠነቅቅ፦«በዚህች ሌሊት ሁላችሁ በእኔ ትሰናከላላችሁ፤ እረኛውን እመታለሁ በጎችም ይበተናሉ» ብሏቸው ነበር (ማር 14÷27)። ጴጥሮስ ሲመልስለት፦ «ሁሉም ቢሰናከሉ እኔ ግን ከቶ አልሰናከልም አለው»። ከታሪኩ እንደምንረዳው ጴጥሮስ ኢየሱስን ከድቶ ሸሽቶአል። እረኛም የሌላት ነፍስ ልክ እንዲሁ ናት። ትቅበዘበዛለች ከዚያም ትጠፋለች። ነፍሳችን በታላቁ እረኛ ካልተመለሰች መመለሻ አይኖራትም።

**አ**ምስተኛው ስለ ማዳኑ ውጤት ነው (ቊ 25ለ)። «አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል»። ስንቅበዘበዝ ያየን ጌታ ሊመልሰንና ሊታደገን መጣ። በብሉይ ኪዳን እስራኤል እንደ በግ ተመስላ እንደ ነበር ሁሉ፣ እግዚአብሔርም እንደ እረኛ ተመስሏል (ዘፍ 48÷15፤ መዝ 23፤ ኢሳ 40÷11፤ ኤር 23÷1-4፤ ዘካ 11÷4-17)። እግዚአብሔር ማዳኑን የሰጠን ከመቅበዝበዝ ሕይወት ወጥተን በእርሱ እንድናርፍ፣ ወደ እርሱም እንድንመለስ ነው። «መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል» (ዮሐ 10÷11)። ይህ እረኛ እረኝነቱ «የነፍስ» ነው። በመሆኑም ጴጥሮስ ጌታውን ከድቶ እንደ ሸሸ አልቀረም። ጌታ ስለ ነፍሱ ተሟግቶ ስለ ነበር፣ እንደ ባዘነ አልቀረም። «ስምዖን ሆይ እነሆ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና» (ሉቃ 22÷31-32)።

**እ**ንግዲህ 1ኛ ጴጥሮስ 2÷24-25 የሚናገረው ስለ ምንድን ነው? የክፍሉ ዐውደ ምንባብ እንደሚያስረዳን ክፍሉ የሚናገረው ስለ መዳን ወይም ደኅንነት ነው። ግን ስለ የትኛው መዳን? ስለ ሥጋ ወይስ ስለ ነፍስ? ክፍሉ በግልጽ የሚናገረው ስለ ነፍስ (ወይም መንፈሳዊ) ፈውስ እንጂ ስለ ሥጋዊ ፈውስ አይደለም። ወደዚህ ድምዳሜ ያልደረሰ ትርጓሜ ዐውዳዊ፣ ሐቲታዊና ሥነ ልሳናዊ ጕዳዮችን በትክክል ያላገናዘበ መሆን አለበት። ምክንያቱም የአንድ ምንባብ ትክክለኛ ትር ጕሙ የሚወሰነው በዐውዱ፣ በሐቲቱና በሥነ ልሳኑ መሠረት ነው። ደግሞም እውነተኛ ተርጓሚ የሚያሰኘን ምንባቡ የሚለውን ስንል ብቻ ነው። አልያ እኛ የምንፈልገውን ምንባቡ እንዲልልን የምናደርግ ከሆነ እውነተኞች አይደለንም።

## የእምነት እንቅስቃሴ ታሪካዊ ዳራ
### ምዕራፍ አምስት

«**የ**እምነት እንቅስቃሴ» በመባል የሚታወቀውን መናፍቃዊ ትምህርት ጠንሳሽ ናቸው የሚባሉት፣ በ1879 ዓ.ም በኒው ዮርክ ከተማ የተወለዱት ዊሊያም ኬንየን ናቸው።

ኬኒየን የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን የነበሩ ሰው ቢሆኑም፣ በ1892 ዓ.ም ላይ ዲበ አካላዊ መናፍቃን በመባል የሚታወቁት መናፍቃዊ እንቅስቃሴዎች ከፈለቁበትና ቦስተን ከተማ ከሚገኘው ኤመርሰን ኮሌጅ በመግባት፣ «አዲሱ አስተሳሰብ» (New Thought) በመባል የሚታወቀውን ትምህርት ተማሩ:: ይህ ትምህርት መሠረት ያደረገው፣

> «በቁሳዊ ነገሮች ላይ ለሚከሠቱት ነገሮች ሁሉ ምንጫቸው፣ በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ እውን የሆነው ነገር ሲሆን. . . አወንታዊ ቃል በመናገር እንደ ጤንነትና ሀብት ያሉትን ቁሳዊ ጥቅሞች እውን ማድረግ (ማግኘት) ይቻላል»[1]

በሚል አስተምህሮ ላይ ነው:: ዲበ አካላዊ መናፍቃን በመባል ከሚታወቁት መናፍቃዊ እንቅስቃሴዎች መኻል አንዱ የሆነውና ክርስቲያን ሳይንስ በመባል የሚታወቀውን መናፍቃዊ ድርጅት መሥራች የሆነችው ሜሪ ቤከር ኤዲ፣ በጀርባ ዐጥንት በሽታ እየተሠቃየች ሳለ፣ ሜይን ስቴት፣ ፓርትላንድ ከተማ ውስጥ «የአእምሮ ኀይል ፈውስ» ("mental healing") በሚባለው የፈውስ ዘዴ ታዋቂ ከነበረው ዶክተር ፊኒስ ኩምቢ ጋር ተገናኘች:: ፊኒስ ኩምቢ፣

> «ቁስ አካል እውነትነት የለውም:: እውነት ያለው በመንፈሳዊው ዓለም ብቻ ነው:: እውነተኛው ሰው መንፈስ ስለሆነ፣ በአእምሮአችን ወይም በስሜት ሕዋሳቶቻችን ከምንገበያቸው ዕውቀቶች ሁሉ የሚበልጠው በመገለጥ የምናገኘው ዕውቀት ነው:: የበሽታ ምንጭ መንፈሳዊ ነው:: እኛ ግን በውስጣችን አምላክ ስለሚኖር፣ ይህን አምላካዊ ኀይል በመጠቀም በሽታዎቻችንን ማባረር እንችላለን»[2] የሚል ዲበ አካላዊ የሆነ መናፍቃዊ ትምህርት ያስተምር ነበር::
> ሜሪ ቤከር ኤዲ፣ በኩምቢ የፈውስ ቀመር ተፈወሰች:: የኩምቢ ደቀ መዝሙርት

በመሆንም ክርስቲያን ሳይንስ የተባለውን ሃይማኖታዊ ድርጅት መሠረተች:: እንደ ኩምቢ ሁሉ ሜሪ ቤከረም፣ «ቁስ አካል እውነታነት የለውም:: ስለዚህም በስሜት ሕዋሳቶቻችን ስለ ቁስ አካል የምንማረው ትምህርት ሁሉ ስሕተት ነው፤ እውነታነት የሌለው የአእምሮ ምትሐት (illusion) እንጂ:: ኀጢአት፣ በሽታና ሞት የተሳሳተ የአእምሮ ውጤቶች ናቸው፤ ወይም የአእምሮ መቀባዠሮች ናቸው:: ስለዚህ የተስተካከለ የአስተሳሰብ አቋም በመያዝ፣ ዘወትር ጤናሞችና ባለጠጎች መሆን እንችላለን»[3] የሚል ትምህርት ማስተማር ጀመረች::

ሜሪ መከር ኤዲ ይህን ትበል እንጂ፣ ዐይኗን ያማት ስለነበር የዐይን መነጽር ታድርግ እንዲሁም የተለያዩ በሽታዎች ስለነበሩባት አብዝታ ዶክተር ዘንድ ትሄድ እንደ ነበር በሕይወት ታሪኳ ላይ የተጻፉ ጽሑፎች ያስረዳሉ::

በ1917 ዓ.ም የተወለዱትም ኬኔት ሐጊን እንቅስቃሴውን ይበልጥ በማራመድ፣ የእንቅስቃሴው አባት በመባል ታዋቂነትን አገኙ:: የእንቅስቃሴው ትምህርት በሕይወታቸው ስፍራ ሊያገኝ እንዴት እንደቻለም ሲገልጹ፣ «በዐሥራ ሰባት ዓመቴ በማይድን የልብ በሽታ ታምሜ በዐልጋ ላይ ተኝቼ ሳለሁ፣ የማር 11÷24 ጥቅስ

---

[1] Charles E. Hummel, Fire in the Fire Place (Ivp, 2nd ed, 1993) ገጽ 5::
[2] D.R. Mcconnell, A Different Gospel (Hendrickson Pub, Inc, 1998) ገጽ 25
[3] ዝኒ ከማሁ::

በመገለጥ ወደ እኔ መጣ፤ ጥቅሱንም ሳንሰላስል፣ ፈውሴን የምቀበለው ከማመን በኋላ እንደ ሆነ ተገነዘብሁ። በዐልጋዬ ላይ ተኝቼም ሳለሁ፣ ከበሽታዬ ተፈውሻለሁ እያልሁ መናገር ጀመርሁ፤ ከሁለት ቀን የሙከራ ጊዜ በኋላም፣ ከዐልጋዬ ተነሥቼ ከቤተ ሰቦቼ ጋር ቍርስ መብላት ቻልሁ»[4] ይላሉ።

ኬኔት ሐጌን በ1937 ዓ.ም ላይ «የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት» ተቀብለው የእግዚአብሔር ጉባኤ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሆኑ። 1943ዓ.ም ነገረ መለኮት ሳይማሩ «ምስጢራዊ በሆነ መንገድ የማስተማር ስጦታ» እንደ ተቀበሉ ይገልጹ ጀመር። ከዘጠኝ ዓመት በኋላም «መገለጦችና ራእዮችን ማየት የሚያስችላቸውን የነቢይነት ስጦታ» (አገልግሎት) ተቀበሉ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ባሉት ዓመታት ለስምንት ጊዜ ያህል ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንደ ተገናኙና ብዙ የመገለጥ ልምምዶችንም እንደተቀበሉ ይገልጻሉ።

ኬኔት ሐጌን የነቢይነትና የማስተማር ስጦታ ስለተቀበልሁ ትምህርቴ መለኮታዊ መገለጦችን የሚያስተላልፍና መጽሐፍ ቅዱስን ልዩ በሆነ መንገድ የሚተነትን ነው ቢሉም፣ ትምህርታቸው መሠረት ያደረገው የኬንያንን መጻሕፍት ለመሆኑ በርካታ የጽሑፍ ማስረጃዎች አሉ። ምንጯቸውን ሳይጠቅሱ ከኬንየን መጻሕፍት ቃል በቃል በመውሰድ (ስርቆተ ጽሑፍ ይሉታል ፈረንጆቹ (Plagiarisms) ያሳተሟቸው መጻሕፍት ለዚህ እውነት በቂ እማኞች ናቸው። ከ1970ዓ.ም ወዲህም የኬኔት ሐጌን ስም እየገነነ መጣ። «የእምነት ዐወደ ጥናት በሬዲዮ» ("Faith Seminar of the Air") የሚል የሬዲዮ ሥርጭት ጀመሩ። በ1974 ዓ.ም ከልጃቸው ጋር በመሆን፣ «ሬማ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት» በመባል የሚጠራውን ኮሌጅ ከፈቱ። ይህ ኮሌጅ ከ1980-1981 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ብቻ ከሁለት ሺህ በላይ ተማሪዎችን ለማስተማር ተቀብሎአል። ከተቈረቈረ ከዓመት በኋላም 11,400 ለሚሆኑ ተማሪዎች የተልእኮ ትምህርት መስጠት ጀመረ።

በዚህ መልኩ እንቅስቃሴው እየተስፋፋ ሄደ። ኬኔት ሐጌንና ግሎሪያ ኮፐላንድ «የብልጽግና ትምህርት» የሚለውን አስተምህሮ ትኩረት በመስጠት፣ «የእምነት ቃል» የሚባለውን ትምህርት በስፋት ማስተማራቸውን ተያያዙት። በ1975ዓ.ም ላይ የሬዲዮው ሥርጭት ከተጀመረ ከአራት ዓመት በኋላ፣ አገልግሎቱን በቴሌቪዥንም ማሠራጨት ጀመሩ።

የእነ ሐጌንና የእነ ኮፐላንድ የእምነት ቃል ትምህርት እንደነ ጄሪ ሳቪሊን ያሉትን «የእምነት ቃል» አስተማሪዎችን አፈራ። ፍሬዴሪክ ፕራይስ የተባለው ሌላው «የእምነት ቃል» ሰባኪም፣ በኬኔት ሐጌን ስብከት ወደ እንቅስቃሴው እንደ ገባ ይገልጻል። እነዚህ የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን በዓመት ከ30,000 በላይ መጻሕፍትንና ካሴቶችን ያሠራጫሉ፤ ከ500,000 በላይ የሚሆኑ በራሪ ጽሑፎችንም ይበትናሉ። እንቅስቃሴው ከአሜሪካንም ውጪ በተለያዩ አገሮች ውስጥ በከፍተኛ ፍጥነት በመስፋፋት ላይ ነው። በስዊዲን አገር ኦፕስላ በተባለው ስፍራ የሚገኘው፣ «የሕይወት ቃል ቤተ ክርስቲያን» ከ1,000 በላይ ተማሪዎችን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ በማስተማር ላይ ይገኛል። በደቡብ አፍሪካ የሚገኘው የእንቅስቃሴው ማእከል፣ «ሬይ ማክኮውሊ ሬማ አገልግሎት» በመባል ሲታወቅ፣ በናይጄሪያ የሚገኘው ደግሞ፣ ዴቪድ ኦይዲፖ ሊቪንግ

[4] ዝኒ ከማሁ።

ፌዝ ወርልድ አውትሪች» ይባላል። እንቅስቃሴው በሶቪየት ኅብረትም በከፍተኛ ፍጥነት በመስፋፋት ላይ ይገኛል።

የእምነት እንቅስቃሴ ትምህርት በተጠናከረ መልኩ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ያደረገው፣ በናይጄሪያ የሚገኘው፣ የ«ዴቪድ አይዲፓ ሊቪንግ ፌዝ ወርልድ አውትሪች» የሚባለው ድርጅት ነው። ከዚህ በፊት የእንቅስቃሴው አስተምህሮ ወደ አገሪቱ የገባው «ስመ ጥር» ናቸው በሚባሉት የውጪ አገር መጋቢያን፣ ሰባኪያንና መምህራን መጻሕፍትና ካሴቶች አማካይነት ነው።

በተለይ በደርግ ዘመን ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች ለመንፈሳዊ ዕድገት ታላቅ ጠቀሜታ አለው በሚል፣ የእነዚህን ግለሰቦች ስብከትና ትምህርት በጾምና በጸሎት እንዲሁም በምዕላ (በማኅበረ ጸሎት) ጊዜያቸው አብዝተው ያነቡትና ይሰሙት ነበር። ይህን መደላድል ሲያደርግ የቆየው እንቅስቃሴ በተጠናከረ መልክ በናይጄሪያ አቋርጦ ሲገባ፣ ብዙ ሰዎች ልባቸውን በመክፈት በእልልታና በሆታ ተቀበሉት፤ ከተጠበቀውም በላይ ዕድገት አሳየ። በጥቂት ዓመታት ውስጥ መሠረተ እምነታቸውን የእንቅስቃሴውን አስተምህሮ ያደረጉ በርካታ ቤተ ክርስቲያናት በመዲናዋ በአዲስ አበባና በሌሎችም አካባቢዎች መከፈት ጀመሩ፤ እንቅስቃሴውም ዕለት በዕለት እያደገ ሄደ። በዚህ እኩይ ትምህርት ዋነኛ ሰለባ የሆኑትም የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ምዕመናን ናቸው።

ለእንቅስቃሴው መስፋፋት ከላይ ያየናቸው ሁኔታዎች ሰፊውን ድርሻ ቢወስዱም፣ የአስተምህሮውን ሕጸጽ ግልጥልጥ አድርገው የሚያስተምሩ መምህራን የተፈለገውን ያህል ባለመኖራቸው፣ ያሉትም «የመንፈስ ቅዱስ ተቃዋሚዎች» የሚል ቅጥያ እየተሰጣቸው መወገዛቸው እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ለቃለ እግዚአብሔር ትምህርት ያላት ስፍራ እየጠበበ መምጣት፣ ለችግሩ መግዘፍ እንደ ምክንያት ከሚቈጠሩት ውስጥ ዋናኞቹ ናቸው።

## የእምነት እንቅስቃሴ ስለ እምነት ያለው አስተምህሮ
## ምዕራፍ ስድስት

በዚህ አነስተኛ መጽሐፍ ትኩረት ሰጥተን የምናጠናው እንቅስቃሴው «እምነትን» አስመልክቶ ያለውን አስተምህሮ ሲሆን፣ ትምህርቱ ከቃለ እግዚአብሔር ጋር ምን ያህል ይጣጣማል የሚለውንም ጒዳይ ለመመልከት እንሞክራለን።

እንቅስቃሴው በአስተምህሮተ እግዚአብሔር፣ በሥነ ሰብ፣ ሰዎች በኀጢአት ስለመውደቃቸው፣ ስለ ክርስቶስ የደኅንነት ሥራ ስለትምህርተ ክርስቶስ እንዲሁም አስተምህሮተ ቤተ ክርስቲያንን አስመልክቶ የሚያስተምረው ትምህርት ከብሉያትና የሐዲሳት ትምህርት ጋር ፍጹም የሚቃረን ነው። ነገር ግን ካለን የገጽ ውስንነት ካላይ ያነሣነውን ርእሰ ጒዳይ ብቻ በዚህ አነስተኛ መጽሐፍ ውስጥ እንቃኘዋለን።

## እምነት

«በእምነትህ ላይ እምነት ይኑርህ»። እንደ እንቅስቃሴው መምህራን አባባል እግዚአብሔር ራሱ እምነት አለው። አምላክ ለክርስቲያኖችም ይህን ዐይነቱን እምነት ሰጥቶአቸዋል። ይህ አምላክ ራሱ ያለው ዐይነት እምነት (ማር 11÷12) ለክርስቲያኖች የተሰጠው በስጦታ ነው (ሮሜ 12÷3፤ ኤፌ 2÷8)። እግዚአብሔር ተራራ የሚያናውጠውን ይህን ዐይነቱን እምነት ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ሰጥቶታል። እግዚአብሔር ዓለማትን የፈጠረው በዚህ ዐይነቱ እምነት ነው (ዕብ 11÷3፤ እንዲሁም ሮሜ 4÷17)[5] ።

ክርስቲያን ያልሆነ ሰው እንኳ የሚናገረውን ቃል የሚያምን ከሆነ የተናገረውን ያገኛል። ምክንያቱም ኢየሱስ፣ «ማንም ያለው ነገር እንዲያደርግለት ቢያምን. . . » (ማቴ1÷23) ይሆንለታል ብሏል[6]። እምነቱ በአማኒያኑም ሆነ በኢአማኒያኑ ሕይወት የሚሠራ መንፈሳዊ ሕግ ነውና[7] እንዲያውም ሐጌን እንዲህ ይላሉ፡-

> «ያልዳኑ ሰዎች ሲሳካላቸው የማየቴ ጉዳይ ግራ ያጋባኛል። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያኔ ሰዎች [ይህ ዐይነቱን] ውጤት አያዩም። ኀጢአን ምን እያደረጉ ነው ለሚለው ያገኘሁት መልስ ከዚህ ዐይነቱ የእግዚአብሔር ሕግ ጋር መተባበራቸው ነው፤ ይኸውም የእምነት ሕግ ነው።»[8]

በአጠቃላይ «ማናቸውንም ነገር ከእግዚአብሔር ማግኘት የሚፈልግ ሰው፣ በእምነቱ ላይ እምነት ሊኖረው ይገባል[9]። እንግዲያው እምነት ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን ጥያቄ የእንቅስቃሴው መሪዎች «ኀይል ነው»[10] የሚል ትርጉም ይሰጡታል። ይህም እምነት ያልሆነውን እውን ማድረግ፣ ያልተፈጠረውን ነገር ደግሞ መፍጠር ይችላል (ሮሜ 4÷7)[11]። እምነት ረቂቅ ሆኖ የማይታየውን ነገር እንዲታይ ያደርገዋል[12]።

የእንቅስቃሴው መምህራን፣ «እውነተኛ እምነት ቁሳዊ የሆነውን እውነታ አይቀበልም» ይላሉ (ሮሜ 4÷19፤ 2ቆሮ 4÷18፤ 5÷17)[13]። እንዲሁም እምነት ምክንያታዊ እንዳልሆነ ነገር ግን ከአመክኒዮ ጋር እየተጋጨ በጭፍን የሚታመን እንደ ሆነ ይገልጻሉ[14]።

እንደ እንቅስቃሴው መምህራን ቃለ እግዚአብሔር እምነት የሚለውን ቃል የሚጠቀመው በዐላፊ ጊዜ ነው (ዕብ 11÷1)፤ ነገር ግን ተስፋ በትንቢታዊ ጊዜ ነው ጥቅም ላይ የዋለው። ስለዚህ እምነት አሁን በእጃችን ያለ ነገር እንጂ (ማር 11÷23) ወደፊት

---

[5] Hagin, New Thresholds of Faith ገጽ 74-76። Copeland, The haws of Prosperity, ገጽ 18-19
[6] Hagin, Having Faith in Your Faith (Tulsa Keneth Hagin ministries, 1980) ገጽ 3-5
[7] Charles Capps, The Tongue: A Creative Force (Tulsa: Harrison House 1976), ገጽ 132
[8] Hagin, Haring Faith in Your Faith, ገጽ 3-4
[9] ዝኒ ከማሁ ገጽ 5።
[10] Copeland, The Force of faith በተለይ ገጽ 13-14፡19 እንዲሁም Capps, Faith and Confession, ገጽ 44
[11] Hagin, New Thresholds of Faith, ገጽ 7-8 እንዲሁም Right and Wrong Thinking Copeland, Our Covenant with God, ገጽ 38-39።
[12] Hagin, Real Faith, ገጽ 26። Knowing What Belongs to Us ገጽ 6-7፡10፡29። Price, How Faith Works, ገጽ 25
[13] Price, How Faith Works, ገጽ 31።
[14] Hagin, Words, ገጽ 32 በተጨማሪም ገጽ

*በእጃችን የሚገባ ጉዳይ አይደለም*[15]*:: ስለዚህ፣ «ተስፋ የምታደርገውን ነገር ትተህ፣ ያለህን እምነት በመጠቀም የምትፈልገውን ነገር በእጅህ አስገባ»*[16] *ይሉናል::*

## *አወንታዊ ዐዋጅ*

*እንደ እንቅስቃሴው መምህራን አስተምህሮ ማንኛውንም ነገር እንደምናገኝ ብናምንና ያመነውንም ነገር እንዳገኘነው ብናውጅ ያሻነውን* (*የፈለግነውን*) *ነገር እናገኛለን* (*ሮሜ* 10÷10)*:: ይህ የፈለግነውን ነገር የምናገኝበት «ቀመር» ወይም «ሕግ» ነው*[17]*:: የምናገኛቸው ክፉም ሆኑ ደግ ነገሮች በእምነት ሆነን በቃላት በምንገልጻቸው ነገሮች ይወሰናሉ*[18]*:: እንቅስቃሴው እነዚህን ባዕድ ትምህርቶች በቃለ እግዚአብሔር ላይ ለማስደገፍ የሚሞክረው በሚከተሉት ሁለት መንገዶች ነው:: አንደኛው:- እግዚአብሔር ዓለማትን ለመፍጠር እንደ መሣሪያ አድርጎ የተጠቀመው ቃላትን ነው* (*ዘፍ* 1፤ *መዝ* 33÷6፡9፤ *ዕብ* 11÷3)*:: ይህም ቃል በሁለንታ* (*በጽንፈ ዓለም ውስጥ*) *እጅግ ኀይለኛ ነገር መሆኑን የሚያመለክት ነው*[19]*:: ሁለተኛው በርካታ የቃለ እግዚአብሔር ንባባት ሰዎች በሚናገሩት ነገር ዕጣ ፈንታቸው እንደሚወሰን ያስረዳሉ:: የምንናገራቸው ማናቸውም ነገሮች የሕይወትም ሆነ የሞት ኀይል አላቸው* (*ምሳ* 18÷21)*::*

*መጽሐፍ ቅዱስ ለምትናገሩት ነገር ጥንቃቄ ይኑራችሁ የሚለው፣ ቃላት ክፉም ሆነ ደግ ነገር የማድረግ ኀይላቸው ከፍተኛ ስለሆነ ነው* (*ምሳ* 6÷2፤ *ማቴ* 12÷37)[20]*:: እንቅስቃሴው ስለ «እምነትና» ስለ «ዐዋጅ» የሚያስተምረውን ትምህርት አንድ የእንቅስቃሴው ዕውቅ መምህር ያሉትን ነገር እንመልከት:- «እምነት ፈጣሪ ኀይል ነው:: ቃል ደግሞ ይህን ፈጣሪ ኀይል የሚሸከም መሣሪያ ነው:: እምነት እግዚአብሔርን ለሥራ የሚቀሰቅሰው ሲሆን፣ ፍርሀት ደግሞ ሰይጣንን ለሥራ ያነሣሣዋል»*[21]*::*

*«አንዲት ጠንቋይ እንዲህ ስትል ነገረችኝ «በጥንቈላ አዕዋፍን እንዲሁም ሰዎችን በቃል እንዴት እንደምንገድል ተምረናል:: ሊሸነፉ የሚችሉበትን የተወሰኑ ቃላት በመናገር፣ በአዕዋፋትም ሆነ በሰዎች ላይ በሽታን እንዴት ማምጣት እንደምንችል ተምረናል:: ቃል በመናገር አዕዋፋትን እገድላለሁ! አለችኝ' እኔም፣ 'እግዚአብሔር ሆይ ሰይጣን ይህን የመሰለ ኀይል እንዳለው አላውቅም ነበር' አልሁት:: እግዚአብሔርም፣ 'ሰይጣን በቃል ይገድላል፤ አንተ ደግሞ በቃል ሕይወትን መስጠት ትችላለህ' አለኝ:: እኛ ክርስቲያኖች በአፋችን ላይ ያለውን የቃል ኀይል አናውቅም*[22]*:: ስለዚህ፣ 'ወደ እግዚአብሔር ፊት ቀርባችሁ ጌታ ሆይ ፈቃድህ ቢሆን የሚል፣ እምነትን የሚገድል ጸሎት በፍጹም! በፍጹም አትጸልዩ:: ትሕትና ይመስላችሁ ይሆናል፣ ነገር ግን ጅልነት ነው:: ይህን ማለታችሁ እግዚአብሔርን ሞኝ ነህ እንደ ማለታችሁ ነው:: ይህ ዐይነቱ*

---

[15] Copeland, The Force of Faith, **ገጽ** 9-12:: Price, How Faith Works, **ገጽ**48::
[16] Hagin, The Real Faith **ገጽ** 41-42:: Capps, Faith and Confession **ገጽ** 15
[17] Hagin The Real Faith **ገጽ** 25
[18] Hagin, New Thresholds of Faith **ገጽ** 43:: Price, How Fath Works, **ገጽ** 111::
[19] Hagin, New Thresholds of Fath **ገጽ** 10
[20] **ዝኒ ከማሁ ገጽ** 77:: Capps, The Tongue, **ገጽ** 12-14:: Price, How Faith Works **ገጽ** 58
[21] D.R Mcconnell **ገጽ** 146 **ከ** Benny Him, "Double Portion Anointing Part #3" audiotape#A 031791-3 **ጠቅሶ እንደ ጻፈው::**
[22] **ዝኒ ከማሁ** 146 **ከ** Benny Hinn, "Praise the Lord" Program on TBN (1June 1989) **ጠቅሶ እንደ ጻፈው::**

ጸሎት እምነታችንን ከመሠረቱ በመንቀል፣ ፍርሀት በሕይወታችን እንዲነግሥ በማድረግ ሰይጣን እንዲሠራ ያደርገዋል»[23]

## ጸሎት

እንደ እምነት እንቅስቃሴ አስተምህሮ እግዚአብሔር አስቀድሞ የሰጠንን ነገር ስጠን ብሎ መጸለይ እንዲሁም ቀድሞ ያደረገውን ነገር አድርግ ብሎ መማጸን ስሕተት ነው:: እግዚአብሔር ቀድሞውንም ቢሆን በክርስቶስ ወጀአዊ ሥራ ደኅንነትን፣ የኀጢአት ይቅርታን፣ ፈውስን እንዲሁም ብልጥግናን ሰጥቶናል[24]::

ቀድሞ የሰጠውን ነገር ስጠን እንዲሁም ቀድሞ ያደረገውን ነገር አድርግ ብሎ መጸለይ የሰንካላ እምነት ዐይነተኛ ምልክት ነው:: ስለዚህ «ፈቃድህ ቢሆን» ብሎ መጸለይ ስሕተት ነው፤ ምክንያቱም ደኅንነት፣ ፈውስ፣ የኀጢአት ይቅርታ እንዲሁም ብልጽግና ቀድሞውኑም ቢሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ናቸውና:: ስለዚህ በአንድ ርእሰ ጉዳይ ላይ ከመጸለያችን በፊት የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነው የቱ ነው የሚለውን ጥያቄ ከቃለ እግዚአብሔር መመለስ ይፈልጋል:: ይህን ካረጋገጥን በኋላ እነዚህ ነገሮች የእኛ መሆናቸውን በእምነት ማወጅ ነው:: ስለዚህ በጸሎታችን ልንከውነው የሚገባን ነገር፣ እግዚአብሔር ቃሉን እንዲያከብር «ማዘዝ» ብቻ ነው (ዮሐ 14÷13-14 እንዲሁም 15÷7 ባሉት ክፍሎች «ጠይቁ» የሚለው ቃል ይህ ዐይነቱን ትርጒም ወክሎ እናገኘዋለን»)[25]:: ኮፕላንድ ይህን ጉዳይ እንዲህ ሲሉ ያብራሩታል:-

«አማኞች እንደ መሆናችሁ መጠን፣ በኢየሱስ ስም የማዘዝ መብቱ አላችሁ:: ቃሉን መሠረት እስካደረጋችሁ ድረስ፣ ቃሉን እውን እንዲያደርግ የማዘዝ መብት አላችሁ:: ምክንያቱም መሠረት ያደረጋችሁት ቃሉን ነውና:: ታማኝ የሆነ ሰው ቃሉን እስከሰጣችሁ ድረስ በቃሉ የታሰረ ነው»[26]::

## የእምነት እንቅስቃሴ ስለ እምነት የሚያስተምረው ትምህርት ግምገማ

የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን እምነትን በተመለከተ ያላቸውን ትምህርት ተመልክተናል:: ከዚህ በኋላ ትምህርቱን በቃለ እግዚአብሔር ወደ መመዘኑ እንዘልቃለን::

የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር እምነት አለው የሚለውን ትምህርት አያስተምረንም:: ምክንያቱም እምነት ማለት በአንድ ሰው ወይም በተወሰነ ነገር ወይም ደግሞ በተለየ አካል መተማመን ወይም መመካት ማለት ነውና (ምዕራፍ አንድን ያነሷል):: «እግዚአብሔር እምነት አለው» የሚለውን ዐረፍተ ነገር መጠቀም የምንችለው፣ እግዚአብሔር በራሱ ኀይልና ጥበብ ይተማመናል በሚለው ትርጒሙ ብቻ ነው:: ነገር ግን የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን እግዚአብሔርንም ሆነ ሰዎችን አስመልክተው እምነት የሚለውን ቃል የሚጠቀሙት፣ አንድ ሰው የሚያምነውን ወይም

---

[23] ዝኒ ከማሁ::
[24] Hagin, You Can Write Your Own Ticket with God, ገጽ 18:: Capps Faith and Confession ገጽ 15::
[25] Hagin, Name of Jesus, ገጽ 73-74::
[26] Copeland, Our Covenant With God, ገጽ 40-41::

የሚፈልገውን ነገር በአንደበቱ በመናገር የሚያገኝበት ወይም እውን ያልሆነውን ነገር እውን የሚያደርግበት፣ ዘላለማዊ ከሆነው መንፈሳዊ ሕግጋት ጋር ተጣምሮ የሚሄድ ኀይል አድርገው ነው:: ነገር ግን ይህ ዐይነቱ ትምህርት ከቃለ እግዚአብሔር ጋር በግልጽ የሚቃረን ነው::

ክርስቲያኖች ሁሉ የሚያድን እምነት ተሰጥቷቸዋል፤ ነገር ግን ክርስቲያኖች ሁሉ ተኣምር የሚሠራ እምነት የላቸውም:: በርግጥም እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፤ የእምነት እንቅስቃሴ መምህራንም በዚህ እውነት ይስማማሉ (ሮሜ 12÷3፤ ኤፌ 2÷8):: ነገር ግን እግዚአብሔር «ተራራን የሚያናውጥ» እምነት ለሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ አልሰጠም:: ጳውሎስ እንደሚለው ይህ ዐይነቱ እምነት ከመንፈሳዊ ስጦታዎች መኻል አንዱ ነው (1ቆሮ 12÷9፤ 13÷2፤ ሮሜ 12÷3፡6):: ጳውሎስ ክርስቲያኖች ሁሉ አንድ ዐይነት ስጦታ የላቸውም የሚለውም ለዚሁ ነው (ሮሜ 12÷4-6፤ 1ቆሮ 12÷4-6፡ 14-19፡ 28-30)::

ጌታ «ተራራን ስለሚነቅለው» እምነት ሲያስተምር (ማቴ 21÷21፤ ማር 11÷23) ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ የዚህ ዐይነቱ እምነት ባለቤት ነው አላለም:: ይህ ዐይነቱ እምነት ስጦታ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ ራሱ፣ «እንደ ፈቀደ» የሚሰጠው (1ቆሮ 12÷11)::

አንዳንዴ እግዚአብሔር ለማመን አስቸጋሪ የሆነውን ነገር እንድናምን እምነት ይሰጠናል:: ነገር ግን ቃለ እግዚአብሔር፣ ይህ ዐይነቱ እምነት ክርስቲያኖች ሁሉ ሁል ጊዜ ገንዘብ ያደረጉት እምነት ነው አይልም::

ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ሁሉ እምነት የላቸውም:: እምነት ስለሌላቸውም ነው ክርስቲያን ያልሆኑት፤ እምነት ሰዎች ሁሉ ያላቸው ነገር ሳይሆን እግዚአብሔር አምላክ ሰዎች ለደኅንነታቸው በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነትና ጌትነት ላይ እንዲታመኑ የሚሰጣቸው ሰማያዊ ስጦታ ነው::

## እምነት ማለት ምን ማለት ነው?

ቃለ እግዚአብሔር እምነት፣ «ኀይል ነው» አይልም:: ሰዎች እምነትን እንደ መሣሪያ በመጠቀም እውን ያልሆነውን ነገር እውን የሚያደርጉበት ወይም መንፈሳዊውን ቁሳዊ የሚያደርጉበት ነገር ነው የሚለው የእንቅስቃሴው መምህራን ትምህርት ለቃለ እግዚአብሔር ፍጹም ባዕድ ነው:: መምህራኑ ይህን ትምህርት በቃለ እግዚአብሔር ላይ ለማስደገፍ የሚጠቀሙባቸውን ሁለት የአዲስ ኪዳን ንባባትን እንቃኝ:: የእንቅስቃሴው መምህራን፣ እግዚአብሔር ለመፍጠር የተጠቀመበትን ቃል በማወጅ እውን ያልሆነውን ነገር እውን ማድረግ ይቻላል ለማለት አዝወትረው የሚጠቅሱት ጥቅስ «. . . ለሙታን ሕይወት በሚሰጥ የሌለውንም እንዳለ አድርጎ በሚጠራ. . .» የሚለውን ሮሜ 4÷17 ክፍል ነው:: ነገር ግን የሌለውን ነገር እውን ማድረግ የሚችለው አብርሃም ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር ነው:: አብርሃም በእግዚአብሔር ያመነበትም ዐይነተኛው ምክንያት፣ «ለሙታን ሕይወት ስለሚሰጥ፤ ያልነበረውንም እንደ ነበር ስለሚያደርግ ነው» (ቊ17):: የተስፋውን ቃል የሰጠው እንዲሁም የተስፋውን ቃል የፈጸመው ራሱ እግዚአብሔር ነው (4÷20-21)::

«ክርስቲያን ጤንነትንና ብልጽግናን በማመን ያመነውንም ነገር እውን ይሆንለት ዘንድ በማወጅ ያሻውን ነገር ያገኘዋል» ለሚለው የእንቅስቃሴው ትምህርት የሚጠቀሰው ጥቅስ ኤፌ 1÷3 ነው። ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ በክፍሉ ላይ የሚዘረዝራቸው በረከቶች ሁሉ ቁሳዊ ሳይሆኑ መንፈሳዊ ናቸው፦

1. የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችን (ቁ5)
2. በደሙ የተደረገውን ቤዛነታችንንና የኀጢአት ስርየት ማግኘታችን (ቁ7)
3. የፈቃዱን ምስጢር ማወቃችን (ቁ9)
4. የእግዚአብሔር ርስት ወራሽ መሆናችን (ቁ11)
5. በመንፈስ ቅዱስ መታተማችን (ቁ13)

እነዚህ በረከቶች ሁሉ መንፈሳዊ እንጂ ስለአካላዊ ጤንነት ወይም በገንዘብ ስለሚገኘው ብልጽግና የሚናገሩ አልያም መንፈሳዊው ነገር በእምነት ቁሳዊ መሆን እንደሚችል የሚገልጹ አይደሉም።

እምነት ቁሳዊ የሆነውን እውነታ የሚክድ አይደለም። ለምሳሌ የአብርሃምን ታሪክ ከሮሜ ምዕራፍ 4 እንመልከት። በክፍሉ አብርሃም የአካሉን ማርጀት እንዲሁም ልጅ ለመወለድ ዐቅም እንደ ሌላው ሲክድ አንመለከትም። ምውት የሆነውን የእርሱንና የባለቤቱን አካል ራሱ እግዚአብሔር በኪነ ጥበቡ ሕያው በማድረግ ልጅ እንደሚሰጣቸው አመነ እንጂ። ይህ የእምነት ሰው ሙት የሆነውን የእርሱንና የባለቤቱን አካል እየካደ ሲናገር አንመለከትም (ቁ19)።

የእንቅስቃሴ አስተማሪዎች፣ «የሚያየውን እንጂ የማይታየውን ባንመለከት. . .» (2ቆሮ 4÷18) የሚለውንም ጥቅስ አዘውትረው ይጠቅሱታል። ነገር ግን በክፍሉ ጳውሎስ እያለ ያለው ቁሳዊ እውነታዎችን እንካድ ሳይሆን፣ የሕይወታችን መሠረት ሊሆን የሚገባው የሚታየውና ጊዜያዊ የሆነው ነገር ሳይሆን፣ ዘላለማዊና ከሚታየው ነገር በላይ የሆነው ነገር መሆን አለበት ነው። እንዲያውም ሐዋርያው በክፍሉ «የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ. . .»(ቁ16) የሚለው ገለጻው ቁሳዊ እውነታን እንደማይክድ የሚገልጽ ነው። «የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ. . .» የሚለው ሐረግ የሚያሳየን አካላችን እንደሚሞትና እንደሚበሰብስ የሚያስረግጥ ነው። ለእንቅስቃሴው መምህራን ይህ ዐይነቱን የጳውሎስ ንግግር «አሉታዊ ዐዋጅ» በማለት ይጠሩታል። ጳውሎስ ግን ቁሳዊ እውነታን መናገር ነውር ነው አይልም። «. . . በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና. . .» (2ቆሮ 5÷7) የሚለው የጳውሎስ ንግግር «ማየትን» የሚቃወም አይደለም። ነገር ግን ሕይወት የሚመዘነው አሁን እየኖርንበት ባለው ሕይወት ስላልሆነ፣ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ተስፋ ካመን፣ ያለመሞትና በትንሣኤ ጊዜ የከበረ ሕይወት ባለቤቶች እንሆናለን (ቁ 1-8)።

እምነት ምክንያታዊነትን (አመክንዮን) ይቃወማል የሚለው አስተሳሰብ ስሕተት ነው። እምነት በፍጹም ኢምክንያታዊ አይደለም፤ ምክንያቱም እምነት ዓለማትን የፈጠረውና ዓለማትን በእውነት በሚያስተዳድረው አምላክ መተማመን ስለሆነ፤ እንዲሁም ትክክለኛው እምነት የዕውቀትና የመረዳት መጠናችንን ውሱኑነት ያገናዘበ ነው። «. . . በራስህም ማስተዋል አትደገፍ. . .» (ምሳ 3÷5) ማለት ኢምክንያታዊ ሁን ማለት

ሳይሆን፣ ሕይወትህን ለመምራት በራስህ ብቃት ስለሌለህ በእግዚአብሔር ዕውቀትና ፍርሀት ኑር ማለት ነው (ቊ 6-7)። እምነት የአሁን ጊዜ (Present tense) ጒዳይ ነው የሚለው የእንቅስቃሴው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። በእንግሊዝኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒሞች ላይ፣ የአሁን ጊዜን የሚያመለክቱ ግሶችና (is) ቃላት (Now) የተጠቀሙት ለሐሳብና ለዐረፍተ ነገር ሽግግር እንጂ የጊዜን ቅደም ተከተል ለማመልከት አይደለም፤ ለምሳሌ፦ 1ቆሮ 7÷1 ይመለከቷል። የአሁን ጊዜን የሚያመለክተው ረዳት ግስ (is) የእምነት ትንታኔ ለመግለጽ የገባ እንጂ ጊዜን ለማመልከት አይደለም።

ቃለ እግዚአብሔር እንደሚያስተምረን እምነት የዐላፊ፣ የአሁን እንዲሁም የመጪን ጊዜ እውነታ አቀናጅቶ የያዘ ነው። እምነት የአሁን ጊዜ እውነታ ስለሆነ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት የሚያሳይ ነው፤ ይኸውም እግዚአብሔር እንደሚወደን፣ ከእኛ ጋር እንደሚኖር ወዘተ (ሮሜ 15÷13)።

እምነት የዐላፊ ጊዜ እውነታንም ማዕከል ያደረገ ነው። ኢየሱስ እኛን ለማዳን የሞተውና ሞትን ድል አድርጎ የተነሣው ባለፉት ዓመታት ውስጥ ስለሆነ (ሮሜ 10÷9፤ 1ቆሮ 15÷1-11)። እምነት የመጪውንም ጊዜ እውነት ያማከለ ነው። ይኸውም በሕይወት ዘመናችን እውን ያልሆኑ ነገሮች፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ይፈጽምልናል የምንላቸው ቃል ኪዳኖች (ተስፋዎች) ሁሉ መጪውን ጊዜ የሚያመለክቱ ናቸው (ዕብ 11÷6)። ከብሉይ ኪዳን ቅዱሳንም የምንማረው ይህን ባሕርይ ነው (ሮሜ 6÷8፤ 2ጢሞ 1÷12)። ይህ የሚያሳየን እምነት መጪውንም ጊዜ የሚያመለክት እንደ ሆነ ነው (1ተሰ 4÷14)። እምነት እግዚአብሔር የሰጠንን ተስፋ እውን ያደርገዋል (ይፈጽመዋል) ብለን የምንታመንበት መሠረት እንጂ፣ አንድ ነገር የእኛ እንዲሆን የምናስገድድበት (የምናዝበት) መሣሪያ አይደለም። እምነት እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን መግቦት (Providence) ዛሬም ሆነ ወደፊት የምናረጋግጥበት ጒዳይ ነው።

## አወንታዊ ዐዋጅ

የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን ለአወንታዊ ዐዋጅ አበክረው ከሚጠቅሷቸው ጥቅሶች መኻል ሮሜ 10÷10 ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል፣ «ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና»። መምህራኑ ከዚህ ጥቅስ በመነሣት የተፈለገን ነገር ማግኘት የሚቻልበትን «ቀመር» ቀምረዋል፤ «ሕግን» ደንግገዋል። ነገር ግን የክፍሉ ዐውድ ይህን የሚደግፍ አይደለም። ዕብራውያን የብሉይ ኪዳንን ሕግ በመፈጸም ጽድቅ እንደሚገኝ ያምናሉ፤ በአፋቸውም ይመሰክራሉ፤ ነገር ግን ዕብራውያኑ ይህን በማድረጋቸው ትክክል አይደሉም (ሮሜ 9÷30፤ 10÷3)። ማመንና መመስከር ብቻውን ለውጥ አያመጣም። ከዐውዱ እንደምንመለከተው ጳውሎስ እመኑ፤ በአፋችሁም መስክሩ የሚለው፣ «ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ» እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው ነው። ከዚህ በመነሣት አጠቃላይ የሆነ ቀመር መቀመር፣ «ሕግን» መደንገግ ስሕተት ነው። ሌላው፣ «ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ፤ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው» እኛ ብናምን ወይም ባናምን፤ በአፋችን ብንመሰክር ወይም ባንመሰክር፣ እውነታውን እውነት ከመሆን የሚቀንሰው (የሚከለክለው) አንዳች ነገር የለም። ስለዚህ ኬኔት ሐጌንና መሰሎቻቸው፣

«አንድ ሰው ድኛለሁ ብሎ ካላወጀ በስተቀር፣ ደኅንነትን አያገኝም»[27] የሚለው ትምህርታቸው በቃለ እግዚአብሔር የተደገፈ አይደለም።

ከላይ እንደ ተመለከትነው «የምናገኛቸው ክፉም ሆኑ መልካም ነገሮች ሁሉ፣ በእምነት ተሞልተን በቃላት በምንገልጸው ነገር ይወሰናሉ» ለሚለው ትምህርት የእንቅስቃሴው መምህራን የሚጠቅሱት ሌላው ጥቅስ ማቴዎች 9÷29፣ «. . . እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ ብሎ ዐይኖቻቸውን ዳሰሰ» የሚለውን ነው። ነገር ግን ኢየሱስ እነዚህ ሰዎች ወደ እርሱ ሲመጡ፣ «ፈውስ እንዲሰጣቸው እንዲያምኑ፤ ተፈውሻለሁ ብለውም እንዲያውጁ» ሲያበረታታቸው፣ «እኔ የምፈውሳችሁ እምነት ሲኖራችሁ ብቻ ነው» ሲላቸው አንመለከትም። ይልቁንም፣«. . . ይህን ማድረግ እንድችል ታምናላችሁን?» (ቁ28) ብሎ ሲጠይቃቸው እንጂ፤ ይህ የሚያሳየን ዐይነ ስውሮቹ የተፈወሱት በእምነታቸው ሳይሆን በኢየሱስ ፈዋሽነት ነው። ኢየሱስ ሊፈውሳቸው እንደሚችል ማመናቸውን ተጠየቁ እንጂ፣ «ፈውስ የእኛ ነው» ብለው እንዲያውጁ አልተጠየቁም። ፈውስን ከኢየሱስ ለመቀበል እምነት አስፈላጊ ነው፤ ነገር ግን ለመፈወስ ብቸኛው ምክንያት እምነት አይደለም።

የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን አሉታዊ ዐዋጅ የሚሉትን አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ላይ ለማስደገፍ የሚጠቀሙባቸው ጥቅሶች፣ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ያለውን ኀይል ለመግለጽ የሚጠቀምባቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ቃል ኀይለኛ የሆነበት ምክንያት የእግዚአብሔር ስለሆነ (እግዚአብሔር ስለተናገረ) እንጂ (ሮሜ 4÷16-21) ቃላት በራሳቸው ኀይል ስላላቸው አይደለም። ዘማሪው፣ «እርሱ ተናግሮአልና ሆኑም፤ እርሱ አዘዘ፤ ጸኑም» (መዝ 33÷9) ያለበት ምክንያት «ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲፈራው፤ በዓለም የሚኖሩም ሁሉም ከእርሱ የተነሣ እንዲደነግጡ» (ቁ10-11) ነው። እንግዲያው ፍሬ ነገሩ እንዲህ ነው፦ እግዚአብሔር ያለው ወይም የተናገረው ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል፤ ሰዎች ያሉት ግን (በነሲብና ፤ ሁኔታውን በመገመት) ሊፈጸምም ላይፈጸም ይችላል። ዘማሪው «ሰብአውያን የሚናገሩት ቃል እውን እንዲሆን በእምነት ተሞልተው ይናገሩ» የሚል ምክር አይመክርም። ይልቁንም ዘማሪው እስራኤል አምላኪ የሆነውን እግዚአብሔርን እንድትፈራ፣ ምሕረቱንም ተስፋ እንድታደርግና ርዳታውንም እንድትሻ ይመክራል (ቁ 16-22)።

የቃለ እግዚአብሔርን ሥልጣን (ኀይል) በማስተማር ከሚታወቁት ክፍሎች መኻል ኢሳ 55÷11 አንዱ ነው «ከአፌ የሚወጣ ቃል እንዲሁ ይሆናል፤ የምሻውን ያደርጋል፤ የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም»። እግዚአብሔር እንዲህ ያለበት ምክንያት እስራኤል የተሐድሶ ዘመኗ የእግዚአብሔርን ምሕረት ለማግኘት ፊቷን ወደ አምላኳ እንድትመልስ ለመግለጽ ነው (ቁ 6-13)። ይህ የሚሆንበት ምክንያት፣ እግዚአብሔር ልዑል ስለሆነ መንገዱ ከሰብአውያን መንገድ ሰማይ ከምድር የሚርቀውን ያህል ስለሚርቅ እርሱ የሚለው ሁሉ እውነት እንደ ሆነ እርግጠኞች ነን (ቁ 8-9)።

27 Hagin, Understanding Our Confession ገጽ 4።

መጽሐፈ ምሳሌ ቃላት መንፈሳዊ ኀይል አላቸው የሚል ትምህርት አያስተምርም። እንዲያውም በርካታ የመጽሐፈ ምሳሌ ንባባት የሰብአውያን ቃላት በራሳቸው ኀይል እንደ ሌላቸው ያስተምራል (ምሳ 14÷23፤ 17÷10፤ 26÷23፡26፤ 29÷19)።

የእንቅስቃሴው መምህራን፣ የምንናገራቸው ማናቸውም ነገሮች የሕይወትም ሆነ የሞት ኀይል አላቸው፣ ለሚለው ትምህርታቸው የሚጠቅሱት ጥቅስ «በአፍህ ቃል ተጠመድህ፤ በአፍህ ቃል ተያዝህ» (ምሳ 6÷2) የሚለውን ነው። ነገር ግን ክፍሉ የሚያወራው ለጐረቤቶች ዋስ ሆኖ በዋሱ መሠረት ስለተያዘ ሰው ነው፤ «ልጄ ሆይ፤ ለጐረቤትህ ዋስ ብትሆን፣ ስለሌላ ሰው እጅህን አጋና ብትመታ በአፍህ ቃል ተጠመድህ፤ በአፍህ ቃል ተያዝህ» (ምሳ 6÷1-2)። ቃላት የሕይወትና የሞት ኀይል አላቸው ለሚለው ትምህርት የሚጠቀስ ሌላው ጥቅስ «ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ናቸው፤ የሚወድዱአትም ፍሬዋን ይበላሉ» (ምሳሌ 18÷21) የሚለው ክፍል ነው። ቃላት የሕይወትና የሞት ኀይል አላቸው የተባለው ቃላት የእምነትን ኀይል ስለሚያስተላልፉ ሳይሆን የምንናገረው ንግግር ጥሩም ሆነ መጥፎ ውጤት ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ነው፤ በዚህ ዐውድ የሰነፍ ንግግር ጸብን ስለሚጭር በዚህም የሰዎችን ሕይወት ስለሚቀጥፍ ነው (ቍ 6-7)።

ሰአወንታዊ ዐዋጅ የሚጠቀሰው ሌላው ጥቅስ ማቴዎስ 12÷36-37 ነው። በክፍሉ ኢየሱስ ፈሪሳውያን በንዝላልነት የሚናገሩትን ከንቱ ንግግር ሲነቅፍ ይታያል። የእንቅስቃሴው መሪዎች ከዚህ ጥቅስ በመነሣት አሉታዊ ዐዋጅ የሚያስከትለውን ጥፋት የሚገልጽ ቀመር ቀምረዋል፤ ይኸውም «ለምትመኘው ነገር ጠንቃቃ ሁን፤ ምክንያቱም የተመኘኸውን ነገር ድንገት ከተናገርኸው ታገኘዋለህና»። ነገር ግን በዚህ ክፍል ኢየሱስ ለማስተማር የፈለገው ነገር ፍጹም ከዚህ የተለየ ነው። ይኸውም ኢየሱስ ሲያወግዘው የነበረው ንግግር ፈሪሳውያን መንፈስ ቅዱስን (እግዚአብሔርን) የመሳደባቸውን ጉዳይ ነው (ቍ 31-32)። መንፈስ ቅዱስንም የመሳደባቸው ውጤት፣ በራሱ በእግዚአብሔር እንደሚፈረድባቸው ወይም እንደሚቀጡ እንጂ፣ አሉታዊ ነገር በመናገራቸው ምክንያት ብቻ፣ የተናገሩት ንግግር በራሱ አሉታዊ ውጤት ያመጣባቸዋል ማለት አይደለም። ለምንናገራቸው አወንታዊም ሆኑ አሉታዊ ንግግሮች ተጠያቂዎች መሆናችን እሙን ነው፤ የምንጠየቀውም የተናገርነውን ነገር የምናምንና የተናገርነውም ነገር እውን እንዲሆን የምንሠራ ከሆነ ነው።

እንደ እንቅስቃሴው መምህራን ትምህርት ከሆነ፣ «ጐስቋላና ምስኪንም ድኻም ዕውርም የተራቈትህም መሆንህን ስላማታውቅ. . .» (ራእ 3÷17) የሚለው ንግግር የሰይጣን ውሸት ነው ማለት ነው? በፍጹም አይደለም። የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያንማ፣ «ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ፤ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም የምትል. . .» ነበረች፤ ነገር ግን ይህን ማለቷ ያለችውን እንድትሆን አላደረጋትም። እንዲያውም እውነቱ ከተናገረችው ነገር ተቃራኒ ሆኖ ስለተገኘ ነው ራሱ ጌታ ጐስቋላ ነሽ፣ ምስኪን ነሽ ድኻ ነሽ፣ ዕውር ነሽ እንዲሁም የተራቈትሽ ነሽ የሚላት።

## ጸሎት

እግዚአብሔር የሰጠንን ነገር ስጠን ብሎ መጸለይ እንደማ ያስፈልግ፣ እንደ እንቅስቃሴው መምህራን ሁሉ እኛም እናምናለን። እግዚአብሔር ኀጢአታችን

እንዲዋጀን ልጁን ልኮልን ሳለ እንደገና ላክልን ብለን መጸለይ አያስፈልገንም፤ እንዲህ ዐይነቱ ጸሎት ስሕተት ነው (ሮሜ 9÷15-18፤ ያዕ 4÷6-10)።

የእንቅስቃሴው መምህራን በዮሐንስ 14÷3-14 እንዲሁም 15÷7 «ጠይቁ» የሚለው ቃል «ፈልጉ» የሚል ትርጒም አለው ማለታቸው ስሕተት ነው። በአማርኛቹም ሆነ ተአማኒነት ባላቸው የእንግሊዝኛ ቅጆች ላይ «ኤትዎ» የሚለው የግሪክ ቃል የተተረጐመው «ፈልጉ» ተብሎ ሳይሆን «ጠይቁ» ተብሎ ነው። ቃሉ የሚገኝበትን ሌላ ዐውድ ስንመለከት እውነቱ ይኸው ሆኖ ነው የምናገኘው (ሉቃ 23÷23፤ ሉቃ 23÷52፤ ማቴ 7÷7-11)። ኸረ ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር ቃሉን እንዲያከብር «እዘዙት» ይላልን?

እንደ እንቅስቃሴው አስተምህሮ፣ «ፈቃድህ ቢሆን» ብሎ መጸለይ ስሕተት ነው። ይህ ትምህርት ጒልሕ የሆኑ ሁለት ችግሮች አሉበት። አንደኛው ቃለ እግዚአብሔር «ፈቃድህ ቢሆን» ብለን መጸለይ እንዳለብን ያበረታታናል። ጌታ ስለ ጸሎት ባስተማረው ስፍራ (ማቴ 6÷10) «ፈቃድህ ይሁን» ብለን መጸለይ እንደሚገባን ገልጾልናል። ጌታ ራሱ በዚሁ መልክ ይጸልይ እንደ ነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል (ማቴ 6÷39)። ያዕቆብም «ብንኖር ጌታም ቢፈቅድ በሉ» ይለናል (ያዕ 4÷15)። ሐዋርያው ዮሐንስም፣ «በእርሱ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል» (1ዮሐ5÷14) ይላል። የሐዋርያው ጳውሎስም ጸሎት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማዕከል ያደረገ ነበር (ለምሳሌ ሮሜ1)። ሁለተኛው ቃለ እግዚአብሔር ከበሽታችን ሁሉ እንደምንድን ወይም የገንዘብ ችግር ሲያልፍ እንኳ እንደማይነካን ያስተምረናል? በማርቆስ 11÷24 ኢየሱስ፣ «የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ፤ ይሆንላችሁማል» ሲል፣ እምነት የምናምነውንና የምንናገራቸውን ማናቸውንም ነገሮች እውን የሚያደርግ ኀይል ነው ማለቱ ነው? በፍጹም አይደለም። በክፍሉ ትምህርት መሠረት ነገሮችን እውን የሚያደርገው ራሱ እግዚአብሔር እንጂ እኛ አይደለንም።

ቃለ እግዚአብሔር «በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል» (ዮሐ15÷7) ይለናል። «የምንወደው ነገር ሁሉ» ሊሆንልን የሚችለው እኛ በጌታ ስንኖርና ቃሎቹም በእኛ ሲኖሩ ነው፤ ይኸውም፦

1. ክፉ ባልሆነ ልብ (ምኞት) ጸሎታችንን ማቅረብ (ያዕ 4÷3)፣
2. ከሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነት ማስተካከል (1ጴጥ 3÷7) ፣
3. እንደ ፈቃዱም መጸለይ (1ዮሐ 5÷14)።

ይህን አሟልተን «የምንወደውን ነገር ሁሉ» እንዲሰጠን መጸለይ እንችላለን፤ ነገር ግን የሚሆንልን፣ ልዑል እግዚአብሔር «ይረባቸዋል ስለዚህም ይሁንላቸው» የሚለው ነገር ብቻ ነው። ምክንያቱም የሚያስፈልገንን ነገር እርሱ ያውቃልና። *እኛ እግዚአብሔርን ልናስገድደው የምንችል ትናንሽ አማልክት ሳንሆን በሚያስፈልገን ነገር ሁሉ በእርሱ ላይ የምንደገፍ፣ ጸሎታችን ያልተሰማ በመሰለን ጊዜ እንኳ በእርሱ የምንታመን የእግዚአብሔር ትንንሽ ልጆቹ ነን፡፡*

## ማጠቃለያ

የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን በእምነት፣ አወንታዊ ዐዋጅንና ጸሎትን በተመለከተ ያላቸው ትምህርት በግማሽ እውነት ላይ መሠረት ያደረገ ነው። በእግዚአብሔር የምንታመን ከሆነ እግዚአብሔር አስደናቂ ነገር እንደሚያደርግ እሙን ነው፤ ነገር ግን እኛ በእርሱ በመታመናችን እግዚአብሔር ተገዶ ተአምራትን ያደርጋል የሚለው ትምህርት ስሕተት ነው። አወንታዊ በሆነ ሁኔታ ማሰብና መናገር ትክክል ነው፤ ነገር ግን አወንታዊ ዐዋጅ፣ አወንታዊ ውጤት ሲኖረው፣ አሉታዊ ዐዋጅ ደግሞ አሉታዊ ውጤት ሊያስከትል የሚችል ዘላለማዊ የሆነ መንፈሳዊ ሕግ አለ ማለት ደግሞ ስሕተት ነው። እግዚአብሔር እንዲባርከን በሙሉ ልብ መጸለይ አለብን፤ ነገር ግን እግዚአብሔር የምንጠይቀውን ነገር እንዲያደርግልን «ማዘዝ» አንችልም፤ ልናደርገውም አይገባም። ይህ ዐይነቱ ጸሎት ትሑት ሆነን በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ታምነን ጸሎታችንን እንዳናቀርብ ይከለክለናል። ምን ያህል ሰዎች በእምነት እንቅስቃሴ መምህራን የጸሎት ቀመር «ያዘዙት ትእዛዝ» አልሞላ ብሎ ከዚህ የተነሣ በእግዚአብሔርና በቃሉ ላይ ያላቸው እምነት ተናግቶ ይሆን?

# እግዚአብሔር እምነት አለውን?

## ምዕራፍ ሰባት

በነገረ መለኮት ውስጥ ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዘው ትምህርት አስተምህሮተ እግዚአብሔር ነው። የእምነታችን ብቸኛ መሠረት እግዚአብሔር እስከ ሆነ ድረስ፣ በእርሱ ማንነትና ሥራ ላይ ያለን እምነት «ሃይማኖታዊ አስተምህሮአችን ርቱዕ ነው ወይስ ኑፋቄ» የሚለውን ጉዳይ ይወስነዋል። የእምነት እንቅስቃሴ አስተምህሮ ሰንካላነት ከዚህ ይጀምራል።

እንደ እንቅስቃሴው ትምህርት እግዚአብሔር የሚሠራውን ሥራ ሁሉ የሚሠራው በእምነት ነው፤ ሥራውም (ፈቃዱም) እውን እንዲሆን የእምነት ቃል ይናገራል። ልክ እንደዚሁ እኛም «የእምነት ቃል» በመናገር የምንሻውን ነገር ማግኘት እንችላለን።

## የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን ምን ይላሉ?

እግዚአብሔር እምነት አለው፤ አንድ ነገር መሥራት የሚፈልግ ከሆነ የእምነት ቃል መናገር አለበት፣ የሚለው የእንቅስቃሴው አስተምህሮ ብዙዎቻችንን ሊያስደንቀን ይችላል፤ ነገር ግን የእንቅስቃሴው ትምህርት መሠረት ካደረገባቸው አስተምህሮዎች መኻል ይህ አንዱ ነው።

ለምሳሌ የእንቅስቃሴው አንጋፋ መምህር እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፣ «እምነት በሰው ውስጥ ያለ ፈጣሪ ኀይል ነው፤ እምነት በፈጣሪ ውስጥ ያለ ፈጣሪ ኀይል ነው፤ እግዚአብሔር የሚናገረው ቃል 'ይሁን' የሚለው ነው»[1] ልክ እንደዚሁ ኬኔት ሐጌንም፣

---

[1] Kenyon, Two Kinds of Knowledge, ገጽ 14-15፤ እንዲሁም Kenyon, The Bible in the Light of our Redemption ገጽ 15

«እንደ እግዚአብሔር ዐይነቱ እምነት. . . ነው በመናገር ዓለምን የፈጠረው. . . እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው በቃላት ነው፡፡ በየትኛውም ዓለም እምነት እንደሞላባቸው ቃላት ኀይለኛ ነገር የለም»[2]፡፡

ኬኔት ኮፐላንድ ደግሞ፣ «እግዚአብሔር እምነት ያለው አካል ነው. . . እግዚአብሔር ያለ እምነት ምንም ነገር ሊሠራ አይችልም»[3]፡፡ «መንፈሳዊው ሕግ ነው ቁሳዊውን ሕግ የሚፈጠረው፡፡ ዓለምም ሆነ ዓለምን የሚያስተዳድረው ቁሳዊው ኀይል የሚፈጠረው በእምነት ኀይል ነው፤ ይህም መንፈሳዊ ሕግ ነው፡፡ መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የፈጠረው በእምነት ኀይል ነው. . . እምነት መንፈሳዊ ኀይል ነው፤ መንፈሳዊ ጉልበት ነው፤ መንፈሳዊ ዐቅም ነው፡፡ መንፈሳዊው ዓለም ሥራውን የሚያከናውነው በዚህ የእምነት ኀይል ነው»[4]፡፡

ቻርለስ ካፐስ የተባሉትም የእምነት እንቅስቃሴ መምህር ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አስተምህሮ አላቸው፣ «እግዚአብሔር እምነት አለው እግዚአብሔር እምነቱን የሚያወጣው (የሚያሳየው) በቃላት ነው. . . እግዚአብሔር እምነቱን የሚያወጣው (የሚያሳየው) በቃላት ነው»[5]፡፡

እነዚህ ሁሉ የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን ለዚህ ትምህርታቸው መደገፊያ ያሚያደርጉት ማርቆስ 11÷22 «. . . በእግዚአብሔር እመኑ» የሚለውን ክፍል ነው፡፡ እንደ እነዚህ ግለሰቦች ትምህርት፣ «በእግዚአብሔር እመኑ» የሚለው የእንግሊዝኛም ሆነ አቻ ትርጒም ያለው የአማርኛው ቅጅ ከግሪኩ (ከበኲረ ጽሑፉ) በትክክል አልተተረጐመም፡፡ የክፍሉ ትክክልኛ ትርጒም፣ «የእግዚአብሔር ዐይነት እምነት ይኑርህ» ነው የሚለው፡፡ ፍሪድ ፕራይስ የተባሉት የእንቅስቃሴው መምህር ይህን በተመለከተ ሲናገሩ፣ «የእምነት ዐይነቶችን መክፈል (መለየት) ያስፈለገበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ ታውቃላችሁ? ምክንያቱ በዓለማችን ሁለት ዐይነት እምነቶች ስላሉ ነው፡፡ አንደኛው ተፈጥሮአዊ የሆነው ሰብአዊ እምነት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ መንፈሳዊ የሆነው እምነት ወይም የእግዚአብሔር ዐይነቱ እምነት ነው»[6]፡፡ ፍሪድ ፕራይስ ዕብራውያን 11÷3 አስመልክቶ እንዲህ ይላሉ፡- «እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠ ረው እኛ ያመንበት ዐይነት እምነት እየተናገረ ብቻ አይደለም፡፡ ልክ ነው ክፍሉ እንደዚያ ይላል፤ ነገር ግን የክፍሉ ትምህርት ከዚህም በላይ ነው፡፡ እግዚአብሔር [ዓለምን] እንዴት እንዳበጀም ጭምር እንጂ!. . . እግዚአብሔር በልቡ የሚያምነውን ነገር በአፉ የሚናገረው ነገሩ እውን እንዲሆን ነው፤ ስለዚህም ይናገራል. . . አባታችን እምነት ያለው አምላክ ከሆነ፣ እምነት ላለው አምላክ እምነት ያላቸው ልጆች ልንሆን ይገባል»[7]፡፡

የእምነት እንቅስቃሴ አራማጆች፣ እግዚአብሔር እምነት ያለው አምላክ ነው የሚለውን ትምህርታቸውን በቃለ እግዚአብሔር ለመመዘን ለሚከተሉት ሦስት ጥያቄዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ ማግኘት ያስፈልጋል፡- (1) ማርቆስ 11÷22 የእግዚአብሔር ዐይነት

---

[2] Hagin New Thresholds of Faith,ገጽ 74-76፡፡ ዝኒ ከማሁ ጠቅሶ እንደ ጻፈው፡፡

[3] Kenneth Copeland, The Laws of prosperity ገጽ 18-19 ዝኒ ከማሁ ጠቅሶ እንደ ጻፈው፡፡

[4] Charles Capps, God's Creative Power, ገጽ 2፡25 እንዲሁም Capps, Authroity in Three Worlds, ገጽ 24-25 ዝኒ ከማሁ ጠቅሶ እንደ ጻፈው፡፡

[5] Frederick K.C.Price, How Faith Works, ገጽ 93 ዝኒ ከማሁ ጠቅሶ እንደ ጻፈው፡፡

[6] ዝኒ ከማሁ፡፡

[7] ዝኒ ከማሁ ገጽ 99፡101፡፡ በቅንፍ ያለውን አይጨምርም፡፡

እምነት እንዲኖረን ያስተምረናል? (2) ዕብራውያን 11÷3 እግዚአብሔር ዓለማትን ለመፍጠር እምነቱን (አለው የተባለውን) ተጠቅሞአልን? (3) እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚፈጽመው ቃል እየተናገረ ብቻ ነው?

## እግዚአብሔር እምነት አለውን?

ማርቆስ 11÷22 ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን፣ «. . . በእግዚአብሔር እመኑ» ነው ያላቸው ወይስ፣ «የእግዚአብሔር ዐይነቱ እምነት ይኑራችሁ» ነው ያላቸው? ሁሉም የአማርኛና የእንግሊዝኛ ትርጒሞች ክፍሉን የተረጐሙት፣ «. . . በእግዚአብሔር እመኑ» ብለው እንጂ እንደ እንቅስቃሴው መምህራን የእግዚአብሔር ዐይነቱ እምነት ይኑራችሁ ብለው አይደለም፤ ችግሩ ያለው የእንቅስቃሴው መምህራን ዘንድ ነው ወይስ በእጃችን የሚገኙት የአማርኛና የእንግሊዝኛ ቅጆች? ይህን ጥያቄ ለመመለስ የግሪኩን ሰዋስው መመርመር ስለሚያስፈልግ ወደዚያው እንዝለቅ፡-

የአማርኛ ትርጒሞችንም ሆነ የእንግሊዝኛ ትርጒሞችን የተረጐሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓምያን፣«. . . በእግዚአብሔር እመኑ» ብለው የተረጐሙት ቃል ግሪኩ፣ «. . . ኤክተ: ፒስቲን ቴው» ይለዋል። ፕሬ ትርጒሙም፣ «ይኑራችሁ እምነት እግዚአብሔር» የሚል ነው።

የክርክሩ ማዕከል የሆነው፣ «ቴው» («እግዚአብሔር») የሚለው ቃል ስለሆነ የትኩረት አቅጣጫችንን ወደዚያው እናድርግ። «ቴው» («እግዚአብሔር») የሚለው ቃል በሰዋስው፣ «ዘርፍ ሙያ»[8] (Genitive case) በመባል ይታወቃል። «ቴው» (እግዚአብሔር) የሚለው ቃል አወቃቀር፣ «የባለቤት ዘርፍ» (Subjective Genitive) ከሆነ ማለትም የክፍሉ ባለቤት የሆነውን «ቴው» የሚገልጽ ከሆነ የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት፣ «ቴው» («እግዚአብሔር») ስለሆነ የእምነት የሚኖረው እግዚአብሔር ይሆናል፤ ስለዚህም፣ «እግዚአብሔር ያለው እምነት» ተብሎ ይተረጐማል ማለት ነው። ይህ ደግሞ የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን እያሉት ያለው መሆኑ ነው።

ነገር ግን ከክፍሉ አወቃቀር የምንማረው፣ «ቴው» የሚለው ቃል፣ «የተሳቢ ዘርፍ» ነው። ስለዚህም ቃሉ የሚናገረው ስለ ዐረፍተ ነገሩ ባለቤት (ማለትም ስለ እግዚአብሔር) ሳይሆን ስለ ተሳቢው (object) (ማለት እምነቱ ይኑራችሁ ስለተባሉት ሰዎች) የሚናገር ይሆናል። በዚህ ሰዋስዋዊ ትንታኔ የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር እምነት ለሚለው ቃል ተሳቢ እንጂ ባለቤት አይደለም።

ስለዚህ ክፍሉ መተርጐም ያለበት፣ «በእግዚአብሔር እመኑ» ተብሎ እንጂ፣ «እንደ እግዚአብሔር ዐይነት እምነት ይኑራችሁ» ተብሎ አይደለም። ሰዋስውን የዚህን ያህል ካየን በቂ ስለሚሆን አገባቡንና (usage) ዐውደ ምንባቡን ደግሞ በአጭሩ እንመልከት። ከአገባብ እንጀምር፡- በአዲስ ኪዳን ግሪክ፣ «እምነት» (በግሪኩ «ፒስቲስ» የሚለው ቃል ዘርፍ የሆነ ስም) (Genitive noun) ሲከተለው አብዛኛውን ጊዜ ዘርፉ፣ የተሳቢ ዘርፍ ይሆናል።

---

[8] ዘርፍ ሙያ (Genitive Case) ማለት ስሞች ወይም ስሞችን መስለው የሚገኙ ቃላት በዐረፍተ ነገር ውስጥ ተገጣጥመው በተነገሩ ጊዜ የቃሉን ንብረት የምናውቅበት ክፍል ሙያ ይባላል። በግሪክ ቋንቋ ሙያ የባለቤት ዘርፍ [Subjective Genitive] እና የተሳቢ ዘርፍ [Objective Genitive] በመባል ለሁለት ይከፈላል።

ለአብነት ያህል ጥቂት እንመልከት፡- «እምነት በስሙ» (ሐሥ 3÷16) ማለት፣ «በስሙ ላይ መሠረት ያደረገ እምነት» ማለት እንጂ፣ «ስሙ ያለው እምነት ማለት» አይደለም። እምነት በእውነት» (2ተሰ 2÷13) «በእውነት ላይ መሠረት ያደረገ እምነት» ማለት እንጂ፣ «በእምነት ላይ መሠረት ያደረገ እውነት» ማለት አይደለም። «ወንጌል በእምነት» (ፊል 1÷27) ማለት፣ «በወንጌል ላይ መሠረት ያደረገ እምነት» ማለት እንጂ በእምነት ላይ መሠረት ያደረገ ወንጌል ማለት አይደለም። እናት ቋንቋ ለሆነው ለግሪኩ ሰዋስዋዊ አወቃቀር እንዲሁም ለዐውደ ምንባብ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒሞች ክፍሉን እንዴት እንደ ተረጐሙት ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጆች ይመልከቱ።

እንደ ሰዋስው ሁሉ ዐውደ ምንባቡም ከላይ ያየነውን እውነት («የተሳቢ ዘርፍ») ፍንትው አድርጐ የሚያሳይ ነው። በክፍሉ የምናነበው ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በሚጸልዩበት ጊዜ እምነት እንዲኖራቸው ነው (ቊ 24)። ስለዚህ የክፍሉ ባለቤት እነርሱ እንጂ እግዚአብሔር አይደለም። በተጨማሪም በክፍሉ ውስጥ ኢየሱስ፣ እግዚአብሔር ራሱ እምነት ያለው አምላክ ነው የሚል ትምህርት (ፍንጭ) አልሰጠም።

በአጠቃላይ ከማርቆስ 11÷22 የምንማረው ትምህርት እግዚአብሔር የእምነታችን ማዕከል እንደ ሆነ ነው እንጂ፣ እግዚአብሔር ያለውና ፈቃዱን እውን ለማድረግ የሚጠቀቡበትን ዐይነት እምነት ይኑራችሁ የሚል አይደለም።

## እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው በእምነት ነውን?

ማርቆስ 11÷22 አንብበን፣ «በእግዚአብሔር እመኑ» የሚለውን ትምህርት እንጂ፣ «የእግዚአብሔር ዐይነት እምነት ይኑራችሁ» የሚለውን እንደማንረዳ ሁሉ፣ ዕብራውያን 11÷3 አንብበን፣ «ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ. . . በእምነት እናስተውላለን» የሚለውን እንጂ፣ «እግዚአብሔር ዓለማትን የፈጠረው እምነቱን በመጠቀም ነው» የሚል ግንዛቤ ሊኖረን አይችልም። ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጆች የምንማረውም ይህንኑ እውነት ነው። የእንቅስቃሴው መምህራን ክፍሉን የሚረዱት፣ «እግዚአብሔር ዓለማትን የፈጠረው እምነቱን በመጠቀም ነው» ብለው ነው።

የእነዚህን ሁለት ትርጒሞች ቅራኔ የሚፈታው የዐረፍተ ነገሩን ሰዋስዋዊ አወቃቀር፣ በተለይ የቃላት አሰካኩን (Syntax) በመመርመር ነው። የነገረ መለኮት ምሁራንም ሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓምያን ክፍሉን የተረጐሙት፣ «ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ. . . *በእምነት* እናስተውላለን» ብለው ነው። የእንቅስቃሴው መምህራን ደግሞ፣ «ዓለሞች *በእምነት* በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ. . . እናስተውላለን» ብለው ነው። ነገሩን ግልጽ ለማድርግ የዐረፍተ ነገሮቹን አወቃቀር በሥዕል እንመልከት።

### የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓምያን



እግዚአብሔር ቃለ በእምነት

- ከዚህ አወቃቀር የምንመለከተው ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ፣ እኛም ይህን እውነት የመንረዳው በእምነት መሆኑን ነው።

## የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን

ዓለማት እንደ ተዘጋጁ እናስተውላለን
በእምነት በእግዚአብሔር ቃል

- ከዚህ አወቃቀር የምንመለከተው ደግሞ ዓለሞች በእምነት በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ እንረዳለን የሚለውን ነው።

ግሪክኛውን ቃል በቃል (በቁሙ) ስንተረጉመው፣ «በእምነት እንረዳለን እንደ ተፈጠሩ ዓለማት በእግዚአብሔር ቃል» የሚል ትርጉም ይዞ እናገኘዋለን።

ከዐረፍተ ነገር አሰካኩ በተጨማሪ እንዲያውም ከአወቃቀሩ በተሻለ ሁኔታ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓምያንን የዐረፍተ ነገር አሰካክ እንድንከተል የሚያደርጉን በርካታ ማስረጃዎች አሉ። እነዚህም፦

1. ክፍሉ የሚገኝበት ምዕራፍ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ስላላቸው እምነት እንጂ እግዚአብሔር ስላለው እምነት አይናገርም፣ «አቤል. . . በእምነት አቀረበ. . . ሄኖክ. . . በእምነት ተወሰደ. . . ኖኅ. . . በእምነት አዘጋጀ. . . አብርሃም. . . በእምነት ታዘዘ. . . ሣራ. . . በእምነት አገኘች. . . እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ. . . » (ዕብ 11÷4፡5፡7፡8፡11፡13)።

በምዕራፉ፣ «እምነት» የሚለው ቃል ዐሥራ ዘጠኝ ጊዜ (19) የተጠቀሰ ሲሆን፣ ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት ለማሳየት ነው (ዕብ 11÷3-5፡ 7-9፡ 11፡ 17፡ 20-24፡ 27-31፡ 33)። የእነዚህ የእምነት ሰዎች እምነት ማዕከል ያደረገው እግዚአብሔር አለ፤ እንዲሁም ከልብ የሚሹትን ይክሳቸዋል በሚለው እውነት ላይ ነው (ቁ 6)።

ከምዕራፉ የምንማረው ነገር ሰዎች በፈጣሪያቸው በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት እንጂ፣ አምላክ ፈጣሪ እንዲሆን ያስቻለውን እምነት አይደለም።

2. የምዕራፉ መግቢያ የሆነውና አሁን እየተነጋገርንበት ካለው ጥቅስ ሁለት ዐረፍተ ነገር ከፍ ብለን የምናገኘው ዐረፍተ ነገር፣«እምነት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው» (ቁ1) ይላል። ከዚህ ዐረፍተ ነገር የምንረዳው እምነትና ተስፋ እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሄዱ ነገሮች እንደ ሆኑ ነው። እግዚአብሔር እምነት አለው ካልን ተስፋም አለው ማለታችን የግድ ነው። ኸረ ለመሆኑ ለእግዚአብሔር ተስፋ የሚሰጠው፣ እግዚአብሔርም

ተስፋውን የሚጥልበት ማነው? እግዚአብሔር ተስፋ ሲያደርገው የቆየውን ነገር ነው በእምነት እውን የሚያደርገው? በርግጥ ቃለ እግዚአብሔር ይህ ዐይነቱን ትምህርት ያስተምረናል? መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር «የተስፋ አምላክ» (ሮሜ 15÷13) ነው ሲል፣ እግዚአብሔር ተስፋ የሚያደርገው ነገር አለው ማለት ሳይሆን፣ እርሱ ብቻ የተስፋ ምንጭ እንደ ሆነ፣ የሰጠውንም ተስፋ እውን እንደሚያደርግ የሚያስተምር ነው።

# ማጠቃለያ

የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን ማርቆስ 11÷22 እንዲሁም ዕብራውያን 11÷3 በመጥቀስ እግዚአብሔር እምነት አለው፤ ዕቅዱንም እውን የሚያደርገው ወይም ፍጥረታትን የሚፈጥረው በእምነት ተሞልቶ በሚናገረው ቃል ነው የሚለው ትምህርታቸው የክፍሉን ትክክለኛ

ትርጒም መሠረት ያደረገ አይደለም። ይህ ትምህርት ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለቃል እግዚአብሔር ባዕድ ነው። እግዚአብሔር እምነት ከሌለው፣ «የእግዚአብሔር ዐይነት እምነት ይኑራችሁ» የሚለው የእንቅስቃሴው ትምህርት በርግጥ ድርሳነ ፈጠራ ነው!

## እግዚአብሔር ለመፍጠር<br>ቃላትን የግድ መጠቀም አለበትን?

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ዓለማትን እንደ ፈጠረ፣ ፈቃድንም እውን ያደረገው በቃሉ እንደ ሆነ ያስተምረናል። ዕብራውያን 11÷3 ዓለማት በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተፈጠሩ ይገልጻል። ዘፍጥረት 1 «እግዚአብሔርም አለ. . . ይሁን» በሚለው ቃሉ ዓለማትን እንደ ፈጠረ ያስተምራል። የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን እንዚህና እንዚህን መሰል ጥቅሶች በመጥቀስ እግዚአብሔር የመፍጠርን ሥራ የሚሠራው «የእምነትን ቃል» («እምነት የሞላባቸውን ቃላት») በመናገር ነው። እኛም በእግዚአብሔር መልክ ከተፈጠርን የምንሻውን ነገር ማግኘት የምንችለው «እምነት የሞላቸውን ቃላት» በመናገር ነው።

የእንቅስቃሴው መምህራን ያልተረዱት ነገር ቢኖር የእግዚአብሔር ቃል ሲባል ፈቃዱን ወይም ሐሳቡን ለመግለጽ በቈሳዊ ጆሮ የሚሰማ ድምፅ ይናገራል ማለት አይደለም። (በጆሮ የሚሰማ ድምፅ ለመፍጠር አየር ያስፈልጋል፤ አየር ከሌለ እርግብግቢት የለም፤ እርግብግቢት ደግሞ ከሌለ ድምፅ የለም፤ ታዲያ እግዚአብሔር አየርን ከመፍጠሩ በፊት የነበረውን ዓለም እንዴት ፈጠረው ሊባል ነው?)።

ቃለ እግዚአብሔርም፣ እግዚአብሔር ለመፍጠር ድምፅ ይጠቀማል አይልም።

> «ድምፁን ባሰማ ጊዜ ውሆች በሰማይ ይሰበሰባሉ፤ ከምድርም ዳር ደመናትን ከፍ ያደርጋል፤ ለዝናብም መብረቅን ያደርጋል፤ ነፋስንም ከቤተ መዛግብቱ ያወጣል» (ኤር 10÷13)

ኤርምያስ እግዚአብሔር በቀጥታ ነፋስን የሚያከማችበት ቤተ መዛግብት አለው እያለ ነውን? እግዚአብሔር ውሆችን ለመሰብሰብ በቀጥታ ድምፁን ያሰማል ማለት

ነውን? አይደለም ነገር ግን ተምሳሌታዊ አነጋገር እንጂ! የሚከተለውን ክፍል ደግሞ ይመልከቱ፡-

«ሰማየ ሰማያት አመስግኑት፤
የሰማየት በላይም ውሃ፡፡
እርሱ ብሎአልና ሆኑም፤
እርሱ አዝዞአልና ተፈጠሩም፤
የእግዚአብሔርን ስም ያመሰግኑት፡፡
ለዘላለም ዓለም አቆማቸው፤
ትእዛዝን ሰጠ አያልፍምም፡፡
እባቦች ጥልቆችም ሁሉ፤
እግዚአብሔርን ከምድር አመሰግኑት
እሳትና በረዶ አመዳይና ውርጭ፣
ቃሉን የሚያደርግ ዐውሎ ነፋስም፤»
(መዝ 148÷3-8)

በክፍሉ ላይ የተጠቀሱት ግዑዛን ፍጥረታት ማለትም፣ ፀሓይ፣ ጨረቃ ከዋክብት ወዘተ ቃል በቃል እግዚአብሔርን «ተመስገን» ብለው ያመሰግኑታል ማለት ነው? አይደለም! ነገር ግን ቃላት ሳይተነፍሱ ምስጋናውን ያውጃሉ፤ ፈጣሪያቸውን ያስተዋውቃሉ ማለት ነው (መዝ 19÷1-3)፡፡ ልክ እንደዚሁ እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚፈጽመው ወይም ፍጥረታትን የሚፈጥረው በጆሮ የሚሰማ ድምፅ እየተናገረ አይደለም! ግዑዛን ፍጥረታትም ይሁን በጆሮ የሚሰማ ድምፅ እየሰሙ ነው አእምሮ እንዳላቸው ፍጥረታት ለድምፀ (ለቃሉ) የሚታዘዙት? በፍጹም አይደለም!

የእንቅስቃሴው መምህራን ፈቃዱን እውን የሚያደርገው በጆሮ የሚሰማ ድምፅ እየተናገረ ነው ለሚለው ትምህርታቸው አዝወትረው የሚጠቅሱት ጥቅስ መዝ 33÷6-9 ነው፡፡ እንግዲያው ክፍሉን ቃል በቃል ከተረጎምነው እግዚአብሔር ውሆችን፣ ንፋሳትን ወዘተ የሚያከማችበት ቁሳዊ ግምጃ ቤት አለው ማለት ነው? አጀብ! በእርግጥ እግዚአብሔር ቁሳዊ አፍና ትንፋሽ አለው?

ይህ ሲባል ግን እግዚአብሔር ፈቃዱን ለመግለጽ በጆሮ የሚሰማ ድምፅ ሊናገር አይችልም ማለት አይደለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በጆሮ የሚሰማ ድምፅ የተናገራቸው ሰዎች እንዳሉ ይነግረናል፡፡ እነዚህን ክፍሎች በቀጥታ የማንተረጉምበት ምንም ምክንያት አይኖረንም፡፡ እግዚአብሔር ከመላእክትም ጋር ይሁን ከመንፈሳዊው ዓለም ጋር የሚግባባበት ቋንቋ የለውም ማለትም አይደለም፡፡ ነገር ግን እያልን ያለነው እግዚአብሔር አንድን ነገር ለመፍጠር ወይም ለማከናወን የግድ ቃል መናገር የለበትም እያለን ነው፡፡

በእንቅስቃሴው ትምህርት መሠረት አንድ ሰው በልቡ የሚያምነውን በቃላት ካልገለጸ እምነቱ ከንቱ ነው፤ የፈለገውንም ነገር አያገኝም፡፡ ይህም ሰዎችን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርንም ይመለከታል፡፡

እንደ ቃለ እግዚአብሔር ትምህርት ግን እግዚአብሔር እምነት ያለውም፤ ፈቃዱንም እውን ለማድረግ የግድ ቃላትን መናገር አያስፈልገውም፡፡

# ጤንነትና ብልጽግና

## ምዕራፍ ስምንት

የእምነት እንቅስቃሴ በስፋት የሚታወቀው፣ «ጤንነትና ብልጽግና» በሚለው አስተምህሮው ነው። በዚህ ምዕራፍ ለማየት የምንሞክረው፣ እንቅስቃሴው ጤንነትና ብልጽግናን አስመልክቶ የሚያስተምረውን ትምህርት ነው።

## ጤንነትና ብልጽግና እንደ እምነት እንቅስቃሴ አስተምህሮ

እንቅስቃሴው ፈውስን እንዲሁም ቁሳዊ ብልጽግናን አስመልክቶ የሚያስተምረው ትምህርት በአምስት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ መሠረት ያደረገ ስለሆነ፣ እነዚህን ነጥቦች እንመልከት፡-

### የአወንታዊ ዐዋጅ ኀይል

እንቅስቃሴው አካላዊ ጤንነትንና ቁሳዊ ብልጽግናን የሚያስተ ምረው፣ «እምነትና አወንታዊ ዐዋጅ» በሚለው መሠረት ላይ ነው። እንደ እንቅስቃሴው አስተምህሮ፣ «በእምነት የተሞሉ ቃላት» ማንኛውንም ነገር የማድረግ ወይም የመፍጠር ታላቅ ችሎታ ስላላቸው፣ አካላዊ ጤንነትንም ሆነ ቁሳዊ ብልጽግናን የሚፈልግ ሰው፣ «በእምነት የተሞሉ አወንታዊ ዐዋጆችን በማወጅ» ያሻውን ነገር ማግኘት ይችላል።

እንቅስቃሴው «እምነትና አወንታዊ ዐዋጅ» በሚል፣ የሚያስ ተምረውን ትምህርት ከዚህ በፊት በስፋት ተመልክተነዋል። እግዚአብሔር ፍጥረታትን የሚፈጥረው የእምነት ቃል በመናገር አይደለም። ቀና ነገር ማሰብ ከብዙ ጐኑ መልካም ቢሆንም፣ አወንታዊ ንግግሮችን በመናገር ያሻነውን ነገር ሁሉ ማግኘት እንችላለን የሚለው ትምህርት ግን፣ በቃለ እግዚአብሔር የተደገፈ አይደለም።

## ከርግማን ዐርነት መውጣት

እንቅስቃሴው የሚያስተምረውን የጤንነትና የብልጽግና አስተ ምህሮ ለማጽናት መሠረት የሚያደርግበት ሁለተኛው ነጥብ፣ «ኢየሱስ ክርስቶስ የሕግን መርገም ከላያችን ላይ አንሥቶልናል» የሚለው ትምህርቱ ነው። ኬኔት ሐጌን ገላትያ 3፥13 አስመልክተው እንዲህ ይላሉ፡- «የሕግ ርግማን ማለት ምን ማለት ነው? ይህን ነገር መረዳት የምንችለው፣ ሕግ ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን ነገር መመርመር ስንችል ብቻ ነው። በአዲስ ኪዳን፣ 'ሕግ' በመባል የሚታወቁት የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያዎቹ አምስት መጻሕፍት የሆኑት የሙሴ መጻሕፍት ናቸው። ወደ እነዚህ መጻሕፍት (ሕግጋት) ስንሄድ የምናገኘው ነገር የእግዚአብሔርን ሕግ ማፍረስ ሦስት ዐይነት ቅጣቶችን ወይም ርግማኖችን ማስከተሉን ነው፤ እነዚህም፡- ድኽነት፣ በሽታና መንፈሳዊ ሞት ናቸው»[1]

ከሕግ ርግማን ዐርነት የወጣን ሰዎች ከሆንን፣ በአንጻሩ ደግሞ እነዚህ ርግማኖች በሽታንና ድኽነትን የሚያካትቱ ከሆኑ ከድኽነትና ከርግማን ዐርነት የማንወጣበት

---

[1] Hagin, Redeemed: From Poverty, Sickness, Death, 2ded., ገጽ 1።

አንዳችም ምክንያት የለም:: ይህን ትምህርት ለማጽናት ከብሉይ ኪዳን ከሚጠቀሱት ጥቅሶች መኻል ዘዳግም 28 አንዱ ነው:: ዘዳግም 28 አስመልክቶ ሌላው የእንቅስቃሴው መምህር፣ ኬኔት ኮፕላንድ እንዲህ ይላሉ፣ «በዘዳግም 28 የተጠቀሱትን ጥቅሶች ታስታውሳለህ? የተለያዩ ዐይነት ድኽነቶች፣ ፖለቲካዊ ውድቀቶች፣ ድርቅ፣ ጦርነት እንዲሁም በሰው ልጆች ላይ የሚመጡ የተለያዩ ዐይነት ጥፋቶች ናቸው:: ኢየሱስ ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ ዐርነት አውጥቶናል:: በሽታዎች ሁሉ፣ በሽታ አምጪ ተዋሕስያን ሁሉ እንዲሁም በዚያ ክፍል ያልተጠቀሱ ነገሮች ሁሉ ተረግመዋል:: ስለዚህ የመዋሸትንና የመስረቅን ፈተና እንደምትዋጉት ሁሉ የሕመምንም ፈተና ልትዋጉ ያስፈልጋችኋል»[2]::

## በወጅ ውስጥ ፈውስ አለ

እንቅስቃሴው የጤንነትና የብልጽግና ትምህርቱን ለማጽናት መሠረት የሚያደርግበት ሌላው ነጥብ፣ «የክርስቶስ ወጅአዊ ሥራ አካላዊ ፈውስንም ያካተተ ነው» የሚለው ነው:: ክርስቲያኖች ከአካላዊ በሽታ ነጻ ናቸው ለማለት የሚጠቀሱት ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው (ኢሳ 53÷4-5፤ ማቴ 8÷16-17፤ 12÷15-16፤ 1ጴጥ2÷24)::

ሐጌን ይህን አስተምህሮ በተመለከተ እንዲህ ይላሉ፣ «ተፈጥሮአዊ ከሆነው እውነት የምንማረው፣ አንድ ሰው የሚያመው ከሆነ በአካሉ ውስጥ በሽታ መኖሩን ነው:: ነገር ግን ቃለ እግዚአብሔር፣ 'እርሱ ድካማችንን ተቀበለ ደዌያችንንም ተሸከመ' (ማቴ 8÷17) ይለናል፤ እንዲሁም በእርሱ ቍስል መፈወሳችንን (1ጴጥ 2÷24):: ለመሆኑ በአንድ ወቅት እውነት የሆነው የእግዚአብሔር ቃል በሌላ ጊዜ እውነት አይሆንምን? በበሽታ ታሞ የመዳንን ያህል ይህ እውነት የሆነ ጕዳይ አይደለምን? የስሜት ሕዋሳቶቻችሁ የሚነግሩአችሁን በማመን፣ 'ፈውስ የለኝም፤ ታምሜያለሁ' ትሉ ይሆናል፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል በማመን፣ 'ተፈውሻለሁ፤ በእርሱ ቍስል ተፈውሻለሁ ' ልትሉ ይገባል»[3]::

በክርስቶስ ወጅአዊ ሥራ ውስጥ አካላዊ ፈውስም መልስ ስላገኘ፣ ፈውሳችን ሙሉ ለሙሉ እንዴት እውን ማድረግ እንደምንችል ሐጌን እንዲህ ይላሉ፣ «ፈውስ በአካል ላይ ሊገለጽ ይችላል፤ ምክንያቱም በቌሳዊ ነገር የሚገለጠው በመንፈሳዊው ዓለም እውን የሆነው ነገር ብቻ ስለሆነ፤ ይህ ደግሞ መንፈሳዊ በረከት ነው:: እግዚአብሔር አንተን ለመፈወስ ያልሠራው ሥራ የለም፤ በሽታንና ሕመምን በኢየሱስ ላይ አድርጐአል. . . የእግዚአብሔር ቃል በሚለው መሠረት ፈውስህን ተቀበል»[4]::

## የንጉሥ ልጆች ነን!

ባለጠጎችም ሆነ ጤናሞች የማንሆንበት ምክንያቱ ምንድን ነው? የንጉሥ ልጆች አይደለንም እንዴ? የሚለው ነጥብ እንቅስቃሴው፣ «ጤንነትና ብልጽግናን» አስመልክቶ ለሚያስተምረው ትምህርት አራተኛ ነጥብ ነው::

---

[2] Copeland, Our Covenant With God ገጽ 28::
[3] Hagin, Real Faith, ገጽ 9፡22
[4] ዝኒ ከማሁ ገጽ 25::

እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ እግዚአብሔር ደግሞ የተትረ ፈረፈ ሕይወት በጁ በደጁ ነው:: ብሩም ወርቁም የእርሱ ነው:: ታዲያ ጤናሞችና ባለጠጎች የማንሆንበት ምክንያቱ መንድን ነው?

እንደ እምነት እንቅስቃሴ አስተምህሮ ድኽነትና በሽታ ሰይጣን በእኛ ላይ ያኖረው ቀንበር ነው:: ሰዎች በኀጢአት ሲወድቁ ሰይጣን የዚህች ምድር ሕጋዊ አምላክ ሆነ፤ ሰይጣን በእኛ ላይ ሥልጣን እንዲኖረው ያደረገውም ይኸው ምክንያት ነው:: ይህን አስመልክተው ሐጌን እንዲ ይላሉ:- «ኢየሱስ ሊዋጀን የመጣው ከሰይጣን ባርነትና ኀይል ነው. . . በሕይወት ላይ ንጉሥ እንድንሆን ነው:: ሕይወታችንን መግዛት እንድንችል ነው:: እንድንገዛ እንጂ በእርሱ ቊጥጥር ሥር እንድንሆን አይደለም:: ድኽነት በአንተ ላይ አይንገሥ፤ አይምራህም:: ነገር ግን በድኽነት ላይ ልትነግሥ እንዲሁም ልትመራው ይገባል:: በበሽታ ላይ ልትነግሥ ልትመራውም ይገባል:: ከክርስቶስ ሕይወት የተነሣ ልትነግሥ ተጠርተሃል፤ ቤዛነትንም ያገኘነው በክርስቶስ ነው»[5]::

## ጤንነትና ብልጽግና የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው!

የእንቅስቃሴው አራማጆች ክርስቲያን መታመምም ሆነ ድኻ መሆን የለበትም፤ ስለዚህ «የእግዚአብሔር ሕዝብ ጌታ ያዘጋጀለትን ጤንነትና ብልጽግና በሕይወቱ ተግባራዊ ሊያደርገው ይገባል» ባዮች ናቸው:: በእንቅስቃሴው መምህራን መሠረት ሐዋርያው ዮሐንስ፣ «ወዳጅ ሆይ፤ ነፍስህ እንደሚከናወን፣ በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ» (3 ዮሐንስ 2) ያለሁ ለዚሁ ነው ባዮች ናቸው:: ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ጥቅሶችም ይጠቀሳሉ (መዝ 103÷2-3፤107÷20፤ ማር 10÷29-30):: ፈውስን በተመለከተ አዘውትረው የሚጠቅሱት ጥቅስ ያዕቆብ 5÷10-20 ነው:: «የእምነት ጸሎት ድውዩን ያድናል፤ ጌታም ያስነሣዋል» (ያዕ 5÷15) ስለሚል በእምነት የተጸለየ ጸሎት ድውያንን ሁሉ የማይፈውስበት አንዳችም ምክንያት የለም::

## የእምነት እንቅስቃሴ ጤንነትና ብልጽግናን በተመለከተ የሚያስተምረው ትምህርት ግምገማ

ጳውሎስ፣ ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሞተው በሕግ ከመጣብን መርገም ዐርነት ሊያወጣን ነው የሚለው የእንቅስቃሴው አስተምህሮ፣ ትክክል ነው (ገላ 3÷13):: ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስ ወጅአዊ ሥራ ከቅዱሳን ትንሣኤ በፊት ሙሉ የሆነ አካላዊ ፈውስ ያመጣል አላለም:: በክፍሉ ጳውሎስ እያስተማረ ያለው፣ የአብርሃም በረከት ቍሳዊ ሳይሆን መንፈሳዊ መሆኑን ነው (ቊ 6)፤ ይኸውም፣ «የመንፈስን ተስፋ በእምነት» መቀበልን::

በሽታና ድኽነት በሕግ በኩል የመጣብን ርግማን ነው የሚለው የእንቅስቃሴው ትምህርት ሙሉ ለሙሉ ትክክል ነው:: ዘዳግም 28 መሠረት በማድረግ ክርስቲያን ድኽነትና በሽታ ሊነካው አይችልም ማለት ግን ፍጹም ስሕተት ነው:: ዘዳግም 28

---

[5] Hagin, New Thresholds of Faith ገጽ 53-54::

እስራኤል ለአምላኳ ለእግዚአብሔር የምትታዘዝ ከሆነ፣ እግዚአብሔር በአገር ደረጃ (ማለትም እንደ መንግሥት) የሚባርካትን በረከት የሚገልጽ ነው (ዘዳ 28÷1-14)። በአንጻሩ ደግሞ አምላኳ እግዚአብሔርን ባትታዘዝ እግዚአብሔር በበሽታና በድኽነት እንደሚቀጣት ያስተምራል (ዘዳ 28÷15-68 በተለይ ቍጥር 20-21፡ 36-37፡ 45-48፡ 58-59 ይመለ ከቷል)። የእንቅስቃሴው መምህራን በሽታና ድኽነት ከሰይጣን እንጂ ከእግዚአብሔር አይመጣም የሚለው ትምህርት ከክፍሉ አስተመህሮ ጋር የሚጻረር ነው። በዚሁ ምዕራፍ ብቻ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ መርገም እንደሚያመጣባት ዐሥራ ስድስት ጊዜ (16) ተደጋግሞ ተነግሮአል።

በአጠቃላይ ዘዳግም 28 መሠረት በማድረግ፣ ለእስራኤል እንደ አገር (ሕዝብ) የተነገረውን፣ የአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖችንም የሚወክል ነው ማለት ስሕተት ነው።

## በወጆ ውስጥ ፈውስ አለ

በኢየሱስ ክርስቶስ ወጆአዊ ሥራ ውስጥ አካላዊ ፈውስና ቈሳዊ ብልጽግና አለ የሚለው የእንቅስቃሴው ትምህርት ሙሉ ለሙሉ ትክክል ነው። ነገር ግን እንቅስቃሴው ይህን መሠረት በማድረግ አሁን እውን ይሆናል የሚለው ትምህርቱ ስሕተት ነው። ይህ እውን የሚሆነው የሞት መውጊያ ከተሰበረ፣ ትንሣኤ ሙታን ከሆነ በኋላ ነው። ከትንሣኤ በፊት ያለው አካላችን ደካማ እንዲሁም ፈራሽ ነው፤ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ገለጻ፣ «ተፈጥሮአዊ ነው»። ከትንሣኤ በኋላ ግን ይህ አካላችን የማይበሰብስ፣ የከበረና ኀይልን የተሞላ ይሆናል (1ቆሮ 15÷42-45)። እስከዚያው ግን ለሥቃይና ለመበስበስ በተገዛ ተፈጥሮ ውስጥ የክርስቶስን መጽአት(መገለጥ) እየተጠባበቅን እንኖራለን(ሮሜ 8÷18-23)። ሮሜ 8÷18-23 ሆነ ሌሎች በርካታ የአዲስ ኪዳን ንባባት፣ የክርስቶስ ወጆአዊ ሥራ ያመጣልንን በረከት በአሁኑ ሕይወት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ እንደማይሆን ይገልጻሉ። የክርስቶስ ዳግም ምጽአት «የከበረ ተስፋችን» ነው የምንልበትም ምክንያት ይኸው ነው። አሁን ከክርስቶስ የደኸንነት ሥራ ተጠቃሚ የሆነው መንፈሳዊ የሆነው ማንነታችን ነው፤ ይኸውም የኀጢአት ስርየት ማግኘታችን፣ መጽደቃችን እንዲሁም ሌሎች መንፈሳዊ የሆኑ በረከቶች ናቸው (ሮሜ 3÷24፤ ኤፌ 1÷3-4፤ ቆላ 1÷12-14)።

ከላይ እንደተመለከትነው ሙሉ የሆነው በረከት እውን የሚሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ ነው። በዚህ ሕይወት የክርስቶስ ወጆአዊ ሥራ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ስላልሆነ ነው፣ ክርስቲያኖች አካላዊ ሞት የሚሞቱት (1ተሰ 4÷13-17)።

አካላዊ ፈውስን በተመለከተ የሚጠቀሰው ሌላው ጥቅስ፣ ኢሳይያስ 53÷5 ነው፣ «እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቈሰለ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበር፤ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን»። «ስለመተላለፋችን» እና «ስለ በደላችን» የሚሉት ቃላት አንድ ዐይነት ትርጕም የሚወክሉ ናቸው (ቢያንስ ተቀራራቢ)። እንደዚሁ ሁሉ፣ «ቈሰለ» እና «ደቀቀ» የሚሉትም ቃላት በተለዋዋጭነት ጥቅም ላይ የዋሉ አንድ ዐይነት (አሊያም ተቀራራቢ) ትርጕም ያላቸው ናቸው። የክፍሉ ትምህርት የኀጢ አተኞችን ቅጣት («ተግሣጽ») ኢየሱስ ስለተሸከመ የእርሱ ቈስል ሌሎችን ፈወሰ። ሐዋርያው ጴጥሮስ በመልእክቱ ይህን የብሉይ ኪዳን ክፍል በመጥቀስ ፈውሱ ከኀጢአት እንደ ሆነ ይገልጻል (1ጴጥ 2÷24)፤ ክፍሉ የሚገኝበትም ዐውድ ስለ አካላዊ ፈውስ የሚገልጸው ነገር የለም።

በአንጻሩ ደግሞ ማቴዎስ ኢየሱስ ሰዎችን ከአካላዊ በሽታ መፈወሱ የኢሳይያስ 53÷4-5 ትንቢት ፈጻሚ እንደ ሆነ ያስተምራል፤ ኢየሱስ ይህ ያደረገው ኀጢአትን ይቅር ለማለት ሥልጣንንና ኀይል እንዳለው ለማሳየት ነው:: በቀጣዩ ምዕራፍ (9÷1-7)ላይ የምንማረው ይህንኑ እውነት ነው፤ ይኸውም ሽባውን ሰው የፈወሰው ኀጠ ኢአትን ለማስተሰረይ ሥልጣን እንዳለው ለማሳየት ነው፣ «በምድር ላይ ኀጢ አትን ያስተሰርይ ዘንድ ለሰው ልጅ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ፣ በዚያን ጊዜ ሽባውን፦ ተነሣ፤ ዐልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ አለው» (ቍ 6):: ኢሳይያስ 53÷5 ጌታ መንፈሳዊውን ደኅንነት ብቻ ሳይሆን አካላዊውንም በሽታ እንደሚፈውስ ይገልጻል:: ነገር ግን ልብ ልናደርገው የሚገባን ጉዳይ፣ ኢየሱስ ኀጢአትን ይቅርታ በሰጠበት ቦታ ሁሉ አካላዊ ፈውስን ሲያካሂድ አንመለከትም:: ጌታ ለቤተ ክርስቲያን የፈውስ አገልግሎትን ሰጥቶአል፤ ነገር ግን ሁሉም አይፈወሱም፤ የኀጢ አት ይቅርታ ስላላገኙ ሳይሆን እግዚአብሔር ስለፈቀደ ብቻ ነው:: የኢሳይያስ 53÷5 ትንቢት ሙሉ ፍጻሜ የሚያገኘው፣ ከትንሣኤ በኋላ ነው:: በሽታና ሕመም፣ ችግርና ጉስቁልና እንዲሁም ሞት ለዘላለም ድል የሚደረጉት ከትንሣኤ በኋላ ነውና::

## ለመንገሥ መጻለይ

ኬኔት ሐጌንን ጨምሮ በርካታ የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን፣ ጳውሎስ በሮሜ 5÷17 ላይ ክርስቲያኖች «በሕይወት መንገሥ» አለባቸው የሚለው አሁን ነው የሚል አቋም አላቸው:: ነገር ግን ጳውሎስ፣ «በሚሞተው ሥጋችሁ ኀጢአት አይንገሥ» ይላል እንጂ (6÷12-13) «በሚሞት ሥጋችሁ በሽታ አይንገሥ» አይልም:: «ይነግሣሉ» የሚለው ግሥ መጪውን ጊዜ የሚያመለክተውም ለዚሁ ነው::

ጳውሎ፣ «አሁን ነግሡናል» የሚሉትን የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች፣ «አሁን ጠግባችኋል፤ አሁንስ ባለ ጠጎች ሆናችኋል፤ ያለእኛ ነግሣችኋል» እያለ ድካማቸውን በምፀት ይገልጥላቸዋል (1ቆሮ 4÷8):: ጳውሎስና የእርሱ የወንጌል ተባባሪዎች ግን ለክርስቶስ ሲሉ ደካሞች እንደ ሆኑ፣ እንደ ተራቡ፣ እንደ ተጠሉ፣ መጠለያ እንኳ እንዳልነበራቸው ያስረዳል (1ቆሮ 4÷8-13)::

የእንቅስቃሴው መምህራን ቃለ እግዚአብሔር <u>ወደፊት</u> በሙላት ይሆናል የሚለውን ጉዳይ፣ <u>አሁን</u> እንደሚሆን አድርገው መውሰዳቸው የችግሩ ዋነኛ ምክንያት ነው:: ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ፣«ክፉ ከሆነው ከአሁኑ ዓለም ያድነን ዘንድ እንደ አምላካችንና እንደ አባታችን ፈቃድ ስለ ኀጢአታችን ራሱን ሰጠ» (ገላ 1÷4) ይላል፤ ነገር ግን ዛሬም «ክፉ በሆነው በአሁኑ ዓለም ውስጥ እንኖራለን:: ጳውሎስ በዚህ ዓለም ስትኖሩ፣ «ይህንን ዓለም አትምሰሉ» (ሮሜ 12÷2) የሚለን፣ በክፉው ዓለም ዛሬም እየኖርን ስላለ ነው:: የእግዚአብሔር መንፈስ በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ ይሁን እንጂ ሟች ነን (ሮሜ 8÷9-11):: በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ አሁን ስላለንና ወደፊት በሙላት ስለሚሆነው ነገር በግልጽ እያስተማረ የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን አሁን በሙላት እንነግሣለን ማለታቸው በፍጹም አግባብነት የላቸውም::

# አዘወትረው የሚጠቀሱ ጥቅሶች

ከዚህ በመቀጠል የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን «ክርስቲያኖች የእምነት ቃል በመናገር ጤንነትና ብልጽግናን ገንዘባቸው ማድረግ ይችላሉ»:: ለሚለው ትምህርታቸው መደገፊያ አድርገው የሚጠቀሙባቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በአጭሩ እንመልከት፡-

## «እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ (3 ዮሐንስ 2)

የእንቅስቃሴው አራማጆች አዘወትረው የሚጠቅሱት ጥቅስ ሐዋርያው ዮሐንስ ለወዳጁ ለጋይዮስ የጸለየውን ጸሎት ነው፣ «ወዳጄ ሆይ፤ ነፍስህ እንደሚከናወን፣ በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ» (3ዮሐ 2):: ወዳጆቻችን እንዲከናወንላቸውና ጤና እንዲያገኙ መጸለይ መልካም ነው:: ነገር ግን መጸለያችን ለማግኘታችን ዋስትና አይደለም:: መጸለይ የእኛ ፈንታ ነው፤ እንዳሻው ማድረግ ደግሞ የእግዚአብሔር:: ሐዋርያው ወደ እግዚአብሔር የጸለየው የጋይዮስ ብልጽግናና ጤንነት የእግዚአብሔር ጉዳይ ስለሆነ ነው:: ልብ ልንለው የሚገባን ሐዋርያው ለወዳጁ ለጋይዮስ ጤንነትና ብልጽግና የእኔ ነው እያለ እንዲያውጅ (የእምነት ቃል እንዲናገር) አልመከ ረውም::

## «'መቶ ዕጥፍ' እንድታገኝ» (ማርቆስ 10÷29-30)

የጤንነትንና የብልጽግናን አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ለማስደገፍ የሚጠቀሰው ሌላው ጥቅስ፣ ማርቆስ 10÷29-30 ነው፤

> «ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ፡- እውነት እላችኋለሁ፣ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ቤትን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም ዕርሻን የተወ፣ አሁን በዚህ ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችን ወንድሞችንም እኅቶችንም እናቶችንም ልጆችንም ዕርሻንም መቶ ዕጥፍ፣ በሚመጣውም ዓለም የዘላለም ሕይወት የማይቀበል ማንም የለም»::

በክፍሉ ኢየሱስ ቃለ በቃለ እኔን ለመከተል ስትል ቤትህን ከተውህ አንድ መቶ ቤት እሰጥሃለሁ፤ ወይም እኔን ለመከተል ብለህ እናትህን ከተውህ አንድ መቶ እናት እሰጥሃለሁ እያለ ነው? አይደለም! የክፍሉ ትምህርት ለጌታ ስንል የሥጋ ዘመዶቻችንንም ሆነ ንብረታችንን ብንተው ብዙ ወንድሞችን፣ እኅቶችን፣ እናቶችን ወዘተ በጌታ ቤት ውስጥ ማለትም በቤተ ክርስቲያን እናኛለን የሚል ነው፤ እነዚህ ሰዎች ያላቸውም ነገር ሁሉ፣ የእኛ ንብረት ይሆናል ማለት ነው:: በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁሉ የታየው ይኸው እውነት ነው::

## «እግዚአብሔር መድኀኒቴ ነው» (መዝ 103÷2-3፤ 107÷20)

ለትምህርቱ ድጋፍ ከመዝሙር የሚጠቀሱትን ሁለት ክፍሎች ደግሞ እንመልከት፡-

በመዝሙር 103÷2-3 ባለው ክፍል ዳዊት፣ እግዚአብሔር ኀጢአ ቱን ሁሉ ይቅር እንደሚለውና ደዌውንም ሁሉ እንደሚፈውስለት ይገልጻል።

ነገር ግን ዳዊት ይህ ንግግር በየትኛውም ዘመን ለነበሩ፣ ለማናቸውም ሰዎችና፣ ላለባቸው ሁሉ በሽታ የሚሆን ቃል ኪዳን አይደለም፤ በጊዜው የነበረ የዳዊት መረዳት እንጂ። ለምሳሌ በቁጥር 4 ላይ ዳዊት፣ «ሕይወትሽን ከሞት የሚያድናት» ይላል፤ ክፍሉ የሚያወራው በአካለ ሥጋ ስላለመሞት ነው፤ ነገር ግን ዳዊት ይህን ይበል እንጂ በአካለ ሥጋ አልሞተም ማለት አይደለም። ይህን ክፍል መሠረት አድርገን ክርስቲያኖች አይታመሙም፣ በአካለ ሥጋም አይሞቱም ማለት እንችላለን? ይህ እውነት ሊሆን የሚችለው በዚኛው ዓለም ሳይሆን በሚመጣው ዓለም (ከትንሣኤ በኋላ) ነው።

መዝሙር 107÷20 ዘማሪው በእግዚአብሔር ላይ ስላመፁና እግዚአብሔርም ስለቀጣቸው ሰዎች ይገልጻል፣ «ሰውነታቸው መብልን ሁሉ ተጸየፈች፤ ወደ ሞትም ደጆች ቀረቡ» (ቊ 18)። ከዚህ የነተሣም ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፤ እግዚአብሔርም ሰማቸው (ቊ 19)። ክፍሉ በአንድ የተወሰነ ሁኔታ ውስጥ ስለሆነ ነገር ያወራል እንጂ፣ በየትኛውም ጊዜና ቦታ ስለሚገኙ ሰዎች «የፈውስ ቀመር» አይደለም።

## ልንታመም አንችልም!
## (ያዕቆብ 5÷10-11)

የእንቅስቃሴው መምህራን ክርስቲያን ምናልባት ሥቃይ ሊደርስበት ይችላል ነገር ግን ሥቃዩ በሕመም ምክንያት ሊሆን አይችልም ባዮች ናቸው። ለዚህ ትምህርት በዋቢነት የሚጠቀሰው ጥቅስ ያዕ 5÷10-11 ነው። ይህን ይበሉ እንጂ ክፍሉ ክፍሉ የኢዮብ የሥቃዩ ምክንያት ሕመሙ እንደ ነበር ይገልጻል (ቊ 10-11)። እንዲያውም አንዳንድ የእንቅስቃሴው መምህራን ኢዮብ ያለማመን ምሳሌ እንደ ሆነ ያስረዳሉ። ይሁን እንጂ ያዕቆብ ይህን ትምህርት አይደግፍም። ስለዚህም ኢዮብ የመታገሥ ምሳሌ እንደ ሆነ ይገልጻል (ቊ11)። እንደ ያዕቆብ ትምህርት ደግሞ ትዕግሥት የእውነተኛ እምነት ዐይነተኛ ምሳሌ ነው (ያዕ 1÷3-4)

በርካታ የእንቅስቃሴው አራማጆች የኢዮብ ሥቃይ የራሱ ድካም (ስንፍና) እንደ ሆነ ይገልጻሉ። ኢዮብ፣ «እግዚአብሔር ሰጠ፤ እግዚአብሔርም ነሣ» እንዲሁም፣ «ከእግዚአብሔር እጅ መልካሙን ተቀበልን፤ ክፉ ነገርንስ አንቀበልምን» ማለቱ የችግሩ ሁሉ ምክንያት እንደ ሆነ ያስረዳሉ። ቃለ እግዚአብሔር ግን፣ «ኢዮብ በከንፈሩ» እግዚአብሔርን አልበደለም ይለናል (ኢዮብ 1÷21-22፤ 2÷10)። ኢዮብ ይህ ሁሉ መከራ የደረሰበት፣ «አሉታዊ ንግግር በመናገሩ ነው» የሚለው የእንቅስቃሴው ትምህርት ድርሳነ ፈጠራ ነው። ኢዮብ የፈራው ነገር እንደ ደረሰበት መግለጹ እሙን ነው(ኢዮብ 3÷25)። ነገር ግን ቃለ እግዚአብሔር ፍርሀቱ ለደረሰበት መከራ (ሥቃይ) ምክንያት ነው አይለንም።

የኢዮብ ባልጀሮች ለሥቃዩ ምክንያት ናቸው ያሏቸውን ነገር ከዘረዘሩ በኋላ ኢዮብ ራሱን በማጽደቁ ምክንያት ንስሓ ገብቶአል (40÷3-5፤ 42÷1-6)። የኢዮብ ጓደኞች ስለ ኢዮብ የተናገሩት ነገር ስሕተት ነበር (42÷7)። ይኸውም ሥቃይ የመጣበት በኀጢአቱ

ምክንያት ነው ማለታቸው:: ይህ የባልንጀሮቹ ንግግር ስሕተት ከሆነ ኢዮብ መከራ የደረሰበት በኀጢአቱ ምክንያት አይደለም ማለት ነው::

# ዋቢ መጻሕፍት

## ማጣቀሻ መጻሕፍት


1. Bowmen, Robert M, Jr. *Orthodoxy and Heresy: A Biblical Guide to Doctrinal Discernment* (Grand Rapids: Baker, 1992)
2. Stein, Robert H. *A Basic Guide to Interpreting the Bible: Playing by the Rules* (Grand Rapids: Baker, 1994)
3. Wilkinson, John, *The Bible and Healing A Medical and Theological Commentary.* (Grand Rapids: Eerdmens, 1998)
4. *Anchor Bible Dictionary.* Freedman, David Noel, ed., (New York: Doubleday 1997).
5. *Living By Faith*


## በእምነት እንቅስቃሴ መምህራን የተጻፉ መጻሕፍት


- Capps, Charles. *Faith and Confession* (Tulsa: Harrizon House, 1987) የጸሓፊውን አስተምህሮ በስፋት የሚተነትን መጽሐፍ ነው::
- Copeland, Kenneth. *The Blood Covenant* (Fort Worth Kenneth Copeland Ministries,1992) ከሌሎቹ የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን ጋር ሲነጻጸር ኮፕላንድ ብዙ አልጻፉም:: ትምህርታቸው በስፋት የሚደመጠው በካሴት ነው:: ይህም የካሴት ትምህርት የግለሰቡን ትምህርት በስፋት የሚተነትን ነው::
- ----------------*"What Happened from the cross the Throne"* ይህም በካሴት የቀረበ ትምህርት ነው::
- Hagin, Kenneth E. *The Name of Jesus*, (Tulsa: Kenneth Hagin Ministries, 1979). ዕውቅ የሐጊን መጽሐፍ ነው::
- ----------------*New Thresholds of Faith* 2d ed. (Tuisa: Kenneth Hagin Ministries, 1989). የእንቅስቃሴው ዕውቅ መምህር ስለ እንቅስቃሴው አስተምህሮ በስፋት የተነተኑበት መጽሐፍ ነው::
- Price, Fredrick K.C *Name It and claim It! The Power of Positive Confession* (Tulsa: Harrison House, 1992) የእንቅስቃሴውን አስተምህሮ የተነተነ አፍሪካ አሜሪካዊ ሰባኪ ነው::

- *The Word Study Bible* (Tulsa Harrison House, 1990) በትልቁ የእምነት እንቅስቃሴ ማተሚያ ቤት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አብሮ የታተመ የማጥኛ ጽሑፍ ነው:: የማጥኛ ጽሑፍን ያዘጋጁት የእንቅስቃሴው ዕውቅ መምህራን ናቸው::


## የእምነት እንቅስቃሴን ትምህርት «ከአደጋ» ለመጠበቅ የተዘጋጁ መጻሕፍት


- Bruno, Michael, *Chritianity in Power*, (Slippery Rock, Pa.: Abba Ministries, 1994) ይህ መጽሐፍ፣ «ክርስትና በቀውስ ውስጥ ነው» በሚል ርእስ ሃኒግራፍ ለጻፈው መጽሐፍ የተዘጋጀ መልስ ነው::
- DeArteaga, William L. *Quenching the Spirit: Discover the REAL Spirit Behind the Charismatic Controversy* (Lake Mary, Fla.: Creation House, 1996) «ክርስትና በቀውስ ውስጥ ነው» ለሚለው ለሃኒግራፍ መጽሐፍ የተዘጋጀ መልስ ነው:: ጸሐፊው በእንቅስቃሴው ውስጥ ትክክል ያለሆኑ ትምህርቶች እንዳሉ ቢቀበልም ከዘመናዊቹ የእንቅስቃሴው መምህራን ይልቅ ኬኒዮንን ይበልጥ

እንደሚቀበል ይፋ አድርጎአል። የእምነት እንቅስቃሴ አስተምህሮ «ከአደጋ» ለመጠበቅ ከተሠሩት መጻሕፍት ውስጥ ይህ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል።

- Spencer, James R. *Heresy Hunters: Character Assassination in the Church* (Lafayetta, La.: Huntington House, 1993) መናፍቃንን በመከላከል አገልግሎት ውስጥ የነበረና ቀድሞ የሞርሞንን እምነት ይከተል የነበረ ሰው ነው።

## የእምነት እንቅስቃሴን አስተምህሮ ለማሔስ የተጻፉ መጻሕፍት


- Barron, Bruce. *The Health and Wealth Gospel.* (Downers Grove, Ill.: Inter Varsity Press, 1987) ጸሓፊው የእምነት እንቅስቃሴን አስተምህሮ ፊር የለቀቀ የጴንጤቆስጤአውያን ልምምድ አድርጎ ነው ያቀረበው። በርካታ ዐቃቤ ክርስትናዎች ግን በጸሓፊው ድምዳሜ ላይ አይስማሙም።
- Bowman, Robert M. Jr, *The Word Faith Controversy: Understanding the Health and Wealth Gospel* (Grand Rapida: Baker, 2001) የእምነት እንቅስቃሴን አስተምህሮ ምሁራዊ በሆነ ሁኔታ ያይሔሰ መጽሐፍ ነው። ጸሓፊው ኬንየን የእንቅስቃሴው ቀዳማይ አመንጪ ነው የሚለውን ጕዳይ አይስማም። ይህ አቋሙ በእንቅስቃቀሴው ላይ በርካታ መጻሕፍትን ከጻፉ ምሁራን በእጅጉ የሚለየው ነው።
- Farach, Charles, Jr. *From the Pinnacele of the Tample: Faith vs Presumption* (Plain Field, N. J: Logos International, 1979). ጸሓፊው የጴንጤቆስጤ አማኝ ቢሆንም የእንቅስቃሴው ስሕተት መሆኑን አጠንክሮ የሐየሰ ምሁር ነው።
- Fee, Gordon D. *The Disease of the Health and Wealtn Gospel* (Costa Mesa, Calif The World for Today, 1979) የጴንጤ ቆስጤን አስተምህሮ የሚቀበል የተከበረ የአዲስ ኪዳን ሊቅ ነው። በዚህች አነስተኛ መጽሐፍ የእንቅስቃሴውን ትምህርት ምሁራዊ በሆነ ሁኔታ ሐይሶታል።
- Hanegraff, Hank. *Christianty in Crisis* (Eugene, Ore.: Harvest House, 1993) ጸሓፊው የእምነት እንቅስቃሴ የጰንጤቆስጤን አስተምህሮ ያጐደፈ ነቀርሳ ነው የሚል አቋም አለው።
- ----------------------*Counterfeit Revival.* (Dallas word, 1997) በቶሮንቶ እንቅስቃሴ ላይ የተሠራ ሒስ ነው። እንዲሁም ከቶሮንቶ እንቅስቃሴ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን እንቅስቃሴዎች ሁሉ፣ ያላቸው ሰንካላነት ያሳያል።
- Horton, Michael, ed. *The Agony of Deceit* (Moody 1990) የተለያዩ ምሁራን በእምነት እንቅስቃሴ መምህራን ላይ ያቀረቡትን ጽሑፍ የያዘ ነው።
- Hunt, Dave, and T.A. Macmahon. *The Seduction of Christianity.* (Eogene,ore. . . Harvest House, 1985) በብዙ ሰዎች ዘንድ በስፋት የተነበበ ተወዳጅ መጽሐፍ ነው።
- MacArthur, John. *Charismatic Chaos* (Grand Rapids 20ndervan,1992) መጽሐፉ የእምነት እንቅስቃሴን አስተምህሮ ብቻ ሳይሆን የጰንጤቆ ስጤንም አስተምህሮና ልምምድ ክፉኛ ያይሒሳል።
- McConnell, D.R. *A Different Gospel: A Historical and Biblical Analysis of the Modern Faith Movement.* (Peabody, Mass.: Hendrickson Publisher, 1995) በእምነት እንቅስቃሴ ላይ የሠሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን፣ ለትምህርታቸውና ለጽሑፋቸው ዋነኛ ምንጭ አድርገው የተጠቀሙት ይህን መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ ከኬየን የእንቅስቃሴው ጀማሪ ናቸው የሚል አቋም አለው።
- Moo, Douglas, gen ed. *The Gospel and Contemporary Perspectives: Viewpoints from Trinity Journal* (Biblical Forum servies 2. Grand Rapids: Kregel 1991) በእንቅስቃሴው ላይ የተሰጠ ምሁራዊ ሒስ ነው።